

ዝግጅት

ሙሐመድ ቢን ሙኽታር
አሽ– ሺንቂጢ

# የቁርአን ጠቢብ

## ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ

### ሕይወትና ፋናቸው

ትርጉም

ዐብዱራህማን ሰዒድ
(ሜጢ)

# የቁርአኑ ጠቢብ ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ

ዝግጅት ሙሐመድ ቢን ሙኽታር አሽ-ሺንቂጢ

ትርጉም

ዐብዱራህማን ሰዒድ(ሜጢ)

الوسطية للنشر والتوزيع
Al-Wasatiyyah Publishing

| | |
|---|---|
| ርዕስ | የቁርአኑ ጠቢብ ሙሐመድ ዐብደላ ድራዝ |
| ደራሲ | ሙሐመድ ቢን ሙኽታር አሽ-ሺንቂጢ |
| ተርጓሚ | ዐብዱራህማን ሰዒድ(ሜጢ) |
| እትም | ፩ኛ እትም እ.ኤ.አ 2020 |
| አሳታሚ | ወሶጢያ ህትመት |
| ኢሜይል | alwasatiyyapublishing@gmail.com |

# የቁርአኑ ጠቢብ

# ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ

Copyright © 2020 Al-Wasatiyyah Publishing

## ማውጫ


*መቅድም* ..................................................................................................... 1

የጥናቱ *መግቢያ*..................................................................................... 5

ክፍል አንድ ፡- *የዕውቀት ቋቱ ድራዝ ሕይወት እና ፋናቸው*............. *11*

ክፍል ሁለት በድራዝ እሳቤ ውስጥ የሚዛናዊነት ጎልቶ መታያዎች..... 33

ክፍል ሶስት በድራዝ እሳቤ ውስጥ የተሐድሶ ማዕዘናት........................ 89

ማጠቃለያ..................................................................................................... 116

## በአላህ ስም እጅግ በጣም አዛኝ በጣም ርህሩህ በሆነው

## መቅድም

ይህ ጥናት የዶክተር ዐብደላህ ሙሐመድ ድራዝን የአስተሳሰብ ፍሬና የሕይወት ስሪታቸውን እየቃኘ የሚያስተዋቃቸው አጭር ዳሰሳ ነው፡፡

አንባቢ በ20ኛው ክፍለዘመን ከነበሩ ሙስሊም ከዋክብት መሃል አንዱ የሆኑትን እኚህ ሊቅ በጥልቀት ያውቃቸውና ፅሁፉም ፈጣን መርጃ ይሆነው ዘንድም እመኛለሁ፡፡ በመቀጠል እርሳቸው የደረሱባቸውን የላቁ እሳቤዎችና በመፅሐፍቶቻቸው ውስጥ አኑረው ያለፏቸውን ሉል እስትንፋሳዊ ፍካሬዎች ፣ የሕይወት ታሪካቸው የዳበረበትን አስተምህሮ በራሱ ተነሳሽነት ይመራመር ዘንድም እመኛለሁ፡፡

በድራዝ ስብዕና ውስጥ በጥቂት የ20ኛው ክፍለዘመን ሙስሊም ከዋክብት ላይ ካልሆነ በስተቀር  አንድ ላይ ተሰባስበው የማይገኙ ባህሪያት ሰፍረዋል፡፡ ሸይኹ በምስራቁና በምዕራቡ ባህል፣ በሸሪዓዊ ዕውቀትና አቋም መሃል፣ በአስተሳሰብ ጥልቀትና በመንፈሳዊ ምጥቀት መሃል ሰብስበው ይዘዋል፡፡ እነዚህ ነጥቦች (የ20ኛው ክፍለዘመን ሙስሊም ነቢባን) የሚለውን መፅሐፍ ሳዘጋጅ እንደ መለኪያ ተጠቅሜያቸዋለሁ፡፡ ድራዝ በርግጥ ከነዚያ ነቢባንም መሃል ሆነው በጥቂቱ ተዳስሰዋል፡፡ ነገርግን በድራዝ ሕይወትና እሳቤ ላይ ከነቢባኑ ጋር መድቤ ብቻ አልቆምኩም፡፡ ይልቁንም እንደዚህ ሰፋ ባለ መልኩ ስለርሳቸው ብቻ  በማጥናት እዳስሳቸው ዘንድ ውስጤ ገፋኝ፡፡

ይህን ጥናት ሰርቼ ያጠናቀቅኩት ከአምስት ዓመታት በፊት የነበረ ቢሆንም ሌሎች ኃላፊነቶችና መጣበቦች የሕትመት ብርሃን ሳያገኝ እንዲቆይ አድርገውታል፡፡ ዛሬ ግን በቀረዷዊ ‹የእስልምና ወሰጢያና ተሐድሶ ማዕከል› እና ዶሐ በሚገኘው ሐመድ ቢን ኸሊፋ ዩኒቨርሲቲ የኢስላማዊ ጥናት ፋካልቲ ትብብር ሕትመቱ ብርሃን አገኘ፡፡

መፅሐፉ በመሰረታዊነት ተፅፎ ይጠናቀቅ ዘንድ የቀረዷዊ ማዕከል የጥናት ዕቅድ ውስጥ መካተቱና ክትትል ስለነበረውም ጭምር ነው፡፡ ማዕከሉ ድራዝ በሚዛናዊነትና ተሐድሶ ዘርፍ የነበራቸውን አበርክቶ ትኩረት እንድናደርግበት አድርጎናል፡፡

የድራዝ ድርሳናት በሸሪዓና አኽላቅ ሳይንስ ማዕከል ሁነኛ አበርክቶ አላቸው፡፡ ሸይኽ ድራዝ በዘመናችን «የቁርአን ስነ-ምግባር» (አኽላቀል ቁርአን) ዕውቀት ዘርፍ መስራች ናቸው፡፡ በዘርፉ ከዚህ በፊት ያልተንኳኩ በሮችን ከይዘትና ጥልቅ ዳሰሳ አንፃር ከፍተው ገብተዋል፡፡ ድራዝ የተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች መገናኛና መገጣጠሚያ መንገድ ናቸው፡፡ ከነርሱ ውስጥ የቁርአን ሳይንስ፣ የእምነቶች ታሪክና የስነ-ምግባር ሳይንስ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

አል-ዓላማህ ሸይኽ አል-ጀሊል ዶክተር ዩሱፍ አል-ቀረዷዊ ለሸይኻቸው ዶክተር ድራዝ ውለታ መሙላት፣ የሸይኽ ድራዝ ስራዎች ስብስብ ያለበትን የግል ቤተ-መፅሃፍቻቸውንና ቢሯቸውን ለዚህ ጥናት ክፍት ስላደረጉልኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናቸዋለሁ፡፡ የሸይኽ ድራዝንና ስለርሳቸው የተሰሩ ስራዎችን በሚገባ አጥንቻለሁ፡፡ ኢማም አል-ቀረዷዊን አላህ መልካም ምንዳቸውን ይክፈላቸውና ብዙ ስራዎቻቸውን ቅጂ እንዲኖረኝም ጭምር አውሰውኛል፡፡

ይህን መቅድም ሳልቋጭ በፊት የድራዝ ቤተሰብ ግብፃዊ ከመሆኑ ጋር ሞሮኳዊ የእሳቤ፣ ዘርና የዝንባሌ ማንነት መቀራረብ እንዳላቸው መግለፅ እወዳለሁ። ምናልባትም ግን «ዕውቀት ለባለቤቶቹ ሰብሳቢ ማሕፀን ነው።» እንደሚባለው የማሊኪ መዝሃብ ተከታይ[1] ስለነበሩና በታሪክም ዘራቸው በርሱ ስለታወቀ ይሆናል። የሸይኽ ሙሐመድ ድራዝ ወላጅ አባት የሆኑት ሸይኽ ዐብደላህ ድራዝ የአቢ ኢስሓቅ አል-አንደሉሲ አሽ-ሻጢቢን «አል-ሙዋፈቃት» መፅሐፍ ማብራሪያ ሰርተዋል። ልጃቸው ሙሐመድ ድራዝ ደግሞ ማረጋገጫና እርምት ሰርተውለታል[2]። ቀጥለውም የሻጢቢን አል-ኢዕቲሷም መፅሐፍ አስመልክቶ ዳሰሳ ሰርተው፤ ሳይቋጩት በሞቱት «አል-ሚዛን በይነ ሱነቲ-ወል-ቢድዓቲ» በተሰኘ መፅሐፋቸው ውስጥ አዲስ እሳቤን እንዲወልድና እንዲታደስ ሙከራ አድርገዋል።

በሐዲስ የጥናት ዘርፍ ሰርተፊኬት ከሰጧቸው ሁለቱ ከዋክብት የሞሮኮ ሸይኾች ሲሆኑ የሚጠቀሱት (ከ1884-1962) የኖሩት ሸይኽ ሙሐመድ ዐብዱልሐይ አል-ከታኒ እና (ከ1878-1943) የኖሩት ሸይኽ ሙሐመድ ሐቢበሏህ ቢን ማያቢ አሽ-ሺንቂጢ ይገኙበታል። ድራዝ (አል-ሙኽታር ሚን ኩኑዚ ሱና) በተሰኘ መፅሐፋቸው መግቢያ ላይ እኒህን ጉምቱዎች አውስተዋቸዋል። [3]

ድራዝ ፈረንሳይ ውስጥ በ20ኛው ክፍለዘመን አጋማሽ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት ከአልጄሪያዊው ፈላስፋ ማሊክ ቢን ነቢ ጋር በጠንካራ ወንድማዊ ገመድ ተሳስረው ነበር።

---

[1] ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፤ዲራሳት ኢስላሚያ ፊል ዓላቃት ደውሊያ ወልኢጅቲማዒያ

[2] አቡ ኢስሐቅ አሽ-ሽጢቢ፣ አል ሙዋፈቃት ፊ ኡሱሊ ሸሪዓ

[3] ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፡ ሚን ኩኑዚ ሱና

በሁለቱ ሰዎች መሃል የአስተሳሰብ መመሳሰል በግልፅ ይታይ ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ የቁርአንን ጥናት ዘርፍ በማደሱ ረገድ የደረሱበት ውጤት ተመሳሳይ ነው፡፡

በክፍል ሶስት ላይ ይህን ጉዳይ በዝርዝር አይተነዋል፡፡ ጉዳዩ በአስተሳሰብና ህሊና ከመቀራረብ አልፎ ወደ ወንድማዊ መተሳሰብና ወደ ጋራ የትግል ውህደትም ተሻገረ፡፡ እርሱም የምዕራባዊ ዓረባዊቱን አልጀሪያ ከፈረንሳይ ቅኝ አገዛዝ ጨቋኝ ስርዓት ነፃ ትወጣ ዘንድ ከሚታገሉት ጋር አብረው ሆኑ፡፡ በዚህ መንገድ ላይ ፈረንሳይ ውስጥ ነዋሪ፣ ተማሪና ስደተኛ በሆኑበት ሁኔታ ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ጭምር ነበር የታገሉት፡፡ እኔም ዛሬ ላይ አንደ አንድ ከአካባቢያቸው እንደተገኘ ሰው ስለ ድራዝና አስተሳሰባቸው ስፅፍ በደስታ ነው፡፡

*ሙሐመድ ቢን ሙኽታር አሽ-ሺንቂጢ*

*ደውሐ ቀጠር ረመዷን 10/1437*

*15/06/2016*

## የጥናቱ መግቢያ

ከሸይኽ ዶክተር ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ (ረዐ) እሳቤ ጋር ያለኝ ቁርኝት የጀመረው ከረዥም ዓመታት በፊት ነው፡፡ ወቅቱ 1990 ሲሆን በዶክተር ዐብዱሶቡር ሻሂን ወደ ዐረብኛ የተተረጎሙትን «አዝ-ዟሂረቱል-ቁርአኒያ» እና «ዊጅሃቱ ዓለመል ኢስላሚ» የተሰኙትን በፈረንሳይኛ የተፃፉትንና የአልጀሪያዊውን አሰላሳይ የማሊክ ቢን ነቢ መፅሃፍት በማነብበት ወቅት ነበር፡፡ አገላለፁ ምጡቅ ግንዛቤውም ሰፊ የነበረውን የማሊክ ቢን ነቢን ስራዎች ትርጉም መስራታቸው በእውነቱ ዶክተር ዐብዱሶቡር ሻሂን አስደንቀውኛል፡፡

በዚያው ዓመት ሞሪታኒያ «ዑዩን» ከተማ ውስጥ አንዲት ትንሽ መፅሐፍት መደብር ውስጥ ዓይኔ ድንገት አንድ አይቸውም ይሁን ሰምቼው በማላውቀው መፅሐፍ ላይ አረፈ፡፡ የዶክተር ድራዝ «ዱስቱሩል-አኽላቅ ፊል ቁርአን» ነበር፡፡ የመፅሐፉ ይዘት ስለ ቁርአን ክሪም ሲሆን ተርጓሚው ደግሞ ዶክተር ዐብዱሶቡር ሻሂን ናቸው፡፡

ምንም አላንገራገርኩም ! ገዛሁት፡፡ ለካ የመፅሃፉን ዋጋ ሳላውቀው እጄ ውስጥ የገባው ከኢስላማዊ አስተሳሰብ ቋቶች ከሆኑት የአንዱ እና ከቁርአን እውነተኛ መንፈሱ ምንጮች ውስጥ በአንዱ ስብዕና ላይ ነበር፡፡ አናቅፁ ከመርዘማቸው ፣ ከአገላለፁ ጥንካሬ ፣ ከአስተሳሰቡ ጥልቀት ጋር መፅሐፉን በቀናት ውስጥ በላሁት፡፡ አንዳያልቅብኝ ከመመኘት ጋር ከአንድ ጊዜ በላይም ደጋግሜ አነበብኩት፡፡

በስተመጨረሻም ዶክተር ድራዝ ማለት በኢስላማዊ አስተሳሰብ ካርታ ላይ ዛሬ እየኖርን ባለው የባህል ነውጥ፣ ጩኸትና የድምፆች መደበላለቅ ሳቢያ ቦታቸውን ያላገኙ ግን የዕውቀት ድልብ እንደሆኑ ተረዳሁ፡፡

ቀናት ቢነጉዱም፣ ዓመታት ቢፈተለኩም እኔ ዘንድ ድራዝ ከአስተሳሰብና መንፈስ ምንጫቸው የምዘግንባቸው ጥልቅ የዒልም ማዕዴ እንደሆኑ ዛሬ ድረስ አሉ፡፡

አርሳቸው እኔ ላይ ካሏቸው መብቶች ውስጥ አስደናቂ ሕይወታቸውን አጉልቼ የማሳይበትን፣ ሰምጠው የገቡባቸውን የላቁ እሳቤዎቻቸውን ገላልጬ የማወጣበትን የሆነን ይህን ጥናት መፃፍ አንዱ ሆኖ አገኙሁት፡፡ ታዲያ ጥናቱ ለኡመተል ኢስላም አንዲሁም ለሰው ልጅ ባጠቃላይ መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ ምኞቴ ነው፡፡

**የቀደሙ ጥናቶች**

ደክተር ድራዝን በተመለከተ ብዙ ቁጥር ያላቸው ጥናቶች ተሰርተው ወጥተዋል፡፡ ይህኛው ጥናት በተከተለው ዘዴ ለሚነሱ ጥያቄዎች በሁለት ጉዳዮች አሳጥረን እንመልሳለን፡፡

<u>የመጀመሪያው</u>፡- የቀደሙት ጥናቶች በሁለት የሚከፈሉ ናቸው፡፡ አንዱ ክፍል የርሳቸውን ድርሳናት ማሰባሰብና ማጠናቀር ነው፡፡ ይህን ዘርፍ ኳታራዊው ሸይኽ ዐብደላህ አንሷሪ የጀመሩት ሲሆን የሸይኽ ድራዝን በድምፅ የተላለፉ ንግግሮች ***«አኽላቁል ቁርአን»*** እና ***«ሐዲቀቱል አዝሃር»*** በሚሉ ርዕሶች በተሰናዱ መፅሐፍት ሰብስበው አሰራጭተዋቸዋል፡፡ የኳታር እምነት ጉዳዮች አስተዳደር በአዲስ ህትመት በተጨማሪ አሰራጭቶታልም፡፡

ይህ ዘርፍ ከ20 ዓመታት በኋላ ቆመና የድራዝ አገር ሰው የሆኑትን ሸይኽ አሕመድ ሙስጠፋን አላህ በድራዝ ድርሳናት ስብሰባና ማብራራት ስራዎች ላይ በፍቅር የተጠመዱ ሰው ሆነው አመጣቸው፡፡

በዚህ ዘርፍ ደግሞ ይህ ትልቅ ሸይኽ ብዙ ለፍተዋል፡፡ የድራዝን የማይታወቁ አያሌ መፅሐፍት አጠናቅረዋል፡፡ የተበታተኑ ንግግሮቻቸውንና ህዝባዊ ገለፃዎቻቸውን ሰብስበዋል፡፡ ***«ሐዲዱል ቀለም» «ዲራሳት ኢስላሚያ ፊል ዐላቃቲ ደውሊያ ወል ኢጅቲማዒያ» «ዛዱል ሙስሊሚ ሊዲኒ ወል ሐያት»*** የተሰኙ ሌሎች ጥራዞችን አሰራጭተዋል፡፡

ኡስታዝ ፈዲላም የተበታተኑ የድራዝን ስራዎች፣ ስለ ሸይኹ የተማሪዎቻቸውን ዕይታ በማዘጋጀት ሌላ ውለታ ሰርተዋል፡፡ ከዚህ ኡስታዝ አስመስጋኝ ጥረት በፊት ዐረብና ሙስሊም አንባብያን ከሸይኽ ድራዝ መፅሐፍት ጥቂቶቹን (ዱስቱሩል አኽላቅ ፊል ቁርአን፣ ነበኡል ዐዚም፣ አድ- ዲን፣ በትንሹ ደግሞ መድኸል ኢለል ቁርአኒል ከሪም) አንጂ አያውቅም ነበር፡፡ ከዶክተር ድራዝ ቤተሰብ ወይም ከግል ዲያሪያቸው ያገኙትን የሕይወት ታሪካቸውን በጥልቀት ስለገለጡልንም ኡስታዝ ፈዲላን እናመሰግናለን፡፡ ለምሳሌ በአንዋር ጁንዲ በኩል የተፃፈ «ዶክተር ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ ዲራሳት ወ ቡሑስ ቢአቅላሚ ተላሚዚሂ ወ ሙዓሲሪሂ»[4] የሚል ርዕስ ያለው የጥናት ስራ አሰራጭተዋል፡፡ ይህን ትልቅ ስብዕና በጥልቀት ለመረዳት ወሳኝ ዝርዝሮች ናቸው፡፡

የሸይኽ ድራዝን ስራዎችና ጥረቶች የተመለከተው የርሳቸውን ስብዕና ትንታኔ የያዘው ዓይነት ደግሞ *ሁለተኛው ክፍል* ነው፡፡ ማለትም «ዶክተር ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ ዲራሳት ወ ቡሑስ ቢአቅላሚ ተላሚዚሂ ወ ሙዓሲሪሂ»[5] በሚለው ስር ስለ ድራዝ የዕውቀት አበርክቶ

---

[4] አህመድ ሙስጠፋ ፈዲላ

[5] ዝኒ ከማሁ

የሚያትተው ክፍል ነው፡፡ እኔ ጥናቱን በምሰራበት ወቅት በዚህ ዘርፍ ከመጡ ስራዎች ሁለት መፅሐፍት ናቸው፡፡

- ዶክተር ሐፊት ሙሐመድ ሙኒር አል-አዝሃሪ «በዘመናዊው የኢስላማዊ አስተሳሰብ የሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ አበርክቶ» በሚል ያዘጋጁት አንዱ ሲሆን፤ የድራዝን የሕዳሴ እሳቤ ያሳነሰ፣ በውርስ ባህል ብቻ ራሱን የወሰነ ጥናት ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ፋይዳ ቢኖርም ግን የድራዝን እሳቤ ዋጋውን የሚያውቅና ጥልቀቱን የተረዳ የጥናት ሰው ያሻው ነበር፡፡
- ሁለተኛው መፅሐፍ ደግሞ ቀደም ሲል ያወሳነው የሸይኽ ሙሐመድ ፈዲላ ነው፡፡ ቀደም ሲል በጋዜጦችና መፅሔቶች የተሰራጩ ሐምሳ አካባቢ የዕውቀት ርዕሶች የተዳሰሱበት ድርሳን ነው፡፡

ከነዚህ በተጨማሪ ሶስት የዩኒቨርሲቲ ማስተርስ ፕሮግራም የመመረቂያ ፅሁፎችም ተሰርቶባቸዋል፡፡

1) «የሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ የዳዕዋ አበርክቶ»
አዘጋጅ ጧሚ ቢን ሑደይፋ አል-በቅመ፤ ኢማም ሙሐመድ ቢን ሱዑድ ዩኒቨርሲቲ
2) «ዶክተር ድራዝና የበላጋ ዘርፍ ጥናታቸው»
አዘጋጅ ሙሐመድ አሚን አቡ ሹህባ፤ ካይሮ ዩኒቨርሲቲ
3) «ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ የስነ-ምግባር ጥናት መንገዳቸው»
ዝግጅት ሙሐመድ አል-በዩሚ ዐብዱልዋሒድ አዝሃር ዩኒቨርሲቲ

ይህ ጉምቱ ልሂቅ ከአስተሳሰባቸው ስርገት፣ ከሎጂካቸው ብርታት፣ ከመንፈሳቸው ምጥቀት አንፃር አንደ አዲስ ቢጠኑም አይቆጭም፡፡

በኢስላማዊው እሳቤ ውስጥ የነበራቸውን አበርክቶና የተሐድሶ ተግባር አሁንም እንደ አዲስ የሚያጠናው ያሻዋል፡፡

ስለ ሸይኽ ድራዝ የቀደሙ ስራዎች ሳስብ ማሊክ ቢን ነቢ ስለ ኢብኑ ኸልዱን ያጤነውን ያስታውሰኛል፡፡ ማሊክ ቢን ነቢ የስልጣኔዎች መንኮታኮት አላባውያንን ሲናገር ፡- «የአዕምሮን ተፅዕኖ በማይገነዘብና ወደ ተግባር ሊያመጣው አቅሙ በሌለው ማህበረሰብ ውስጥ የተበታተነ ስለሆነ ድብቅና ብዙሃኑ የማያውቀው ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ የኢብኑ ኸልዱን እሳቤዎች ከወቅቱ ፈጥነው ወይም ዘግይተው የመጡ ይመስላሉ፡፡ የራሱ የሆነ ተጣጣፊነቱን፣ መሻሻልና የተሃድሶ ባህሪውን በወቅቱ ያጣ ሁኔታ ስለነበር ከኢስላም ብርቅዬዎች ውስጥ ሊደነባ አልቻለም፡፡»[6] ነበር፡፡ በተመሳሳይ ድራዝም ከወቅታቸው ፈጥነው ወይም ዘግይተው የመጡ የዘመን ክስተት ናቸው፡፡ እሳቤዎቻቸው ዛሬ ድረስ በኢስላማዊው አስተሳሰብ ዘርፍ ደምስር አልተሰራጨም፡፡ ከዚህ በመነሳት ስለ ድራዝ ማውሳትና እሳቤያቸውን ትኩረት ለመቸር ሲባል ነው የዚህ ጥናት አስፈላጊነትም፡፡ እዚህ ላይ ግን የዓላማችን የብርሃን ጨረር ትኩረት የሚያደርገው በድራዝ እሳቤ ውስጥ የተሐድሶ ማዕዘኖች ላይ ነው፡፡ በመጀመሪያው የጥናት ክፍል የድራዝን ሕይወት፣ የመጠቀ ስብዕናቸውን፣ የአስተሳሰብ ዳናቸውንና የስነ-ፅሁፍ መንገዳቸውን በተቻለ አቅም ዳስሰናል፡፡

ቀጥለን ሁለተኛውን ክፍል ከእሳቤያቸው ውስጥ የወሰጢያ (የሚዛናዊነት) ጎልቶ መታያዎች፣ በኢስላማዊው አስተሳሰብ ውስጥ ጠንከር ያለ የመግለፅ ተግዳሮት ያለባቸውን ትላልቅ የሚሰኙ የጣምራ

---

[6] ማሊክ ቢን ነቢ «ዊጅሃቱል ዓለመል ኢስላሚ»

ፅንሰ-ሐሳቦችን እርሳቸው በገለፁበት መንገድ የምንዳስስበት ነው፡፡ ጣምራዎቹ

1. ዐቅል (አዕምሮ) እና ነቅል (አንቀፅ ተኮርነት)
2. ጀብር እና ኢኽቲያር
3. ዒልም (ሳይንስ) እና ዲን (እምነት)
4. ሱና እና ቢድዓ
5. ሲልም (ሰላም) እና ሐርብ (ጦርነት) ናው፡፡

ድራዝ ከነዚህ የእሳቤ ተግዳሮቶች ጋር የተደራጀና ልዩ መስተጋብራቸው ምን ይመስል እንደነበር ተመልክተናል፡፡

በሶስተኛው ክፍል የድራዝ የተሐድሶ እሳቤ ማዕዘናትን አይተናል፡፡ የተሐድሶ እሳቤያቸው ጎልቶ የወጣው ሁለት የዕውቀት ዘርፎችን የመሰረቱበት የቁርአን ሳይንስ ነው፡፡ ሁለቱ የጥናት ዘርፎች ደግሞ (**አኽላቁል ቁርአን**) እና (**መስደሩል-ቁርአን**) ናቸው፡፡

ይህ ጥናት የችሮታም ይሁን የቀዳሚነት ትሩፋት አለው፤ የተሟላና ሁለንተናዊም ነው አንልም፡፡ ነገርግን ይህን የአንፀባራቂ መንፈስ ባለቤት የሆኑትን ኮከብ በማስተዋወቁ ረገድ ክፍተት ይሞላል የሚል ተስፋ አለን፡ ፡ የድራዝን እሳቤዎች በተመለከተ ለሌሎች የጥናት ሰዎችም አጋዥ ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

# ክፍል አንድ

# የዕውቀት ቋቱ ድራዝ

# ሕይወት እና ፋናቸው

## የሕይወት ታሪካቸው

ኖቬምበር 18 ፣ 1894 ግብፅ ከፍሩ ሸይኽ አውራጃ ታላቁ ዐሊም ሙሐመድ ዐብደላህ ቢን ሙሐመድ ቢን ሑሰነይን ድራዝ ተወለዱ፡፡ የዲን፣ የዕውቀትና ስነ-ምግባር ባለቤት በሆነ ቤተሰብ ውስጥ ታንፀው አደጉ፡፡ ቅድመ-አያታቸው ሙሐመድ እና ሁለተኛ አያታቸው ሑሰነይን አካባቢያቸው ላይ ባለው ዑመሪይ መስጂድ ውስጥ ኢስላምን በማስተማር የሚታወቁ መምህራን ነበሩ፡፡

አባታቸው ሸይኽ ዐብደላህ ድራዝ (ከ18-741932 የኖሩ) ደግሞ አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በኡሱሉል ፊቅህ እና ቋንቋ ዘርፍ ታዋቂ ምሁር ነበሩ፡፡ የኢማም አሽ-ሻጢቢን «ሙዋፈቃት» መፅሐፍም ማብራሪያ አዘጋጅ ናቸው፡፡ ማብራሪያውን ብዙ አንባቢዎችና የጥናት ሰዎች በስህተት የልጃቸው ድራዝ አድርገው ያስቡታል፡፡[7] ከዚህ ቤተሰብ ውስጥ የተገኙት ሌላው ኮከብ ደግሞ የሙሐመድ ዐብደላህ ወንድም የሆኑትና በአዝሃር ዩኒቨርሲቲ የተፍሲር ፋካልቲ መምህር ሆነው ያገለገሉት ዐብዱልመጂድ ዐብደላህ ድራዝ ናቸው፡፡

---

[7]በዚህ የአባትና የልጅ ስም አንባቢን መምታታት እንዳያጋጥመው ሲባል፣ በጥናቱ ውስጥ ያለምንም ገደብ ድራዝ የሚለው ስም ሲመጣ አባትየውን ሸይኽ ዐብደላህ ማለታችን ሳይሆን ዶ/ር ሙሐመድ ዐብደላህን ነው፡ ፡

ሙሐመድ ረጀብ አል-በዩሚ እንደሚያወሱት የድራዝ አባት ታማኝ የተርቢያ እና እነፃ ሰው ናቸው፡፡ እንዲህም ሲሉ ይገልጧቸዋል ፡-«ቤታቸውን በተቅዋ ስርዓት የያዙ ናቸው፡፡ የዒሻና ፈጅር ሶላቶችን ለመላው ቤተሰባቸው መሪ ሆነው ያሰግዳሉ፡፡ በረመዷን ለሊቶች ሰሒሕ አል-ቡኻሪን ጭምር ያነባሉ፡፡ ለልጆቻቸው መልካም የተባለን በሙሉ፣ ሶላትን፣ ጾምና ዘካን ለማስተማርና ለማለማመድ እንቅልፍ ያጡ ነበር፡፡ ሰናይና ከፍ ያሉ ተግባራትን ወዳጅ፣ ዝቃጭና ከወረዱ ነገራት ይርቁላቸው ዘንድ ይተጉ የነበሩ ተግባራዊ መመህር ነበሩ፡፡»[8] ይላሉ፡፡

ድራዝ ገና በልጅነት የመጀመሪያውን አስር ዓመታቸውን እንኳ ሳይሞሉ ነበር ቁርአንን በቃላቸው የሸመደዱት፡፡ አባታቸው የአዝሃርን ቅርንጫፍ ለመመስረት ወደ አሌክሳንደሪያ ከተማ ተመድበው ሲዘዋወሩ ከቤተሰባቸው ጋር በ1905 አብረው ተዘዋወሩ፡፡

ወጣት ድራዝ አባት በመሰረቱትና በሚያስተዳድሩት ማዕከል በተማሪነት ተመዘገቡ፡፡ በ1908 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ምስክር ወረቀት አገኙ፡፡ አባት ሸይኽ ድራዝ አሕመዲ ዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነው ወደ ጠንጣ ሲዘዋወሩ የአዝሃርን የመማር ማስተማር የተሞክሮ ስርዓት ይዘው ነበር የተጓዙት፡፡ ከዚያው ጃሚዕ መስጂድ ድራዝ በ1912 የሁለተኛ ደረጃ ሰርተፊኬታቸውን አገኙ፡፡ በመቀጠል አባት ድራዝ ከመላው ቤተሳበቸው ጋር በመሆን ወደ አሌክሳንደሪያ የአዝሃር ቅርንጫፍ ማዕከል ዳግም ተመለሱ፡፡ ከዚህ ማዕከል ልጅ ድራዝ ዓለማቀፍ የምስክር ወረቀትን ከሁሉም በተሻለ ብቃት ተቀዳጁ፡፡

[8] አህመድ ፈዲላ « ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፡ ዲራሳት ወ ቡሑስ ቢአቅላሚ ተላሚዘቲሂ ወ ሙዐሲሪሂ

የድራዝ የመጀመሪያ የማስተማር ተሞክሮ በ1916 እዚያው ማዕከል ዕድሜያቸው ገና 20ዎቹን ሳይሻገር ነበር፡፡ ከማስተማር ስራቸው ጎን ለጎንም በኢንኪባብ ትምህርት ማዕከል በማታ ፈረቃ ፈረንሳይኛ ቋንቋን ይማሩ ነበር፡፡ በሶስት ዓመታት ውስጥ የፈረንሳይኛን ልሳን ድርና ማግ ልቅም አደረጉት፡፡ በ1919 በፈረንሳይኛ ቋንቋ በተሻለ ማዕረግ ተመረቁ፡፡

ይህን ቋንቋ መማራቸው አገራቸው በ20ዎቹ ማገባደጃ ገደማ ግብፅ ከአንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነፃ ትወጣ ዘንድ በተደረጉ የነፃነት እንቅስቃሴዎች ላይ ሲሳተፉ በጣም ጠቅሟቸዋል፡፡ አገራቸው ከእንግሊዝ ነፃ ትወጣ ዘንድ ግብፅ ውስጥ በነበሩ የሌላ አገራት ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች በር ፊት በፈረንሳይኛ ቋንቋ ዲስኩር (ንግግር) ያደርጉበት ነበር፡፡ ያኔ ታዲያ ጊዜው ከ1918-1919 ድረስ ነበር፡፡

የፈረንሳይኛ ቋንቋ ከዚህም ባሻገር ፈረንሳይ ውስጥ ከብዙ ዓመታት በኋላ ሰርቦን ዩኒቨርሲቲ በነበሩበት ጊዜ በእጅጉ ጠቅሟቸዋል፡፡

በ1928 ድራዝ ለስራ ጉዳይ ወደ አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ተዘዋወሩ፡፡ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በተለያዩ ክፍሎች ላይ አስተማሩ፡፡ ድራዝ በዕድሜ ከርሳቸው ከሚበልጡት የቀደሙ መምህራን ሁሉ ሳይቀር ስማቸው በጊቢው ውስጥ ገነነ፡፡

በ1936 ድራዝ ወደ ሐጅ ስርዓት መከወኛዋ ቅድስት ስፍራ መካ ተጓዙ፡፡ ከዚያ ሲመለሱ በፈረንሳዩ ሰርቦን ዩኒቨርሲቲ ስኮላርሺፕ ዕድል አገኙ፡፡ ፈረንሳይ ውስጥ ለ12 ዓመታት በትጋትና ትግል፣ የምዕራቡን የፍልስፍና እና ስነ-ምግባር ባህል ከዋና ምንጩ በጥልቀት ከመረዳትና በቁርአን ውስጥ ካሉ የስነ-ምግባር ዕውቀት መርሆች ጋር በማነፃፀር ቆዩ፡፡ ድራዝ ከሰርቦን ዩኒቨርሲቲ የላይሰንስና ዶክትሬት ዲግሪንም ተቀዳጁ፡፡

የዶክትሬት ዲግሪያቸውን የተመረቁበት «አኽላቁል ቁርአን» ወይም (La Morale Du Koran) የጥናትና መመረቂያ ጽሁፋቸው ሉዊስ ማሲኒዮንና ሌቪ ብሮፌንሳልን የመሳሰሉ የፈረንሳይ አንቱ የተሰኙ ኦሬንታሊስቶችን አፍ ያስከፈተ ነበር፡፡ ዲፌንስ ያደረጉበት ቀንም 15/12/1947 ነበር፡፡[9]

ድራዝ ከዚህ ዘለግ ያለ የዕውቀት ፍለጋ ጉዞ በኋላ ወደ ግብፅ ሲመለሱ በ1949 በሃይአት ኪባረል ዑለማእ ውስጥ አባል ሆኑ፡፡ በተጨማሪ ግብፅ ውስጥ ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች ብዙ ርዕሶችና ኮርሶች ላይ ሌክቸረር ሆነው አገልግለዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ

- በአዳብ ፋካልቲ ውስጥ የታሪኹል አድያን
- በዳረል ዑሉም ኮሌጅ ውስጥ የተፍሲር ኮርስ
- በዐረብኛ ቋንቋ ፋካልቲ ውስጥ የአኽላቅ ፍልስፍና
- በፖሊስ ማሰጠልኛ ኮሌጅ ውሰጥም ብዙ ዘርፎችን አስተምረዋል፡፡[10]

«ካይሮ ውስጥ በኢኽዋነል ሙስሊሚን ማዕከላት ቋሚ ሌክቸሮችን፣ የተለያዩ ሴሚናሮችን፣ ኮንፈረንሶችንና ውይይቶችንም ያሰናዱ ነበር፡፡ ድራዝ ከሃይአት ኪባረል ዑለማእ አባልነት በተጨማሪ ብዙ የዕውቀት ተቋማት ውስጥ ኮሚቴ ነበሩ፡፡»[11] ከነርሱ ውስጥ

- በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ የመማር ማስተማር ከፍተኛ አመራር ቦርድ አባል
- የብሮድካስት ከፍተኛ ቦርድ አባል

[9] ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ ፣ዱስቱሩል አኽላቅ ፊል ቁርአን ከዶክተር ሰይድ ሙሐመድ በደዊ ለመፅሐፉ ከሰጡት መቅድም የተወሰደ
[10] አህመድ ፈዲላ «ዲራሳት ኢስላሚያ ፊል ዓላቃት ደውሊያ ወል ኢጅቲማዒያ» ለተሰኘው የድራዝ ስራ ከሰጡት መቅድም

[11] ሙሐመድ ዓብደላህ ድራዝ ሸይኽ ዐብደላህ አል አንሷሪ ለሚን ኹሉቂል ቁርአን ከሰጡት መቅድም

- የአዝሃር መማክርት ኮሚቴ አባል
- የአዝሃር አጠቃላይ የፈተናዎች ቁጥጥር ወሳኝ ኮሚቴ ሆነው አገልግለዋል፡፡

ድራዝ በተጨማሪም ብዙ ዓለማቀፍ ኮንፈረንሶችን ተሳትፈዋል፡፡ ከነርሱ ውስጥ

- በ1939 ፓሪስ ውስጥ የተካሄደው ዓለማቀፍ የኃይማኖቶች ኮንፈረንስ
- በ1950 ደግሞ ፈረንሳይ ኒይስ ከተማ ዓለማቀፍ የዩኒቨርሲቲዎች ኮንፈረንስ
- በ1951 ፓሪስ ውስጥ የኢስላማዊ ድንጋጌ (አት-ተሽሪዑል-ኢስላሚ) ኮንፈረንስ
- በ1958 ፓኪስታን ውስጥ በኢስላማዊ የዕውቀት ባህል ላይ ያጠነጠነ ኮንፈረንስ ላይ ተሳታፊ ነበሩ፡፡

በዚህኛው የመጨረሻው ኮንፈረንስ ላይ በ1958 በፓኪስታኗ ላሆር ከተማ ሳሉ ያ ታላቅ ጉምቱና አብሪ ኮከብ የሆኑት ድራዝ ወደ ጌታቸው አላህ እዝነት ተዘዋወሩ፡፡ ወደ አኼራ የሄዱት «ኢስላም ከሌሎች እምነቶች ጋር ያለው ግንኙነቱና አቋሙ» በሚል ርዕስ ያዘጋጁትን ጥናት ሳያቀርቡት ነበር በልብ ሕመም (ስራ ማቆም) የሞቱት፡፡ የኮንፈረንሱ አድማስ በሐዘን ተሞላ፡፡

ሸይኹ ከዚህች ዓለም ነፍሳቸው ብትጓዝም የጥናት ስራቸው ኮንፈረንሱ ላይ ተነበበ፡፡ አስክሬናቸው ወደ አገራቸው ግብፅ ተሸኘ፡፡ በአዝሃር መስጂድ ህልቆ መሳፍርት የጀናዛ ሶላት ሰገደባቸው፡፡ ቁጥሩ በውል የማይታወቅ ህዝብ ወደ መካነ-መቃብራቸው ሸኛቸው፡፡ በግብፅም ይሁን በሌሎች የሙስሊሙ ዓለም ያሉ ሊቃውንት ሁሉ ሀዘናቸውን ገለፁ፡፡

ከነርሱ ውስጥ ሸይኽ መሕሙድ ሸልቱት ይጠቀሳሉ፡፡ እንዲህ የሚል ዐረፍተ-ነገርም ተናገሩ «የመኃይምነትን ነበልባል ያጠፋው የብርሃን ችቦ ሞተ፡፡»[12] ነበር ያሉት፡፡

ድራዝ የአምስት ወንድና የአምስት ሴት ልጆች አባት ነበሩ፡፡ በ1956 ከወራሪዋ እስራኤል ጋር በነበረ ጦርነት ሰማዕት የሆነው የወታደራዊ ጦር አውሮፕላን አብራሪ የነበረው ሶፍወት ድራዝ፣ ጡረታ የወጡት አምባሳደር ፈትሒ ድራዝ፣ የቀዶ ጥገና ዶክተሩ ሰዒድ ድራዝ፣ ፈረንሳዊ ዜግነት የነበራቸው ዶክተር ሙሕሲን እና ስዊዘርላንድ የሚኖሩት ተርጓሚው ሳሚ ድራዝ ናቸው፡፡ አምስቱ ሴት ልጆቻቸው ደግሞ ፈትሒያ፣ ሰዐድ፣ ኢሕሳን፣ ሶፊያ እና ሳሚያ ናቸው፡፡

## ስብዕናዊ ገፅታቸው

የዶክተር ዐብደላህ ድራዝን ባህሪ በመኗኗርም ይሁን ስለርሳቸው ሲነገር በስሚስሚ የሚያውቋቸው ሁሉ የሚስማሙት ስብዕናቸው ከጠራ ማንነት የተሰበዘ፣ ከጠንካራ ማገር የተሳገ፣ ከመጠቀ መንፈስና ከሰላ አዕምሮ የተገነቡ መሆናቸው ላይ ነው፡፡

የድራዝን መለያ ስብዕናዊ ባህሪያት ሸይኽ ዐብደላህ አል-አንሷሪ እንዲህ ይዘረዝሯቸዋል፡- «በጣም ፈጣን፣ በሳል፣ ቻይ፣ የተረጋጉ፣ ለሌሎች ተናናሽ፣ አደራ ጠባቂ፣ ውለታን መላሽ፣ ደፋር፣ ለዓላማ የሚቀድሙ፣ እውነት ላይ የማይደራደሩ፣ ልዝብ ተናጋሪ፣ ባለጥሩ ባህሪ እና ለባልደረባ ምቹ ሰው ነበሩ፡፡»[13] ይላሉ፡፡

---

[12] አህመድ ፈዲላ « ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፡ ዲራሳት ወ ቡሑስ ቢአቅላሚ ተላሚዘቲሂ ወ ሙዐሲሪሂ»

[13] ሼኽ ዓብደላህ አል-አንሷሪ ሚን ኩኑዚ ሱና ለተሰኘው የድራዝ መፅሐፍ የሰጡትን መቅድም አንብብ

ሸይኽ ሑሰነይን ሙሐመድ መኸሉፍ የድራዝ ቅርብ ጓደኛ ሲሆኑ ጠቅለል አድርገው ድራዝን ሲገልፁ፡-«ለምደው አላማጅ፣ አዛኝ አፍቃሪ፣ የሚወደዱ ሰው ነበሩ፡፡ የተረጋጋ እና ለምድራዊ ብልጭልጭ ግድ ያልነበራቸው ስብዕና፣ የጠንካራና ጥልቅ እምነት ባለቤት፣ የምድርን አረንጓዴ አዳጊ ተጣሪዎች ችላ ያሉ፣ ከቁስና ፈተናዎቹ የራቁ እንዲሁም ራሳቸውን ፋናቸው ቀሪ በሆኑ መልካም ስራዎች የወጠሩ ነበሩ፡፡ ከሌሎች ገለል ካሉ አላህን ለማውሳት ወይም ቁርአን ከሪምን ሲያነቡ እንጂ በሌላ አታያቸውም፡፡»[14] ይላሉ፡፡

ሸይኽ መኸሉፍ ድራዝ ባህሪ ላይ «የልብ ጓደኛ፣ ለሌሎች እጅግ ተጨናቂ፣ አዛኝ ባልደረባ የሆኑ ተምሳሌታዊ ሰው ነበሩ፡፡ በኩራት ውስጥ ያለ የእርጋታ፣ በመተናነስ ውስጥ ያለ ስክነትና በግዙፍ ስርዓት ውስጥ ያለ የሐያእ ናሙና ናቸው፡፡ ለኢስላም በዝምታ ይሰራሉ፡፡ ከጊዜያቸው፣ ከጤናቸውና እረፍታቸው ብዙውን ያለምንም ስስትና ወደ ኋላ ማለት ያውሉለት ነበር፡፡ »[15] በማለት ይጨምራሉ፡፡

እኛም ዘርዘር አድርገን ከፊል የድራዝን ባህሪያት ለማየት እንሞክራለን፡፡ ድራዝ የኩሩ ነፍስ ባለቤት ነበሩ፡፡ ከዝቃጭና የወረዱ ባህሪያት የራቁ ሰው ናቸው፡፡

የተሸከሙትን የቁርአን ተልዕኮ ዋጋውን ተረድተዋል፡፡ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት አስፈሪ ሁኔታ፣ ፈረንሳይ ለወራሪው የናዚ ስርዓት ተገዢ መሆኗ ትምህርታቸውን እንዳይከታተሉ፣ ከባለቤታቸውና አስር ልጆቻቸው ጋር በመሆን በፍቅር እንዳይኖሩ እንቅፋት አልሆነባቸውም፡፡

[14] ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዘ፣ ሐሲዱል ቀለም መቃላት ወ ቡሑስ ሊሸይኽ ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ የተሰኘውን የኡስታዝ አህመድ ፈዲላን ጥንቅር ተመልከት
[15] ያለፈው ምንጭ

ልጃቸው ሙሕሲን እንደሚናገረው ከሆነ ፓሪስ ውስጥ ከግብፅ ኤምባሲ ለሕይወታቸው በመስጋት እርሳቸውንም ቤተሰባቸውንም ወደ አገራቸው ግብፅ የመመለስ ተደጋጋሚ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡ የሁልጊዜም መልሳቸው ግን ፡-«የመጣሁበት ዓላማዬ እስከ አሁን አልተጠናቀቀም፡፡»[16] የሚል ነበር፡፡ ድራዝ ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ወደ አገር ቤት መመለስን በፍፁም አልተቀበሉትም፡፡

1948 ጁን 8 ቀን የተወረረቺው ፈረንሳይ ላይ አሜሪካ ባደረሰቺው የፍንዳታ ጥቃት ምክንያት ባለቤታቸው ስለተጎዱ ቤተሰቦቻቸውን ብቻ ወደ ትውልድ አገራቸው ግብፅ ለመላክ ተገደዱ፡፡ ከጀግነንትና የነፍስ ኩሩነት መገለጫዎቻቸው ውስጥ የፈረንሳይ መንግስት ብዙ ቁጥር ያላቸውን የናዚ አስተሳሰብ ተከታይ ግብፃውያንን ባሰረበት ወቅት፣ በዚያ አየሩን ፍርሃት ባቆፈነበት ሁኔታ ውስጥ የጀርመንን ፖሊስ ዋና ኃላፊ ረዠም ሰዐት ተወያይተውትና አሳምነውት ከእስር ማስፈታታቸው ይጠቀሳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፈረንሳይ ነዋሪ በነበሩበት ወቅት የዐረባዊቷን ሞሮኮ የነጻነት እንቅስቃሴ በግልፅ መደገፋቸው ነው፡፡ በወቅቱ ሞሮኮ በፈረንሳይ ቅኝ ተገዝታ ነበር፡፡ ከዚህ የነጻነት እንቅስቃሴ መሪዎች ጋር ያለምንም መደባበቅ በግልፅ ነበር ተባባሪ የሆኑት፡፡ በወቅቱ የፈረንሳይ መንግስት የቅኝ አገዛዝ ስርዓቷን የሚቃወሙትን ሁሉ እንደ አሸባሪ ፈርጃለች፡፡

ወደ አገራቸው ግብፅ እንደተመለሱ የእንግሊዝን ቅኝ አገዛዝ ስርዓት ተቃውሞን ዳግም ጀመሩ፡፡ ሲበዛ ነጻነትን ይወዳሉ፡፡ ሌሎችንም ያበረታታሉ፡፡

[16] አህመድ ፈዲላ « ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፡ ዲራሳት ወ ቡሑስ ቢአቅላሚ ተላሚዘቲሂ ወ ሙዐሲሪሂ 16

በሚፍለቀለቀው ብዕራቸውና ምጡቅ አንደበታቸው ወራሪን በመቃወሙ ሒደት ላይ ግንባር ቀደም ናቸው፡፡ ከአገር ውስጥ መሪዎች ፊትም የሚያሳዩት አቋም፣ ጀግንነትና በራስ መተማመን ከውጭ ኃይል ጋር ከሚያደርጉት ፍጥጫ የማይተናነስ ነው፡፡ ድራዝ በ1952 ከተደረገው ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት በፊት ለንጉሱ የስልጣኑን ብዙ አሉታዊ ጎኖችና ክፍተቶች ማስታወሻ ፅፈውለታል፡፡ አርቲክላቸውም በአገሪቱ ላይ መነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

ድራዝ በአገር ውስጥ ጉዳዮች ሚኒስትር ዐይን ሲገቡ አፍታ አልፈጁም፡፡ በሬዲዮ ፕሮግራሞች ላይ በቁርአናዊ ንግግሮቻቸው ስለሚያውቋቸው ግብፅ ውስጥ የእምነት ጉዳይ ከፍተኛ ቦታ ሊሰጧቸው አቀረቡላቸው፡፡ እርሱም «የአዝሃር ዋና ሸይኽ» ይሆኑ ዘንድ ነበር፡፡ እዚህ ጋር የድራዝ ውስጣዊ ማንነት ተገለጠ፡፡ የምኞታቸው እውነታም ተብራራ፡፡ የኃላፊነትና ተጠያቂነትን ክብደት ሳይረዳ ወደ ስልጣን የሚጓጓ ዓይነት ሰው ጉጉትን ጓጉተው ዕድሉን ቀጨም አላደረጉትም፡፡ ጭራሽ አዝሃር ከፖለቲካዊ ስልጣን ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ በአካዳሚያዊ ስራው ብቻ እንዲቀጥልና በተቋሙ ውስጥም እጅግ አስፈላጊ የሚባሉ ተሐድሶዎችን የሚያደርግ ከሆነ የሚል መስፈርትን አስቀመጡ፡፡ አዲሶቹ የወቅቱ የግብፅ ወታደራዊ አመራሮች ይህን መስፈርት አንቀበልም ብለው ውድቅ ሲያደርጉት ድራዝም ስልጣኑን ከመቀበል ራሳቸውን አቅበው ይቅርታ ጠየቁ፡፡ ተደጋጋሚ ጥያቄዎችና የማሳመን ሙከራዎች ቢያደርጉባቸውም ውድቅ በማድረጋቸው ቀጠሉ፡፡

በድራዝ ሕይወት ጠንካራ ከሚባሉ አቋሞች እና ፖለቲካዊ ማታለያዎች ተደርገው ከሚጠቀሱት ውስጥ የጀማል ዐብዱናስር ስርዓት ከከፊል

የአዝሃር ዐሊሞችና ሃይአት ኪባር አል-ዑለማእ እንዲወጣ ያስደረገውን የጀማዓተል-ኢኽዋንን የተመለከተ ‹‹ተውበታቸውና ትድግናቸው ተቀባይነት የሌለው ኸዋሪጆች ናቸው፡፡›› የሚለው ፈትዋ ላይ ይፈርሙ ዘንድ መጠየቃቸው ሌላው ነው፡፡ ወቅቱ በዩሱፍ ጦልዓት፣ ሙሐመድ ፈርገሊ፣ ሰይድ ቁጥብ፣ ዐብዱልቃድር ዐውዳህና ሌሎችም የጀመዓው አባላት አንገት ላይ የመሰቀያ ገመድ የሚጠለቅበትና ሰማዕት እየሆኑ ሩሐቸው ወደ ላይኛው ዓለም የሚጓዙበት ነበር፡፡ ሙስጠፋ ፈዲላ ከአምባሳደር ልጃቸው ፈትሒ ድራዝ ይዘው በዚህ ጉዳይ የአባታቸውን አቋም ይናገራሉ፡፡ እነዚህ የፈትዋ ብያኔዎች ላይ ይፈርሙ ዘንድ ይዞላቸው ለመጣው ሰው ‹‹የኢስላም ልጆች የሚወገዙበት ብያኔ ላይ እንድፈርም ነው የምትሻው !››[17] ብለው መልሰውለታል ይላሉ፡፡

ድራዝ የትም ይሁኑ ወደየትኛውም አቅጣጫ ይጓዙ የኢስላምና የኡማውን ጭንቀት ተሸክመው ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ፕሮፌሰር ኢማም ዩሱፍ አል-ቀርዷዊ እንዲህ ይላሉ ፡-‹‹እርሳቸው ዘንድ ተቀምጠን ስንመለከታቸው ሁሌም በኢስላም ጉዳይ እና በሙስሊሞች ጭንቀት ውስጥ ሆነው ሲብከነከኑ ነው የምናገኛቸው፡፡››[18] ይላሉ፡፡

---

[17] አህመድ ፈዲላ ‹‹ዲራሳት ኢስላሚያ ፊል ዓላቃት ደውሊያ ወል ኢጅቲማዒያ›› ለተሰኘው የድራዝ ስራ ከሰጡት መቅድም

[18] አህመድ ፈዲላ ‹‹ዲራሳት ኢስላሚያ ፊል ዓላቃት ደውሊያ ወል ኢጅቲማዒያ›› ለተሰኘው የድራዝ ስራ ከሰጡት መቅድም

## የአስተሳሰብ መንገዳቸው

በኮከቡ ተማሪያቸው ፕሮፌሰር ኢማም ዩሱፍ አል-ቀረዷዊ አገላለፅ ድራዝ ማለት «የአዝሃር እና የሰርቦን ፍሬ ናቸው፡፡»[19]

ኢስላማዊውንም ይሁን ምዕራባዊውን ዕውቀት በጥልቀት ከመሰረታዊ ምንጮቻቸው ማጥናታቸው ደርዝ-ጠበቅ ዕይታና የልዩ ትንታኔ ሰው ይሆኑ ዘንድ አስችሏቸዋል፡፡ ለየት የሚያደርጋቸው በወቅቱ የብዙዎችን ህሊና በእኩይ መንገድ ሲያወድም ከነበረው የተወረሰ ባህልና የወራሪው ምዕራባዊ እሳቤ ድንበር መሃል ላይ ከፀጉር ስንጠቃ የራቁ መሆናቸው ነው፡፡

ሙስሊሙ ዓለም ዳግም የሚነሳው በሙሐመድ ኢቅባል ዕይታ «በምስራቁ ልቦና እና በምዕራቡ ህሊና ነው፡፡»[20] የሚል ከሆነ ያለምንም ጥርጥር ድራዝ በልዩ ሁኔታ ሁለቱንም ሰብስበው ይዘዋል፡፡ በገዛሊ፣ በሐኪም፣ቲርሚዚና አቢ ጧሊብ አል-መኪ መንፈሳዊነት የተዋቡ፣ በዴካርት፣ ካንት እና በሮዶሰን ፍልስፍናም የታመቁ ነበሩ፡፡

ድራዝ ከቁርአን በተማሩት ምጡቅ አገላለፅ ተመርኩዘው ደርዝን በጠበቀ እሳቤ አድማሳቸው ከፍታ፣ ትንታኔያቸው ጥልቅ፣ መረጃ አቀራረባቸው አርኪና ረቂቅ መሆኑ ልዩ ልሂቅ አድርጓቸዋል፡፡ የምዕራቡ ዕውቀትና ባህል ከቁርአናዊ ወሕይና ከኢስላማዊው ባህል ከመራራቁ እና የዘመናት ድሪቶ ያጠላበት ከመሆኑ ጋር በጥልቀት በመረዳቱ ረገድ የድራዝ ምሳሌ ልክ እንደ ንብ ነው፡፡

---

[19] *ያለፈው ምንጭ*

[20] *Ali shariati, «A manifestation of self-reconstruction and reformation, Muhammad Iqbal,»* [*http://www.shariati.com/english/iqbal.html*](http://www.shariati.com/english/iqbal.html)*.*

ንብ ከሁሉም ዓይነት የተለያየ ጣዕምና ቀለም ካለው ብቃይ ሁሉ ትመገባለች፡፡ በውስጧ ቀምማ ግን ራሷን የመሰለ ጣፋጭ ማር ትሰራለች፡፡

ድራዝ የተደራጀና ይዘቱን የጠበቀ ህሊና ባለቤት ነበሩ፡፡ «ዱስቱሩል አኽላቅ ፊል ቁርአን» በተሰኘው ወሳኝ መፅሐፋቸው ውስጥ በምስራቅና ምዕራብ ድርሳናት መሃል ያሉ የግዳጅ፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት፣ ምንዳ፣ ትጋት እና ተነሳሽነትን የመሳሰሉ የላቁ የስነ-ምግባር እሳቤዎችን ዳስሰው በዳበረ ህሊናቸው ያጣሯቸዋል፡፡ ቀጥለውም ከመሃላቸው ወደ የትም ባላዘነበለ፣ ስር ሰደድና ከባህር የሰፋ ዕውቀትን የሚያሳይ ፍትሐዊ ዕይታ ይዘው ይወጣሉ፡፡

ይህን የአፃፃፍ ዘዴ «አድ-ዲን» በተሰኘውና መሰል የንፅፅር መንፈስን ባዘሉ ድርሳኖቻቸው ላይ ተከትለውታል፡፡ ድራዝ በአውሮፓ እምብርት የኖሩት አረመኔያዊ ስርዓት በሰው ልጅ ስልጣኔ ላይ መጥፎ ጥርጣሬ ይኖራቸው ዘንድ፣ ወይም ደግሞ የምዕራቡን ባህልና አበርክቶ በሚገመግሙበት ጊዜ ሚዛን ወደመሳት አልገፋቸውም፡፡

ልጃቸው ዶክተር ሙሕሲን እንደሚሉት «በሰው ልጅ ፖለቲካዊ እብደት፣ ግዛትና በምዕራቡ ስልጣኔ አዕማዶች መሃል አዕምሯቸው ወደ መደባለቅ አልጠራቸውም፡፡»[21] ይላሉ፡፡

ይህ የድራዝ ህሊና የምጡቅነት ነፀብራቅና የብያኔያቸውን ሚዛናዊነት አመላካች ነው፡፡

---

[21] አህመድ ፈዲላ « ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፡ ዲራሳት ወ ቡሑስ ቢአቅላሚ ተላሚዘቲሂ ወ ሙዐሲሪሂ

በእውነቱ ከሆነ ድራዝ የዕውቀት ናፋቂና አፍቃሪ ሰው ነበሩ፡፡ በሰው አገርና በአስጨናቂ የጦርነት ድባብ ውስጥ የዕውቀት ጥግ ለመድረስ ሲሉ ታግሰዋል፡፡ በእጃቸው ያለ ውድ ንብረታቸው ለዶክትሬት ዲግሪ የመመረቂያ ፅሁፍ ረቂቃቸው ሆኖ ብዙ ቆይተዋል፡፡ ልጃቸው ዶክተር ሙሕሲን እንደሚተርኩት በፈረንሳይ ዋና ከተማ ፓሪስ ላይ የፍንዳታ ጥቃት ማስጠንቀቂያ በተሰማ ቁጥር ድራዝ በብብት እቅፋቸው መሃል ለወደፊት የሚያቀርቡትን የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ወፍራም በእጅ የተፃፈ ረቂቅ ፋይላቸውን እቅፍ አድርገው ሲደብቁ ይታዩ ነበር፡፡»[22] ይላሉ፡፡ ለዚህ ጥንቃቄ ታዲያ ዛሬ ምን ያህል እኛ ባለዕዳዎች ነን ! እነዚያን በዱስቱሩል-አኽላቅ ፊል ቁርአን በተሰኘ ድርሳናቸው ውስጥ ያሉ የቁርአን ልዩ የጥሞና እሳቤዎች ገና በረቂቅ ደረጃ ሳሉ የጦርነቱ ባሩድ ሰለባ ቢሆኑ ኖሮ ላናገኛቸው በከሰርን ነበር፡፡

ከድራዝ ወሳኝ የስብዕናቸው መገለጫዎች ውስጥና የዕውቀት እንዲሁም የተግባር ውርሳቸው ምንጭ ለቁርአን የነበራቸው ልዩ ፍቅር ነው፡፡ ድራዝ በእውነቱ የቁርአን ከሪም ፍቅር ልባቸውን የተቆጣጠራቸው፣ በፍቅሩም ያብከነከናቸው የቁርአን ሰው ነበሩ፡፡ የአላህ መፅሐፍ ከምንም ነገር የሚያቅባቸው ውድ ነገር፣ ሲያነቡት ወይም አቀርቅረው ሲያስተነትኑት አሊያ ቆመው ሲሰግዱበት አንጂ አይታዩም ነበር፡፡ ድራዝ በየቀኑ ያለምንም ድካምና መሰላቸት በትጋት ስድስት ጁዝእ ቁርአን ያነቡ ነበር፡፡ ቁርአንን ሲበዛ ያልቃሉ፡፡ የቁርአን ተፍሲር እያስተማሩ ሱጁደ-ቲላዋ ሲያጋጥማቸው ትምህርቱን ቆም አድርገው ሱጁድ ይወርዱ ነበር፡፡

[22] አህመድ ፈዲላ « ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፡ ዲራሳት ወ ቡሑስ ቢአቅላሚ ተላሚዘቲሂ ወ ሙዐሲሪሂ

ተማሪዎቻቸውን ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት ውዱእ ያስደርጋሉ፡፡ ወደ ህንድ ላሆር ለኢስላማዊ ኮንፈረንስ ለመጨረሻ ጊዜ የጉዞ ባልደረባቸው የነበሩት ሸይኽ ሙሐመድ አቡ ዘህራ ስለርሳቸው እንዲህ ፅፈዋል ፡-‹‹የዒሻን ሶላት ኢማም ሆነው ያሰግዱንና ሁላችንም ወደ ፍራሻችን ለመተኛት ስንሄድ እርሳቸው ግን ወደ ሶላትና ቁርአናቸው ያቀናሉ፡፡ ቁርአን ሲቀሩ ወይም ሲሰግዱበት እንጂ አታያቸውም››[23] ይላሉ፡፡

ተማሪያቸው ሸይኽ ዩሱፍ አል-ቀረዷዊ ስለርሳቸው ሲፅፉ ‹‹ሸይኻችን ድራዝ ረባኒ (ወደ አላህ ለመቃረብ ትጉ) እና በውዴታውም ግንኙነትን የቀጠሉ ልሂቅ (ዓሊም) ነበሩ፡፡ ወደቤታቸው ስንሄድ ቁርአንን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲቀሩ እናገኛቸዋለን፡፡ ጊዜያቸው በሙሉ አላህን በማውሳት (ዚክር) የተዋበ ወይም መልካም ተግባር በመፈፀም አሊያ ዕውቀትን በማገልገል የተጣበበ ነው፡፡››[24] ይላሉ፡፡

የዕውቀትና ጥናት ራዕያቸውን በሙሉ በቁርአን ላይ ብቻ ገድበውታል፡፡ ምሁራዊ ስራ ካበረከቱ እንኳ መሽከርከሪያውና አስኳሉ ቁርአን ነው፡፡ ድራዝ ለአላህ መፅሐፍ የነበራቸው ፍቅር ራሱ በርሱም የልባቸው መንጠልጠል አብሯቸው ኖሯል፡፡

የቀርአንን ሐረጎች ልክ ልቡ እንደጠፋ አፍቃሪ ክትትልን ይከታተሏቸዋል፡፡ ‹‹የዕውቀት ፍሬዎች››[25] በማለትም ይገልጿቸዋል፡፡

---

[23] ሸይኽ ዐብደላህ አል አንሷሪ ኹሉቁል ቁርአን ለተሰኘው የድራዝ መፅሐፍ ከፃፉት መቅድም የተወሰደ፡፡

[24] አህመድ ፈዲላ ‹‹ ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፡ ዲራሳት ወ ቡሑስ ቢአቅላሚ ተላሚዘቲሂ ወ ሙዐሲሪሂ

[25] ድራዝ ይህን አገላለፅ የተጠቀሙት ‹‹ነዞራት ፊ ፋቲሐቲል ኪታቢል ሐኪም›› በተሰኘ ርዕስ በአህመድ ፈዲላ ጥንቅር ውስጥ ነው

**የአፃፃፋቸው ዘይቤ**

የድራዝ የአፃፃፍ ዘይቤ በጥልቀቱና እውነተኝነቱ፣ ለመረዳት በጣም ቀላልና ቅርብ፤ ያማረ ስብጥር ያለው፣ የቃላት ወይም ሐረጎች ውስብስብነት የሌለበት እና ከግንዛቤ እንግድነት የራቀ ነው፡፡ ሁሌም በአላህ መፅሐፍ ላይ ሙጥኝ ማለታቸው የፈካ መንፈስንና አንፀባራቂ ነፍስን አውርሷቸዋል፡፡ የመፅሐፋቸው ንቁ አንባቢ ይህን በቀላሉ ይረዳል፡፡

ዶክተር ዐብዱሰታር ፈትሑላህ ሰዒድ ይህን የመንፈስ ምጥቀት በዶክተር ድራዝና ኢማም ሐሰን አል-በና መሃል አቆራኝተው በተለይ የከዋክብቱን ንግግር አስመልክተው ይህን ይላሉ ፡- «ልቦናዬና ህሊናዬ ውስጥ የሚደባለቁ የመንፈስ ብርሃናማ ሞገዶች ናቸው፡፡ ወደ ላዕላይ ዓለም ከፍ አድራጊ አስደሳች መንፈሳዊ ምትንም ይሰጣሉ፡፡»

ለዚህ ትርጉም ሲሰጡት ደግሞ «አላህ (ሱወ) ሁለቱን ሸይኾች የመጠቀ የመንፈስ ብርታትን፣ የአላህን ፍቅርና ለርሱም መመንኮስን ችሯቸዋል፡፡» ምክንያቱ ደግሞ ተፅዕኖ አሳዳሪነታቸው ቅርፁን የወሰደው ከውስጣቸው ከነበረ የመንፈስ ፍካት፣ የነፍስ ልዝብነትና የልቦና ልምላሜ ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህ ነው ተፅዕኖዎቻቸው ወደ መንፈስና ልቦና በቀላሉ ኮለል ብለውና ሰርገው የሚገቡት፡፡»[26]

ለድራዝ ጠንከር ያለ የአፃፃፍን ዘይቤ ያወረሳቸው ከቁርአን ጋር ያላቸው የዘወትር የአስተንትኖት ቁርኝት ይመስላል፡፡ አንድ አንባቢ በንግግርና ፅሁፍ ፍንጭታቸው ውስጥ የቁርአንን ቃላትና ሐረጎች ልክ እንደ ሉል

---

[26] አህመድ ፈዷላ « ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፡ ዷራሳት ወ ቡሑስ ቢአቅላሚ ተላሚዘቲሂ ወ ሙዐሲሪሂ

ተበትነው ያገኛቸዋል፡፡ አንባቢው ታዲያ በፅሁፋቸውና ብዕራቸው ውስጥ የአላህን መፅሐፍ የሚተነፍሱ ነው የሚመስለው፡፡ ዘይቤያቸውን በልዩ ቁርአናዊ ስልት ቃኝተውታል፡፡ ይህን አገላለፅ ይበልጥ ለመረዳት የተወሰኑ ምሳሌዎችን አንመልከት፡-

- የራዕዩ አምጪና ተቀባዩ ምሳሌ ታዲያ፡- ይህኛው የተገራ፣ ታዛዥና የዕውቀት ማኖሪያነትን የሚቀበል የነፃ መንፈስ ባለቤት ሲሆን፤ ያኛው መላኢካ ደግሞ *ኃይሎቹ ብርቱው(መልዓክ) የዕውቀት ባለቤት የሆነው*[27]...ነው

- *አላህ ፀሐይን ከምስራቅ ያመጣታል፣ ከምዕራብ በኩል ማን ያመጣታል? ሰዎች ከፊሉ የከፊሉ ረዳት ቢሆኑ አንኳ* ያለ ጊዜዋ ሊያመጧት ይችለላሉን?[28]

- ‹‹ቁርአን የእስራኤል ልጆችን ለመጣራት የተጓዛቸውን አራት እርከኖች ተመልከት....ከነዚህ እርከኖች ውስጥ ሁለት የተለያዩ ጉዳዮችን ለማሳካት የተጠቀመውን በመጨረሻው እርከን ላይ *ዓይንህንም መልስ...* ሁለት እሳቤዎችን *በእርግጥ በተወሰነ ኹኔታ ላይ ተገናኙ፡፡* [29]

- ‹‹አንድ ሰው *ባላካበበው ዕውቀትና ትርጉሙ ባልመጣው* ማስዋሸት፣ *በዕውቀት የጠለቁት* የማይፈፅሙት ስህተት ነው፡፡ ትንሽ ዕውቀት ቀመሶችና ከብዙሃኑ ጉረኞቹ የሚወድቁበት ነው[30]፡፡

- *‹‹ከቅርቢቱ ሕይወት ዕውቀት* ትንሽን የተሰጡቱ አላዋቂያን *ሁሉንም ነገር በዕውቀት ያካበቡ* አድርገው ራሳቸውን ያስባሉ[31]፡፡››

---

[27] ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፣ ‹‹አን-ነበኡል ዐዚም ነዞራቱን ጀዲደቱን ፊል ቁርአን››

[28] ያለፈው ምንጭ

[29] ያለፈው ምንጭ

[30] ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፣ ‹‹አድ-ዲን፡ ቡሑስ መማሃዳ ሊዲራሰቲ ታሪኸል አድያን

[31] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም

- ***ምሳሌያቸው ልክ*** *መሬት ላይ እንደ ወንዞች ምንጭ መለያየት ሲሆን፣ የሁሉም መመለሻ ወደ አንድ ምንጭ መሆኑ ያለመታወሱ ብጤ ነው፡፡ እርሱም* ***አላህ ከሰማይ ውሃን እንዳወረደና በምድርም ውስጥ ምንጮች አድርጎ እንዳስገባው*** *ነው*[32]፡፡

መሰል የቁርአንን ሐረጋትና ቃላት አጠቃቀም ቅኝታቸውን በድራዝ መፅሐፍት ውስጥ ቆጥሮ መዝለቅ ይከብዳል፡፡ ሌላው ቀርቶ ከፈረንሳይኛ የተተረጎሙት «ዱስቱሩል አኽላቅ» እና «መድኸል አለል ቁርአን» የተሰኙት መፅሐፍት ተርጓሚዎቻቸው በድራዝ ቁርአናዊ ዘይቤ ተመስጠውባቸዋል፡፡ አልፎ አልፎም በርሳቸው ሰበብ የትርጉም ስራቸው የጎመራ ሆኖላቸዋል፡፡[33]

በእውነቱ አንዋር ጁንዲ የተሰኙት ምሁር እንዳጤኑት ከሆነ ድራዝ በአፃፃፍ ቅኝታቸው በኢስላማዊው ዘርፍ እና አዝሃር ውስጥ መሰላቸው በቁጥር እጅግ ትንሽ ነው ይላሉ፡፡ በተለይ የአገላለፆቻቸው ሞገድ በትርጉምም ይሁን ትስስር ረገድ፣ የተብራራ ይዘቱ ልቦናንም ህሊናንም በአንድ ላይ ያረካል፡፡

የድራዝ የዐረብኛ ቋንቋ አጠቃቀም ለስላሳና አብሪ መሆኑ የተለየ የልምላሜ ሐሴት ያለው ሲሆን በውስጡ የኡሱሊዮች አስተውሎትና የጸሓፊያን ግልፅነትን አጠቃሏል፡፡ ይህ ጉዳይ በፈረንሳይኛ ቋንቋ አጠቃቀማቸውና ዘይቤያቸውም ሳይቀር የተስተዋለ ነው፡፡ አንዋር ጁንዲ የድራዝን አፃፃፍ አስመልክቶ «በኢስላማዊ ጥናቶችና በአዝሃር ውስጥ መሳያቸው እጅግ ያነሰ፣ ሞገድ ያዘለን አገላለፅ ሲቋጩ ወይም ጭብጥን

---

32 ድራዝ አድ-ዲን

33 ያለፈው ምንጭ

ሲፈጥሩ የተለዩ ናቸው፡፡ በአገላለፅ ምስጢር ውስጥ ልብንም ህሊናንም አርኪ የሆነ ጥበብ አላቸው፡፡» ይላል[34]

በዚህ ችሎታ ደረጃ እና የቋንቋ ፍሰት የሚፅፍ ፀሃፊ ማግኘት አዳጋች ነው፡፡ የመድኸል አለል-ቁርአኒል ከሪም ተርጓሚ የነበረው ሙሐመድ ዐብዱል ዐዚም አንዳጤነው ከሆነ ድራዝ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ዘያቸውና የአፃፃፍ ዘይቤያቸው የመጀመሪያ መደብ ላይ የደረሱ፣ የፈረንሳይኛ ቋንቋ አጠቃቀማቸው ምጡቅና ተስማሚ፣ ውብ አጣጣልና ሐሳብን በግልፅ የማውጣት ደረጃ ላይ የደረሰ፣ የሐረግና ቃላት አመራረጣቸው የረቀቀ ነው፡፡[35]» ይላል፡፡

## የስራዎቻቸው ዝርዝር

ዶክተር ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ ከሌሎች አንፃር ሲታዩ በአስተሳሰብ ስራዎች ላይ ብዙ መፅሐፍትን የፃፉ ሰው ሆነው አይደለም፡፡ ነገርግን በቁርአንና በኢስላማዊ እሳቤ የፃፏቸው ድርሳናት ልቀትና ስፋታቸው ዛሬ ድረስ ለኛ እጅግ ያሹናል፡፡ የድራዝን ስራዎች እንደሚከተለው አጠር ባለ መልኩ እንዘረዝራለን፡፡

1. ‹ዱስቱሩል አኽላቅ ፊል ቁርአን› ዲራሰቱን ሙቃረነቱን ሊል-አኽላቂ አን-ነዞሪየቲ ፊል -ቁርአን

- ወደ ዐረብኛ የተረጎሙት፣ በጥልቅ የመረመሩትና ግርጌ ማስታወሻ የሰሩለት ዶክተር ዐብዱሶቡር ሻሂን ናቸው፡፡ የፅሁፉ መነሻ ድራዝ ከሰርቦን ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት መመረቂያ ፅሁፋቸው መሆኑ ነው፡፡ 1950[36] ካይሮ ውስጥ ዳረል መዓሪፍ የተሰኘ ህትመት ቤት ፈረንሳይኛውን አስራጭቶታል፡፡

---

[34] አህመድ ፊዲላ « ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፡ ዲራሳት ወ ቡሑስ ቢአቅላሚ ተላሚዘቲሂ ወ ሙዐሲሪሂ

[35] ያለፈው ምንጭ

[36] Muhammed Abdallah Draz, *La Morale du Koran: etude compare de la (cairo)*

በዐረብኛ ደግሞ ኩዌይት ውስጥ ዳረል ቡሑስ አል-ዒልሚያ በ1973 አሳትሞ አሰራጭቶታል፡፡ ቤይሩት ደግሞ ሪሳላ ኢንስቲቲዩት በ1987 እና 1991 ድጋሚ አሰራጨው፡፡ ከ I.B Tauris ተቋም ደግሞ ‹የቁርአን ስነ-ምግባር ዓለም›[37] በሚል የእንግሊዝኛው ትርጉም የተሰራ ሲሆን ጊዜውም 2001 ነበር፡፡

2. ‹መድኸል አለል ቁርአኒል ከሪም› በሕሱን ታሪኺዩን፣ ወተሕሊሉን ሙቃረን

- በሰርቦን ዩኒቨርሲቲ የማስተርስ ቴሲሳቸው ነበር፡፡ 1949[38] ግብፅ ውስጥ በዳረል መዓሪፍ ህትመት በኩል በፈረንሳይኛ ወጥቶ ነበር፡፡ 1951[39] ዳግም ፓሪስ ውስጥ በፈረንሳይ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ በኩል ወጣ፡፡ ወደ ዐረብኛ በተረጎሙት ሙሐመድ ዐብዱል ዐዚም[40] በኩል የፈረንሳይኛው ማጠቃለያ በ1997 ተሰርቶለት በዳረል ፈላህ በኩል ታትሟል፡፡ የእንግሊዝኛው ትርጉም በ I.B Tauris[41] ተቋም በኩል ለንደን ውስጥ 2001 ወጥቷል፡፡

3. ‹አን-ነበኡል ዐዚም› ነዞራቱን ጀዲደቱን ፊል ቁርአን›› ድራዝ ፅሁፉን ያጠናቀቁት በ1957 ነው፡፡

- በትንሹ ከ13 ጊዜ በላይ የታተመ ሲሆን ግብፅ ውስጥ ሰዐዳ ማተሚያ 1960 እና 1969፣ ኩዌይት ዳረል ቀለም 1970፣ 1977፣ 1996፣ ኳታር ዳረ-ሰቃፋ 1985፣ሪያድ ዳረ-ጦይባ 1996፣አሌክሳንደሪያ ዳረ-ጠይቢን 1997 ተሰራጭቷል፡፡ በዐዲል ሶለሒ ተርጓሚነት 2007 ለንደን ውስጥ የእንግሊዝኛ ስራም ወጥቶለታል፡፡[42]

4. ‹‹አድ-ዲን ቡሑሱን ሙመሀደቱን ሊዲራሰቲ ታሪኸል አድያን››

---

[37] Muhammed Abdallah Draz, *The Moral World of the Quran* (London)

[38] Muhammed Abdallah Draz, *Initiation au Koran. Exposehistorique analytique et comparatif (cairo: Ed. Al- Maaref,1949)*

[39] M. A Draz, Initiation au Koran (paris: presses universitaires de France ( 1951)

[40] Dr. Mohammed Abdullah Draz, *Initiation au Koran, resume par Mohammed Abdel Azim Aly (El-Falah,1997)*

[41] Muhammed Abdallah Draz, *Introdauction to the Quran(London: I.B. (41) Tauris, 2001)*

[42] Muhammed Abdallah Draz, *The Quran An external Challenge(London) Islamic Foundation*

- በፉአድ አል- አወል ዩኒቨርሲቲ ስለ እምነቶች ታሪክ ያቀረቧቸው ገለፃዎች ስብስብ ነው፡፡ 1952 መክተበቱል ዓለሚያ ግብፅ ውስጥ፣ ዳረል-ቀለም ኩዌይት ውስጥ በ1970 እና 2003፣አሌክሳንደሪያ ውስጥ 1990 አሰራጭተውታል፡፡ ፓሪስ ውስጥ በዳረል በራቅ ማተሚያ ቤት ደግሞ 1999[43] የፈረንሳይኛው ትርጉም ወጥቷል፡፡

5. «አል-ሚዛን በይነ ሱነቲ ወል ቢድዓቲ»

- የድራዝ ፍላጎት ይህ መፅሐፋቸው የኢማሙ አሽ-ሻጢቢ «ኢዕቲሷም» ኪታብ ቀጣይ ክፍል ይሆን ዘንድ ነበር፡፡ 1934 ለተማሪዎቻቸው ገለፃ አድርገውበታል፡፡ ነገርግን መቋጫ የሚያደርጉበት ጊዜ ያጡለት ይመስላል፡፡ 2003[44] ዳረል-ቀለም ግብፅ ውስጥ በሸይኽ አሕመድ ፈዲላ አራሚነት ተሰራጭቷል፡፡

6. «አል-ሙኽታሩ ሚን ኩኑዚ ሱና»

- ከድራዝ የፅሁፍ ስራዎች ቀደምቱ ሲሆን መነሻው አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ሐዲስን በተመለከተ ለኡሱለ ዲን ፋካልቲ ተማሪዎች ያቀረቡት ገለፃ ነው፡፡ [45]

7. «ሚን ኹሉቂል ቁርአን»

- የካይሮ ራዲዮ ካሰራጨው የርሳቸው ንግግሮች የተሰበሰበ ፅሁፍ ነው፡፡ ሸይኽ ዐብደላህ አል-አንሷሪ ሰብስበውና ከሽነው አቅርበውታል፡፡ ኳታር ውስጥ የእምነት ጉዳዮች አስተዳደር በ1979 አሳትሞታል፡፡

8. «ወ ሲያበከ ፈጦሂር፡-ወሊባሱ ተቅዋ ዛሊከ ኸይር»

- ከድራዝ «ሚን ኹሉቂል ቁርአን» መፅሐፍ የተሰበዘ በራሪ ፅሁፍ ነው፡፡ 1978 ግብፅ ውስጥ ዳረል አንሷር አሰራጭቶታል፡፡

9. «ፊዲን ወ አኽላቀል ቀውሚያ»

---

[43] Muhammed Abdallah Draz, *Les homes a la decouvertie de Dieu prologue a une histoire des Religions (paris: Editions Al-Bouraq,1999).*

[44] ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፣ «ዛዱል ሙስሊሚ ሊዲኒ ወል ሐያት» ጥንቅር ላይ ከሸይኽ ቀርዷዊ መቅድም የተወሰደ

[45] ኡስታዝ ፈዲላ ሐሷዱል ቀለም ለተሰኘው መፅሐፋቸው የሰጡትን መቅድም ተመልከት

- የሬዲዮ ፕሮግራም ሲሆን ግብፅ ዳረል ካቲብ አል-ዐረቢ 1967 አሳትሞታል፡፡ ፀረ-እስራኤል ትግልን አነሳሽና አበረታች ይዘት በውስጡ ስለነበረው በዕብራዊ ቋንቋም ተተርጉሞ ወጥቷል፡፡

10. «ሐሷዱል ቀለም...መቃላት ወ ቡሑስ ሊሸይኽ ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ»

- ቁጥራቸው 66 የሚሆኑ የድራዝ የምርምር ስራዎችን ያካተተ፣ ከአጫጭር ፅሁፍ እስከ ረዣዥም ፅሁፎችን የያዘ ድርሳን ነው፡፡ 2004 ዳረል-ቀለም ህትመት አሰራጭቶታል፡፡

11. «አስ-ሶውሙ ተርቢየቱን-ወ-ጂሐድ»

- 1958 እና 1980 በዳረል ቀለም ታትሟል፡፡

12. «ዲራሰቱን ኢስላሚያ ፊል ዐላቃቲ ደውሊያ ወል-ኢጅቲማዒያ»

- ይህ መፅሐፍ ከሰባት የጥናት ስራዎችና ሁለት ኮንፈረንሶች ላይ ካቀረቡት ወረቀት የተጠናቀረ ነው፡፡

13. «ዛዱል ሙስሊሚ ሊዲኒ ወል ሐያቲ»

- ድራዝ በሬዲዮ ያቀረቧቸውን 64 ንግግሮች ያካተተ ነው፡፡ ኡስታዝ አሕመድ ፊዲላ ሰብስበውና አጠናቅረው ያዘጋጁት ሲሆን ዳረል-ቀለም በ2008 አሰራጭቶታል፡፡

-

14. «ነዞራቱን ፊል ኢስላም»

- በ1958 መክተቡል ፊኒ ግብፅ ውስጥ፣ 1972 መክተቡል ሁዳ አሌፖ ውስጥ እና 1972 ዳሩል አርቀም ቤይሩት ውስጥ አሰራጭተውታል፡፡ በ1977 ቱርከኛ ትርጉሙ የታተመ ሲሆን ኢስታንቡል ውስጥ Husnuhayat Matbaas አሰራጭቶታል፡፡

15. «አስሉል ኢስላም»

- ድራዝ በፈረንሳይኛ የፃፉት ሲሆን ፓሪስ ውስጥ ሙአሰሰቱ ሪሳላ በፈረንሳይኛ 2006[46] ላይ አሰራጭቶታል፡፡ 1958 በከፊል ወደ እንግሊዝኛ በክኔስ ሞርጋን ተተርጉሞም ተሰራጭቷል፡፡[47]

---

[46] M. A Draz, *Naissance de lislam: Mohammed peut – il etre lauteur du coran (paris: Arrisala,2006)*

[47] ድራዝ፣ ዲራሳት ኢስላሚያ ፊል ዓላቃት አድ-ደውሊያ ወል ኢጅቲማዒያ 48-77

16. «አውራቁ ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ»

- ድራዝ ገና ወጣት ሳሉ ከ1919 እስከ 1921 ድረስ ባለው ጊዜ ያሰራጪቸው አርቲክሎች ናቸው፡፡

የሆነ ሆኖ የድራዝ ስራዎችን በጥልቀት ላላገኘና ላላነበበ አዲስ አንባቢያቸው የምናሳስበው የርሳቸው እሳቤ መቅኒው በአራት መፅሐፍት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነርሱም

1. ዱስቱሩል አኽላቅ ፊል ቁርአን
2. አድ-ዲን
3. አን-ነበኡል ዐዚም እና
4. መድኸል አለል ቁርአኒል ከሪም ናቸው፡፡

በነዚህ ምሁራዊ ስራዎች ላይ ድራዝ መንፈሳቸውንም፣ ህሊናቸውንም ጨምቀው አፍስሰውባቸዋል፡፡ በዘርፉም ከበቂ በላይ ምንጭ ናቸው፡፡ ሌሎቹ የድራዝ ስራዎች ከነዚህ 4 ስራዎች ውስጥ ውልድ የሆኑና በውስጣቸው ካሉ የላቁ እሳቤዎች ጋር ተቀራራቢ ናቸው፡፡

በተጨማሪም«ሙኽታራት ሚን ኩኑዚ ሱና» እና «አል-ሚዛን በይነ ሱነቲ ወል ቢድዓቲ» ሲቀሩ ሌሎቹ አርቲክሎችና ህዝባዊ ገለፃዎች ስለሆኑ ርዕሶቻቸውን የሰጡት የሰበሰቧቸውና ያሰናዷቸው ሰዎች ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

# በድራዝ እሳቤ ውስጥ የሚዛናዊነት ጎልቶ መታያዎች

አላህ (ሱወ) ነብዩ ሙሐመድን (ሰዐወ) የሰው ልጅ ያለግዳጅ ወደ እርሱ ባርነት የከፍታ መንበር የሚያጎነውን፣ ያለድንበር ማለፍ ለርሱ መሰሉ ፍጡር ባሪያ ከመሆን ነፃ የሚያደርገውን፣ ከጥሜት ወደ ቅናቻ ያዘነበለውንና ገር እንዲሁም ሚዛናዊ የሕይወት መመሪያ የሆነውን የኢስላምን መንገድ አስይዞ ልኳቸዋል፡፡

ወሰጢያ (ሚዛናዊነት) ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብዙዎች ዘንድ ከእውነተኛ እኔነትም ይሁን ከባዶ ነኝነት ተነስተው በዙሪያው ጩኸት ያበዙበት ግንዛቤ ሆኗል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የግንዛቤውን ጥልቀት እና በወቅታዊ የዕውቀት ባህላችን ውስጥም መንገሱን ነው፡፡ በተመሳሳይ ግን ለአዕምሮ ያልተብራራና የስርፀት እጦትም እንዳለበት አመላካች ነው፡፡

### የወሰጢያ ትርጉም

ይህን ክፍል የምንጀምረው የኢስላም ማዕከላዊነት ማለት ምን እንደሆነ በመተርጎም ሲሆን አንባቢ ይህን ቃል እዚህ ውስጥ ስንጠቀመው ምን እንዳሰብን ግልፅ ይሆንለት ዘንድ ነው፡፡

ወሰጢያ (ሚዛናዊነት፣ ማዕከላዊነት) ማለት፡- «እውነትን በመቀደስ እና ለፍጡር በማዘን መሃል የሰበሰበ የእሳቤና ገቢር አቋም ሲሆን፤ ባለቤቱ ከላይ የወረደን ወሕይ የሰውን ልጅ የአረዳድ አንፃራዊነት የሚያውቅበት

በጊዜ ሂደት የሚገነባ አቋም ነው፡፡ አዕምሮንና መለኮታዊ ድርሳናትን በመያዝ፣ ሁሉም ሰው ያለውን መልካም ነገር በመውሰድ ከተቃዋሚ ጋር በንፁህ ልቦና መኗኗር ያስችለዋል፡፡»

የወሰጢያን ግንዛቤ ለሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡-

1) በድፍኑ መጠንቀቅ እና

2) አስፍቶ መረዳት ናቸው፡፡

የወሰጢያ ዋና ፅንሰ-ሐሳቡ ኢስላምን በመገንዘቡና በመተግበሩ ሂደት ከአሐዳዊነት እና ጸጉር ስንጠቃ መራቅ ነው፡፡ በተጨማሪም ከሁሉም አካል አዎንታዊ ጎኑን እየወሰዱ አሉታዊውን ክፍል መተውና መጠንቀቅ ነው፡፡ ሚዛናዊ የሆነን ስብዕና ለዚህ ነው ሁሌም በአስተሳሰብ ትምህርት ቤቶች መሃል በሚነሳ አለመግባባት ላይ ልቅ የሆነ ስሜታዊ ብያኔን ከመስጠት ይልቅ መካከል ላይ የምታገኘው፡፡

የኢስላምን ማዕከላዊነት እሳቤ በሚገባና በመጠቀ ሁኔታ ከገለፁ ልሂቃን መካከል ከቀደምቱ አል-ሐፊዝ ጀማሉዲን ዐብዱራህማን ቢን አል-ጀውዚን እና በዘመናችን ደግሞ ዶክተር ዩሱፍ አል-ቀረዷዊን አግኝቻለሁ፡፡

ኢብኑል ጀውዚ የወሰጢያን እሳቤ በድፍኑ የመጠንቀቁን መስመር ተከትለው ከገለፁት ውስጥ ናቸው፡፡ በኢስላማዊው የዕውቀት ባህል ውስጥ ከስድስት ጥልቅ የመንገድ መዛባቶች አስጠንቅቀዋል ፡-«የሐሳብ ግትርነትን፣ የተናጋሪዎችን ልቅነት፣ ዛሂድ ነን ከሚሉት ቂልነት፣ ስሜታቸውን ከሚከተሉ ሰዎች ሆዳምነት፣ ያለ ተግባር በዕውቀት ስም

ከተሰየሙ ዐሊሞች እና ያለ ዕውቀት ከሚሰሩ ባህታውያን ተጠንቀቅ፡፡»[48] ይላሉ፡፡

ሸይኽ አል-ቀረዷዊ ደግሞ ማዕከላዊነትን የመሰረቱት የተለያዩ ጫፎችን ሰብስበው በአስፍቶ የመረዳት መስመርን ተከትለው ነው፡፡ እንዲህም ይላሉ ፡-«በተለያዩ ድርሳኖቻችን ውስጥ ያሉ ጠቃሚ የሆኑ ምርጥ ንድፎችን መጠቀም ይኖርብናል፡፡ የሕግ ባለሙያዎቻችንን (የፊቂሆችን) ቅንብር፣ የኡሱሊዮችን ስር መሰረት ማስያዝ፣ የሙሐዲሶችን ሒፍዝ፣ የፈላስፎችን ምክንያታዊነት፣ የሱፊዮችን መንፈሳዊነት፣ የታሪክ ሰዎችን ዘገባ፣ የፀሐፊያንን ረቂቅነት፣ የባለቅኔዎችንና ገጣሚዎችን ስርገት፣ የጠቢባንን ማሰላሰል እና የሳይንቲስቶችን ሙከራዎች ሁሉ በአንድ ላይ መጠቀም ነው፡፡»[49] ይላሉ፡፡

እርምጃዎቻቸውንና ፋናዎቻቸውን የተከተለ ሰው እንደሚያጤነው ከሆነ ዶክተር ሙሐመድ ዐብደላህ ዲራዝን ከወሰጢያ ኢስላሚያ ኢማሞች አንዱ ሆነው ያገኛቸዋል፡፡ እሳቤዎችን ከሁሉም እምነቶች፣ ምንጮችና የእሳቤ መስመሮች የሚያሰናስሉ፤ በቁርአናዊ ማጣሪያ የሚያፀዱትና ንፁህ የኢስላምን የአበባ ማር የሚያነጥሩ የሰፋ ዕውቀት አድማስ ባለቤት ንብ ነበሩ፡፡

ድራዝ በዋና ስራቸውና ታዋቂ በሆነው መፅሐፋቸው (ዱስቱሩል- አኽላቅ ፊል ቁርአን) ውስጥ ስለ ዕውቀት ባህል ስብጥራቸው እንዲህ ይገለፃሉ፡- ‹በዚህ ድርሳን ውስጥ በፅሁፍ መልክ ያለው ስራችን የምስራቁ የስነ-ምግባር እሳቤ ከቢጤው ምዕራቡ ጋር በንቃት በታሸ ገለልተኛ ንፅፅር

[48] ኢብኑል ጀውዚ፣ ሶይዱል ኻጥር ገፅ 123

[49] ዩሱፍ አል-ቀረዷዊ፣ ከሊማት ፊል ወሰጢየቲል ኢስላሚየቲ ወ መዓሊማሃ ገፅ 56

የሚገናኙበት የመስክ ዓይነት ነው፡፡ ካለፈ እሳቤ የፀዳ፣ ለአንድ የአስተሳሰብ ትምህርት ቤት ብቻ ከማድላት የራቀ፣ በሁሉም ውይይቶቹ ውስጥ ወሳኝና ፈራጁ እንዲሆን የሚጋብዘው ህሊናን ሲሆን፤ ወደ አስተማማኝ ሰነድ መውሰዱም ነው፡፡»[50]ይላሉ፡፡

ቀጠል አድርገው ለሰብዓውያን ይህን መልዕክት ይናገራሉ ፡-«ከዚህም ከዚያም ልቦናዎች ወደ ሰብዓዊነት ሲዘነበሉና ሲያስቡት ለሰው ልጆች አስበው እጆች በመልካም ተሰባስበው ሲተሳሰሩ፤ በተለያዩ ባህሎችና የዕውቀት ዘርፎች መሃል ሊኖር የሚችለውን የመቀራረብ መልካም ጅማሮ መሆኑን ተመልከት!!!»[51] ይላሉ፡፡

የዚህ ጥራዝ ቁመና ሰፋ ላለ ማብራሪያ በቂ ስላልሆነ በጣም በአጠረ ሁኔታ ድራዝ ዘንድ የወሰጢያን ዋና መለያ ፀባያት አጉልተን እናያለን፡፡ በቀደመው ጊዜና በአሁኑ ዘመን ሳይቀር የኢስላማዊውን እሳቤ ሳሎን ወጥረው የያዙ አምስት ሁለትዮሾች አሉ፡፡ እነርሱም

- አዕምሮና እና አንቀፅ (ጥቅስ)
- መገደድ እና ምርጫ
- ሃይማኖት እና ሳይንስ
- ሱና እና ቢድዓ
- ሠላም እና ጦርነት ናቸው፡፡

እነዚህ ጣምራዎች ውስጥ ገብተን ዳሰሳ ከማድረጋችን በፊት ድራዝ ኢስላማዊውን ተልዕኮና ገራገር ባህሪውን በጥልቅ የተረዱበትን ምስጢር በፍጥነት ለማየት እንሞክራለን፡፡

---

[50] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ 18

[51] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 18

## እርከን ጠበቅነት እና ተሻሽሎት

ድራዝ እርከን መጠበቅ፣ በደረጃ ማደግና መሻሻል የኢስላማዊው ተልዕኮ ባህሪያት መሆናቸውን ተገንዝበዋል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ደግሞ ከወሰጢያ መገለጫዎች ጭምርም ናቸው፡፡ ነፍስን በመቀየሩ ሂደት ውስጥ ጥበብን የተላበሰና እርከንን የጠበቀ ስርዓት መከተልን የተጓዘው የኢስላም አካሄድ የተልዕኮውን ትክክለኛ ምንጭና መለኮታዊ ጥበቡን ገላጭ ነው፡፡ ጉዳዩ በእርከን ጠበቅነት እሳቤ ላይ ብቻ የሚቆም ሳይሆን ፤‹‹አንብብ በጌታህ ስም›› ከተባለባት ቀን ጀምሮ ‹‹ዛሬ ኃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ›› የምትለው አንቀፅ እስከወረደቺበት ዕለት ድረስ ያለውን የድንጋጌና ስነ-ምግባር ምሉዕነት የሚጠቀልል ነው፡፡ ድራዝ ቁርአን ውስጥ አስካሪ መጠጥ እርም የተደረገበትን ታዋቂ ምሳሌ ለዚሁ አስረጂ አድርገው ጠቅሰዋል፡፡ ቁርአን ከሪም ነህል 68 ላይ ከኸምር ዓይነት የሆነውን ‹‹ጠጅ››ን ከ‹‹መልካም ሲሳይ››[52] ይዘት ውጪ አድርጎ በማስወጣት ውስጥን በመናጥ ጠቆመ፡፡ ከዚያ በመቀጠል ቁርአን ኸምር በውስጡ ስለያዘው ወንጀል በመጥቀስ ግን ሐራም መሆኑን ሳይገልፅ አስከተለ፡፡

ከጊዜ በኋላ በሶላት ወቅት እርም አደረገው፡፡ በስተመጨረሻም ሙሉ በሙሉ እርም (ሐራም) አድርጎ ዘጋው፡፡ በእያንዳንዱ እርከን መሃል ለአናቅፁ ስነ-ምግባራዊ ትርጓሜና በነፍስ ላይ የሚታይ ቅርፅ ይይዝ ዘንድ በቂ ጊዜ ነበረው፡፡

ኸምርን በተመለከተ የወረዱ አናቅፅ አራት ናቸው፡፡ ‹‹አራተኛዋና የመጨረሻዋ አስካሪ የተባለን መጠቀምና መጠጣት እርም መሆኑን

---

[52] وَمِن ثَمَرَاتِ النَّخِيلِ وَالْأَعْنَابِ تَتَّخِذُونَ مِنْهُ سَكَرًا وَرِزْقًا حَسَنًا
‹‹ከዘምባባዎችና ከወይኖችም ፍሬዎች (እንመግባችኋለን)፡፡ ከእርሱ ጠጅንና መልካም ምግብንም ትሠራላችሁ፡፡››

የጠቀሰች ናት፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሶስቶቹ ግን የአማኞች ነፍስ ይህን እቀባ ይቀበሉ ዘንድ የማመቻቸት እርከኖች ናቸው፡፡» [83]

ቁርአን እዚህ ላይ ውስጥን በማነፅ ማከም በህግ አስገዳጅ በሆነ ኃይል ከማከም በ75 % እንደሚበልጥ ያስተምረናል፡፡ እርሱም ሶስት አናቅፅ ውስጥን ለማናገር ያስቀመጠ ሲሆን አንዱን ግን አቃቢ የሆነች የህግ አንቀፅ አደረጋት፡፡ ድራዝ በዚህ ጥበበኛ እርከን ጠበቅነትና የኸምርን መከራ ለማስወገድ የተኼደበትን የእዝነት መንገድ አስተያየት ይሰጡበታል፡፡

«ይህ ገርና እርከኑን የጠበቀ አካሄድ የተካኑ ሐኪሞች ለዘመናት የቆየን በሽታ ለማከም የሚሄዱበትን መንገድ ሲያሳየን፣ በተጨማሪም በጥቅል ሁኔታው አጥቢ እናቶች ጠቢ የሆኑ ልጆቻቸውን በምን መልኩ ቀስ በቀስ ጡት እንደሚያስጥሉትም ያስታውሰናል፡፡[53] የአላህ ለባሪያዎች የማዘን ሁኔታ የህክምና ጥበብም ይሁን የእናቶች እዝነት አጠገቡ አይደርስም፡፡ ለንፅፅርም የሚቀርቡ ምሳሌዎች በእርግጥ አይደሉም ፡፡»[54]

---

[53] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 83

54 ያለፈው ምንጭ

ድራዝ የኸምርና የአራጣ እርምነት የተከተሉትን እርከንን መጠበቅ አስመልክተው ክፍልፋይ በሆኑ የሸሪዓ ሐዶች ላይ ብቻ ሳይሆን የቆሙት ጉዳዩን በጥልቀትና ሁሉን አቀፍ በሆነ ሁኔታ ነው የዳሰሱት፡፡ በግልፅ እንዳስቀመጡትም «የመካው ዘመነ-እርከን በአጠቃላይ (ነፍሶችን) ለመጪ ድንጋጌዎች የማዘጋጀት ዓይነት ቅርፅ ያለው ነው[55]፡፡» ይላሉ፡፡

ነገርግን እነዚህ ምጥን የገቢር ውሳኔዎችንና አጠቃላይ መርሆቹን (መዲና ውስጥ) በአስር ዓመታት በተለያየ ቅርፅ ተከፋፍለው መጥተዋል፡፡ መካ ውስጥ የነበረው የነፍስና መንፈስን የማዘጋጀቱ እርከን መዲና ውስጥ ወደ ድንጋጌያዊና ስነ-ምግባራዊ እርከንነት ደረጃ ተለውጧል፡፡ ሁለቱም እርከኖች ግን የተልዕኮውን ወደ ምሉዕነት የማደግ ገላጮች ናቸው፡፡

በተጨማሪም ድራዝ «ገርነት» ከወሰጢያ መገለጫዎች እና ከኢስላም ልዩ ባህሪያት መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በተግባር የሚታየውም ደግሞ በልዩ ፈቃዶች (ሩኽሶች) ላይ የአደጋ ጊዜ ህግጋት መኖራቸው ሲሆን ሶላትን ማሳጠር፣ በሽተኛና መንገደኛ የሆነ ሰው ፆምን አዘግይቶ በመፆምና መሰል ደንቦች መገለፁ ነው፡፡ «የቁርአን አዛኝ ድንጋጌ በግልፅ የሚታየው በነዚህ ሁኔታዎች ላይ ሲሆን ለአዲስ ሕይወት ሁኔታዎች ግዴታዎችን መሰደር መከተሉ ነው፡፡ እንደየሁኔታው በሚኖሩ ለውጦች መቀየርም ይሁን ማቅለል ወይም ማዘግየት አሊያ መዝጋት ሊሆን ይችላል፡፡[56]»

ድራዝ በእርከን ጠበቅነት ላይ እንዳጤኑት ከሆነ ሌላው ጉዳይ ዩስር (ገርነት) ባወሳናቸው ምሳሌዎች ውስጥ ብቻ ያለ የድንጋጌ ዓይነት የሚወሰን ሳይሆን፤ በሁሉም የኢስላም ድንጋጌዎች ገላ ውስጥ የሚሽከረከር መንፈስ ነው፡፡

---

[55] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ 86

[56] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 82

«ጉዳዩ ድንገተኛ ጉዳዮች ብቻ ሲከሰቱ ወይም ከችኮላ የመጣ አዲስ ክስተት ሳይሆን በገቢር ለማስገኘቱ የምንጊዜም ጥረት የሚጠይቅና ከግምት የሚገባ አስኳል መርህ ነው፡፡»[57]

## ውህደት እና ሚዛን መጠበቅ

በኢስላማዊ ድንጋጌ ውስጥ ከሚዛናዊነት መገለጫዎች ሌላው ድራዝ እንዳጤኑት ድንበር ማለፍን መታቀብ ነው፡፡ ድንበር አልፈው ወደ ምነና እና ግዴለሽነት በተዘነበሉ ራሳቸውን አድካሚያንና ምናባውያን ላይ በግልፅ እንደሚታወቀው መረር ያለ ቆራጥ ነብያዊ ማስጠንቀቂያ ተደርጎበታል፡፡ ምክንያቱም «የሸሪዓውን መንፈስ የተጣረሰ መዛባት ስለሆነ ነው፡፡[58]» ይላሉ፡፡ አክለውም «ማንኛውም የአምልኮ እንቅስቃሴ የልብን ንቃት የጠበቀና የደስታውን ጊዜ ያማከለ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ አላህን በማምለካችን ውስጥ በልባችን የሚጠላን ነገር ፈፅሞ ማስገባት አይኖርብንም፡፡[59]»

ሸሪዓ ዒባዳን ቀጣይነት ያለው ስራ ይሆን ዘንድ ውስጣዊ የማንነት ይዘት ሁሌም ንቃት ያለውና ህያው እንዲሆን ይሻል፡፡ ኢማሙል ቡኻሪ በሶሒሕ ሐዲስ የስብስብ ጥራዛቸው ውስጥ አንድ «በስራ የመዘውተርና የማሰብ»[60] የሚል የምዕራፍ ክፍል ሰድረዋል፡፡ በተጨማሪም ኢማም ሙስሊም «የዘውታሪ ስራዎች ትሩፋት»[61] የሚል ምዕራፍ በድርሳናቸው ውስጥ አላቸው፡፡ ሁለቱም ይህን ትርጉም የሚያጎሉ ብዙ የሐዲስ ዘገባዎችን የያዙ ሲሆን ከነርሱም ውስጥ «በመልካም ስራዎች ተቻኮሉ፣ (ወደ አላህም) ተቃረቡ፡፡

---

[57] ያለፈው ምንጭ

[58] ያለፈው ምንጭ

[59] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 76

[60] ሙሐመድ ቢን ኢስማዒል አል-ቡኻሪ፣ ሶሒሕ አል-ቡኻሪ 2372/5

[61] ሙስሊም ኢብኑል ሐጃጅ፣ ሶሒሕ ሙስሊም

አንደኛችሁ በሰራው ስራ ጀነት አንደማይገባ እወቁ፡፡ አላህ ዘንድ ተወዳጅ ስራ በጣም ቢያንስም ቀጣይነት ያለው ነው፡፡»[62] የሚለው ይጠቀሳል፡፡

ለዚህ ሲባል ማንኛውም ድንበር ማለፍና መወብራት፣ ድንበር ማሳጠር እና መሃል ላይ መቋረጥ ይከተለዋል፡፡[63]

ልክ እንደዚሁ የሸሪዓን ውብ ገፅታና ምልክቶቹን በጥልቀት በመገንዘብ ቅኝታቸው ድራዝ «ሁሉን አካታችና ዘልዓለማዊ ድንጋጌ ሲሆን፤ ለሰብዓውያን የሚበጇቸውን ተፈጥሯዊ ፍላጎቶች ዋስትና ይሰጣቸዋል፡፡ ነገርግን በግልፅና በአንክሮ ደግሞ አጥፊና አውዳሚ ስሜቶቹንም ይገፋል፡፡[64] ይላሉ፡፡

ድራዝ ቀጥለው የአንድን ሙስሊም ህሊና ወጥረው የያዙ የሁለትዮሽ ፅንፀ-ሐሳቦች (Dual Concepts) በስርዓት ማከም ጀመሩ፡፡ በዚህ ለኢስላም ሸሪዓ ባለ ጥልቅ የእርከን፣ የመሻሻል፣ የመሞላላት፣ ሚዛን የመጠበቅ ግንዛቤ ብርሃንና ገርነት መሰረት ለነዚህ አምስት ጣምራዎች አዲስ የዕይታ ብርሃንን አመጡ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ አጠር ባለ ሁኔታ እንቃኛቸዋለን፡፡

## አዕምሮ እና አንቀፃዊነት (ራዕይን መያዝ)

የአንድን ሙስሊም እሳቤ ዛሬም ድረስ ወጥረው ከያዙ የመጀመሪያዎቹ ጣምራዎች ውስጥ ናቸው፡፡ በሩ ዛሬም ድረስ ክፍትና ያልተዘጋ ሲሆን መፍትሔውም ደግሞ በአዕምሮና አንቀፃዊነት መሃል ያለውን ትስስርና በሁለቱ መሃል አግባብ ያለውን የማሰናሰል መንገድን መገንዘብ ነው፡፡

በነዚህ ጣምራ ፅንሰ-ሐሳቦች ዙሪያ ክርክር ከሙብዛቱ የተነሳ ጩኸትና ስርዓት መጣሱ በዝቷል፡፡ በሙስሊሞች ውስጥ አዕምሮን በድፍኑ ችላ የሚል ቡድን ሲፈጠር በሌላ በኩል ደግሞ «አዕምሮን መጠቀም» ከፊል ዘመናዊ ሰለፊዮች

---

62 ሶሒሕ አል-ቡኻሪ 98/8

63 ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 76

64 ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 16

የዕውቀት ባህል ውስጥ ነውር እስከመሆን ደርሷል፡፡ በንፁህ ፍላጎታቸውም ከአዕምሯቸው ነፃ ሆኑ፡፡

ሌሎች ደግሞ በሰው ልጅ ህሊና እና የአዕምሮ የላቀ ሚና ላይ፣ ባልተገደበና በተጋነነ ችሎታው ላይ ብቻ ሙሉ በሙሉ ተማመኑ፡፡ እነዚህኞቹ የሰውን ልጅ ውስን የዕውቀት መጠን ከወሰን የለሹ መለኮታዊ ዕውቀት ጋር በማነፃፀር እንኳ መረዳት አልቻሉም፡፡ በዘመናችን ያለው ይህ ድንበር መጣስ ካለፈው ዘመን የቀጠለ ነው፡፡ ሙዕተዚላዎች በውጁድ (Existence) ገለፃቸው ውስጥ «ንፁህ የህሊና ስርዓት በብርሃኑ ብቻ በመታገዝና መመራት ወደ ልዑሉ ፈጣሪ ማንነትና መኖር፣ ተግባራቱን ወደሚቆጣጠሩ ስነ-ምግባራዊ ድንጋጌዎች መድረስ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም እኛ ላይ ግዴታ የሆኑ ህግጋትም ላይ መድረስ ቀላል ነው፡፡»[65] ይላሉ፡፡

የሙዕዚላዎች የአስተሳሰብ መስመር አደገኛ ውጤትና ይዘትን ይዞ ነው የሚቋጨው፡፡ እርሱም በንድፈ-ሐሳብ ደረጃ ከሰማይ ተልዕኮ መብቃቃትና፤ በነፍስ ውስጥ በታመቀ ተፈጥሯዊ የልቦና ብርሃን ብቻ በመብቃቃት፣ ግልፅ የሆነውን የወሕይን (ራዕይ) ብርሃን ችላ ማለት ነው፡፡

በነርሱ እሳቤ «አላህ (ሱወ) ባወረዳቸው መፅሐፍት ፍላጎቶቹን ለፍጡራኑ ግልፅ ባያደርግ እንኳ፤ ወደ መልዕክተኞች ትዕዛዛቱን በራዕይ ባያወርድ፣ በእርግጠኝነት እኛ እናውቃቸው፣ ከዚያም መከተሉ ግዴታ ይሆንብን ነበር፡፡ መፅሐፍቱም ይሁኑ መልዕክተኞቹ የአዕምሯችንን የልቦና ዕይታ ከማፅደቅ የዘለለ ሚና የላቸውም፡፡» ብለው ያስባሉ፡፡[66]

ብዙሃኑ የኢስላም ሊቃውንት ለዚህ ለተሰነዘረ ሐሳብ መልስ ሰጥተውበታል፡፡ በጉዳዩም ላይ ከጅምሩ በውስጣችን ካለው የተፈጥሮ ህግ በተጨማሪ

---

[65] ድራዝ፣ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 66

[66] ድራዝ፣ዱስቱሩለ አኽላቅ ገፅ 67

«ለተጠያቂነታችን ምክንያታዊነትና መልስ በግልፅና አዎንታዊ በሆነ መልኩ ከአላህ ዘንድ ድንጋጌ (ሽሪዓ) መምጣቱ ግዴታ ነው፡፡»[67] ይላሉ፡፡

ድራዝ እንዳጤኑት ለሙዕተዚላዎች ድንበር ዘለልነትና ለህሊናዊ ግትርነታቸው መልስ ለመስጠት ያለምንም የዕውቀት ዝግጅትና በቂ የሽሪዓ ግንዛቤ እጅለጅ የገጠሙ ሌሎች ቡድኖችም ድንበር አልፈዋል፡፡

በተመሳሳይ «ይህን ጋጥ ዘለል ግትርነት ድርቅና እና ለሰው ልጅ አዕምሮ ለሰጡት የተጋነነ የመተማመን ግምት ለመቃወም፤ አሽዓሪዎች የሙዕተዚላዎቹን አስተሳሰብ አንድ በአንድ እያነሱ ጣሉት፡፡»[68] የክርክሩ መንፈስ እነርሱን ሳይቀር ሌላ ጠርዝ እስኪይዙ ግን አድርሷቸዋል፡፡

ሆኖም ሙስሊም ነቢባን ሽሪዓና አዕምሮ ከመለኮት ብርሃናዊ ራዕይ ጋር የሚሞላሉ ማጣቀሻዎች መሆናቸውን ያወቁና ወደ እውነት፣ ሰናይና ውብ መንገድ ለምናደርገው ጉዞ መብራታችን መሆናቸውን ተረድተዋል፡፡ በሕይወታችን ትርጉምና መዳረሻ ላይም ውርዛትን ይጨምሩበታል፡፡

አንዱን ከአንዱ ነጥሎ በተቃራኒ ማየቱ የአስተሳሰብ ክፍተትና በአማኝ ማንነት ውስጥ ያለምንም ነጥሎ መተው በጥቅሉ መቀበል ወሳኝ ነው፡፡ በእውነትና ሐሰት መሃል የመለየትን ችሎታ አላህ የሰውን ልጅ ከፈጠረበት አዕማድ አንዱ ክፍል ነው፡፡ ከዚያም መልዕክተኞች ይህን ተፈጥሮ ለማጠንከር፣ ከአጥማሚ አሻሚና ሆሳ ነገሮች ከአብለጭላጭ የስሜት ጥሪዎች ለማፅዳት ተላኩ፡፡

እዚህ ጋር ከወሕይ በራቀ አዕምሮና በወሕይ በሚመራው መሃል የጎላ ልዩነት አለ፡፡ ድራዝ በሶስት ሐሳቦች አጠቃለውታል፡፡

***የመጀመሪያው ልዩነት-*** በወሕይ ብርሃን ያልሸበረቀ አዕምሮ የምሪቱ ግብ እውነታዎችን ለስለስ ባለ መልኩ ማሳወቅ ብቻ ሲሆን፤ እውነታውን መከተል

---

[67] ያለፈው ምንጭ ገፅ 405

[68] ድራዝ፣ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 67

ግን ግጼታ አያደርግም፡፡ ወሕይ ግን እውነታን ከስጋ ወ ደሙ ጋር ያቀርብልንና በውጼታ ላይ በተመረኮዘ መልኩ እንቀበለው ዘንድ ግጼታ ያደርግብናል፡፡

በድራዝ ዕይታ በዲን (እምነት) እና ፍልስፍና መሃል ያለው ልዩነት ፡- ‹‹የፍልስፍና ግቡ ደረቅ ዕውቀት ሲሆን፣ የዲን (እምነት) ግብ ደግሞ ማመን ነው፡፡ ለፍልስፍና የሚያስፈልገው ደረቅ ያለ የማይንቀሳቀስ ቅርፅ ያለው እሳቤ ሲሆን፤ ዲን ደግሞ መስህብ ያለው መንፈስና አንቀሳቃሽ ኃይል ያስፈልገዋል፡፡›› [69]ይላሉ፡፡ የወሕይ ደግሞ ሚናው ለኛ እውነታን በማጉላት ብቻ ሳይሆን ‹‹ስሜትን ኮርኳሪ ሕያው እሳቤነትም››[70] መለወጥም ጭምር ነው፡፡

***ሁለተኛው ልዩነት ደግሞ***- የእምነት (ዲን) እውነታዎችን ተጨባጭ በሆነ መንገድ ከፍልስፍና እውነታዎች መለየትና እርሱም የሚያመጣውን ተፅዕኖ መገንዘብ መቻል ነው፡፡ ዐቂዳ በባህሪው ቸርነትንና ሌሎችን በፀጋ ማትረፍረፍ፣ መሰራጨትና አብሮነትን የሚያበረታታ ሲሆን ተሸካሚ ባለቤቱን ወደ ጥሪና ድል ቀስቃሽ ኃይል ነው፡፡ ፍልስፍና ደግሞ እንደ ማንኛውም የሰው ልጅ ሐብት ወደ መታገት እና ሞኖፖላይዝ ወደ መደረግ የተዘነበለ ነው፡፡››[71]

***ሶስተኛው ልዩነት***- የአዕምሮ እውነታዎች ‹‹እቀባዎችና ድንበሮች ሆነው የሰው ልጅ በተፈጥሮው የሚቆጣጠራቸው የራሱን ተግባራት ወደ ያልታወቀ መዳረሻ ለማድረስ የዘገመ ሒደትን ይወስድበታል፡፡›› የወሕይ እውነታዎች ‹‹መለኮታዊ አሰራር ስለሆኑና ለተሸካሚ አምባሳደሮቹ ያለምንም ድካምና ልፋት የሚደርሳቸው የከበሩ ልግስናዎች ናቸው፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ራዕዩ ሲወርድ በብርሃናማ አክናፉ ከዐይን እርግብግብታ ወይም ከዚያ በፈጠነ መልኩ ታከባቸዋለች፡፡››[72]

---

[69] ድራዝ፣ አድ-ዲን ገፅ 63

[70] ያለፈው ምንጭ ገፅ 101

[71] ያለፈው ምንጭ ገፅ 65

[72] ያለፈው ምንጭ ገፅ 66

እስልምና የሰዎች ህሊና ንቁ ስለሆነ ብቻ ከውስጡ የሚወጣን አመክንዮ ከነልዩነቱና ተጣርሶው ሁሉ ያምኑትና ይቀበሉት ዘንድ ሰዎችን አይፈልግባቸውም፡፡ ታርቱሊያን (155-240 ዓ.ል) የተሰኘው አንድ የቤተክርስትያን ፖፕ እንደገለፀው «የማይቻል ስለሆነ አምኜዋለሁ» የሚል የጭፍን ተከታይነት የክርስትና ቅርፅ ዓይነትም ኢስላም የለውም፡፡ ይልቅ ኢስላም ከጅማሬው ጥንካሬውን በአመክንዮ ላይ የመሰረተ እምነት ሲሆን ለምሳሌ ያህል መጣረስን አስወግዶ የምክንያትን ሕግ ይይዛል፡፡ ህሊናቸው በደከሙ ወይም መረጃ የመያዝ አቅማቸው የተበላሹ ሰዎች አዕምሮ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ኢስላም ውስጥ በዐቅል (አዕምሮ) እና ነቅል (አንቀፅ ነቃሽነት) መሃል ልዩነት የለም፡፡

ኢብኑ ተይሚያ ይህን በመጠቀ ሁኔታ ሲገልፁት «ማንኛውም ጥመት ከሸሪዓ ጋር መጣረስ እንደሆነው ሁሉ ከአዕምሮ ጋርም መጣላት ነው፡፡» ይላሉ፡፡[73]

በተጨማሪም «ሱናን የሚጣረስ ይዘት ያለው ማንኛውም መንገድ ከሸሪዓ የሚጋጭ ከመሆኑ በተጨማሪ በህሊና ሚዛንም ከንቱ ነው፡፡» [74]

በኢብኑ ተይሚያ ትንተና መሰረት የዚህ በአዕምሮና አንቀፅ ነቀልነት መሃል ያለው ጠንካራ ትስስር መነሻው «አላህ ባሪያዎቹን በእውነት ላይ የፈጠራቸው መልዕክተኞች የተላኩት ይህን ተፈጥሮ ለማሟላትና ለማፅደቅ አንጂ ተፈጥሮውን ለመቀየርና ለመለወጥ አይደለም፡፡»[75] ነው፡፡ «የመልዕክተኞች ጠላቶች ግን በተቃራኒው የአላህን አፈጣጠር መለወጥ ይከጅላሉ፡፡»[76] ኢብኑ ተይሚያ በብዙ ድርሳናቸቸው ላይ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተዋል፡፡[77]

---

[73] አሕመድ ቢን ዐብዱል ሐሊም ኢብን ተይሚያ ‹ሚንሃጁ ሱነቲ ፊ ነቅዱ ከላሚ ሺዓቲል ቀደሪያ›

[74] አሕመድ ቢን ዐብዱል ሐሊም ኢብን ተይሚያ ‹መጅሙዑል ፈታዋ›

[75] ኢብን ተይሚያ፣ መጅሙዑል ፈታዋ 260/5

[76] ኢብን ተይሚያ ‹ሚንሃጁ ሱና›

[77] አሕመድ ቢን ዐብዱል ሐሊም ኢብን ተይሚያ ‹ደርኡ ተዓሩዲል ዐቅሊ ወን-ነቅሊ አው ሙዋፈቀቲ ሶሒሒል መንቁሊ ሊሶሪሒል መዕቁሊ›

ድራዝ የአዕምሮን ጸጋና ውበት ከተፈጥሯዊ አካልነቱ ጋር በሚገባ ለመግለፅ ጥረት አድርገዋል፡፡ ምክንያታዊና ነፃ ፈቃድ በተፈጥሯችን ውስጥ ዋጋ የሚሰጠው አንድ ክፍል ሲሆን የተቀረው ስሪታችንን ግን ከሌሎች ፍጥረታት ጋር የምንጋራው ነው፡፡ የኛ ልዩ መሆንም በርሱ ነው፡፡ በተመሳሳይ ወቅት ግን ማሰብ መቻል በራሳችን ላይ ትኩረት እናደርግ ዘንድ ቀስቃሽ ኃይል ነው.....»[78]

ቀደም ብለው ኢብኑ ተይሚያ እንዳብራሩት ድራዝም የአዕምሮንና ራዕይን ጠንካራ ትስስር ገልፀዋል፡- «በቁርአን ውስጥ አዕምሮና ራዕይ አንድ ላይ ጎን ለጎን ይሄዳሉ፡፡

وَقَالُوا لَوْ كُنَّا نَسْمَعُ أَوْ نَعْقِلُ مَا كُنَّا فِي أَصْحَابِ السَّعِيرِ

«የምንሰማ ወይም የምናስብ በነበርንም ኖሮ በነዳጅ እሳት ጓዶች ውስጥ ባልኾን ነበር» ይላሉ፡፡ (ሙልክ ፤10)

ከሚለው የቁርአን አንቀፅ ውስጥ እንደምንረዳው በአንድ አማኝ ልብ ውስጥ ሁለት ብርሃኖች ይፀናሉ፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ አምላክ የለሹ አንድ ብርሃን እንኳ አያገኝም፡፡ ቁርአን ውስጥ የጥምር የብርሃን ምልክት ሆኖ የተቀመጠው ትርጉም ይህ ነው፡፡

نُّورٌ عَلَىٰ نُورٍ

« (ይህ) በብርሃን ላይ የኾነ ብርሃን ነው፡፡ » (አን-ኑር 35) [79]

የተፈጥሮ ህግና ድንጋጌ ከስነ-ምግባራዊው ራዕይ ድንጋጌ ጋር ተባባሪ ነው፡፡ «የዚህ አዲስ ሸሪዓ ሚና ያለምንም ጥርጥር ፈፅሞ የተፈጥሮን ህግ ከንቱ ማስቀረት አይደለም፡፡

---

[78] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 405

[79] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 67

ምክንያቱ ደግሞ ሁለቱም እውነታዎችና ሊጣረሱ የማይችሉ ስለሆኑ ነው፡፡ ሆኖም የመለኮታዊው ራዕይ ሚና የሚሆነው የተፈጥሮውን ህግ ማፅናት፣ ለንፅህናውና ጽዳቱ ጠንካራ ሰነድ መሆን ነው፡፡[80]»

ድራዝ አክለውም ጉዳዩ ከመሰረቱ ከሁለቱ ምንጮች ጋር አይተሳሰርምም ይላሉ፡፡ ተፈጥሮ እና አሟዩ እንዲሁም አፅንዖት ሰጪው ራዕይ (ወሕይ) ጋር ከምንጭነት አንፃር እኩል ሲሆኑ የሚለያዩት በንፅህና እና በቅርበት ብቻ ነው፡፡ «ለሰዎች በጣም ቅርቡ (አዕምሮ) ሲሆን ከንፅህና አንፃር ዝቅተኛ ነው፡፡ ያ የሚያሟላው ብርሃን ግን (ለአዕምሮ ራዕይ ለማለት እንደሆነ ልብ ይሏል) ለመገኘት በጣም ቅርብ አይደለም፡፡»[81] ይላሉ፡፡

ድራዝ ይህን ያሉት የአዕምሮን ጎዳይና ሚናውን ለማሳነስ አስበው አይደለም፡፡ አዕምሮ የተጠያቂነትና ኃላፊነት ዋነኛ ማዕከል፣ ተቀባይ ወይም ውድቅ አድራጊ መሳሪያ ነው፡፡ ቀጥሎም በሰው ልጅ ስራት ውስጥ በሙሉ እምነትን ግድ ያደርጋል፡፡ የወሕይ ብርሃን ደግሞ የአዕምሮን ብርሃን አፅዳቂ የብርሃን ምንጭ ነው፡፡

«በእኛ ላይ (የቁሳዊ) ኃይል ተፅዕኖ የለውም፡፡ በግለሰባዊ የውስጥ ማንነታችን በኩል ካልሆነ በስተቀር ስነ-ምግባራዊ ትርጉምም የለውም፡፡ ለዚህ ውስጣዊ ማንነት ዕውቅና መስጠት አንዱ መሟላት ያለበት ቁም ነገር ሲሆን ከዚህ የግለሰብ ውስጣዊ ማንነት እጅ፤ በሁሉም ሁኔታዎች ቀጥታ ትዕዛዛትና ጉዳይን እንቀበላለን፡፡ ጤነኛ ሰዋዊ አዕምሯችን ለመለኮታዊ ህግጋት እናድር ዘንድ ያዘናል፡፡»[82]

ቁርአን ከሪም ለዚህ ነው አስተምህሮቱን ለህሊናዊ ቅኝት የሚያቀርበው «እርሱ (ቁርአን) ከሌሎች እሴቶቹ በተጨማሪ ከአዕምሮ ጥበብ፣ እውነታ፣

[80] ያለፈው ምንጭ ገጽ 405
[81] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 34
[82] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 34-35

ፍትሕ፣ ፅናት ጋር ተጣጥሞሽ ይፈጠር ዘንድ ይተጋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ታዲያ የስነ-ምግባር ውስጣዊ ማንነት ይፈጠራል፡፡» [83]

እውነታ መቼም ቢሆን ከእውነታ ጋር አይጣረስም፡፡ በራዕይ (ወሕይ) እውነታዎችና በአዕምሮ እውነታዎች መሃል ፈፅሞ መጣረስ የማይታሰብ ነው፡፡ ይልቁኑ አዕምሮ የእምነት ግንባታ መሰረት እና የኃላፊነት ማዕከል ነው፡፡ እውነተኛ ዲን የሚገነባው በአመክንዮ መርሆችና ሁሉም ልሂቃን እጅ በሚሰጡበት የህሊና የማሰብ ጅማሮ ነው፡፡ በርግጥ ድራዝ በግልፅ እንዳስቀመጡት የአማኝነት መገለጫ በመሰረቱ በህሊና ማህደር ውስጥ በሁለት ምርኩዝ ላይ የተደገፈ ነው፡፡ እነርሱም የምክንያት እና ድንበር ህጎች ናቸው፡፡

«እነዚህ ሁለት ህግጋት በተሟላ መልኩ ከግንዛቤ ከገቡ ማብቂያቸው የሚሆነው የመጠቁ የዲን መሰረቶች፣ የተውሒድ እምነትና የመንፈስ ዘውታሪነት ናቸው፡፡ የሺርክ አስተሳሰብ፣ ጣዖታዊነትና እምነት የለሽነት የሚወለዱት ከአዕምሮ ስንፍና እና ዝንጉነት ነው፡፡»[84]

የምክንያት ህግ እንደሚያመለክተው ከሆነ ማንኛውም አጋጣሚ ከራሱ ተነስቶ ያለ ምክንያት አይከሰትም፡፡ ይህ የአዕምሮና አጠቃላይ ህግ ታዲያ በማይታየው እና በገሃዱ ዓለም ነፀብራቅ መሃል አስተሳሳሪ ገመድ ነው፡፡

«በገሃዱ ዓለም መነሻ ምክንያት ያልተገኘለት ነገር በማይታየው ዓለም ሊኖረው ግድ ነው፡፡»[85] ይላሉ፡፡

ይህን የማይሰበር የአዕምሮ ህግ ከያዝን ዘንድ «መኖሩ ግድ ከሆነውና የምክንያቶች ሁሉ ምክንያትና ከነገራት ሁሉ ማብቂያው አስገኚ ሰበብ መሸሽ አይቻልም፡፡»[86] ማለት ነው፡፡

---

[83] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 406

[84] ድራዝ፣ አድ-ዲን 99

[85] ያለፈው ምንጭ ገፅ 136

[86] ያለፈው ምንጭ ገፅ 100

የማብቂያ ህግ ደግሞ «ማንኛውም ተጣጥሞሽና ደርዝ ያለው ስርዓት የግዴታ ከሚሆንበት ነገር ውስጥ ያለምንም ዓላማ አለመከሰቱ ነው፡፡ ማንኛውም ዓላማም ግብን ማስመርና ማስቀመጥ አይቀርለትም፡፡ ይህ የሚሆነው ቋሚ ወደሆነ አጠቃላይ ግብ እስኪደርስ ድረስ ሲሆን፣ የግቦች ሁሉ ግብም ነው፡፡»[87]

የሰላ አመክንዮ በዚህ መልኩ ከማሰብ ጀምሮ አልፋ አሜጋ ፈጣሪ መኖሩንና የምክንያቶች ሁሉ መነሻና የግቦች ሁሉ ግብ እንደሆነ አመላክቷል፡፡ «የዚህ የመጀመሪያና መጨረሻ እውነታ መገኘት ችላ ሊሉት የማይገባ እጅ ሊሰጡት የሚያሻው የአዕምሮ ግዴታ ነው፡፡»[88]

ከፊል ሰዎች በአዕምሮ እሳቤ የተነሳ ለእምነት ያላቸው ዕይታ ቢሳሳ፣ ያ የአዕምሯቸው አድማስ ማጠርና ስንፍናው እንጂ ፈፅሞ ሌላ አይደለም፡፡ ወይም ደግሞ ከእምነቶች ውስጥ ያጠኗቸው በሰው እጅ ተሰርተው የነተቡትን ሲሆን ነው፡፡ አሊያ የግድፈት ጣት ወደ ገላቸው የገባባቸውን ሰማያዊ መልዕክቶች ነው፡፡ እውነተኛ የእምነት አስተምህሮ ከንፁህ የአዕምሮ ፍሬዎች ጋር ፍፁም አይጣረስም፡፡[89]

ድራዝ ከአድማስ መስፋትና ለድብቁ ዓለም ካለው እሳቤ አንጻር አዕምሮን ለሁለት ከፍለውታል፡፡

1. የረጋ፣ የሰከነና ፈጣን አዕምሮ
2. አድማሰ ሰፊና ነፃ አዕምሮ ናቸው፡፡

የተረጋጋ፣ የሰከነና ፈጣን የተባለው አዕምሮ በሩቁ ዓለም የማመን መርሆችና የቅርብም ይሁን የረዥም ግቦቹ ላይ በመብቃቃት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አዕምሮ አቅጣጫው ከፍጥረተ-ዓለሙ አሻሚ መገለጫዎች ይልቅ ወደ አጠቃላይ የስሪት መርሆችና ስርዓት ወዳለው ትሩፋት የተዘነበለ ነው፡፡[90]

---

[87] ድራዝ፣ አድ-ዲን ገፅ 100

[88] ያለፈው ምንጭ ከገፅ 100-101

[89] ያለፈው ምንጭ ገፅ 165

[90] ድራዝ፣ አድ-ዲን ገፅ 89

አድማሰ ሰፊ፣ ነፃና ምጡቅ አዕምሮዎች ደግሞ «በአንፃራዊ መለኪያዎች እንዲሁም ከፍልፋይ ትርጉሞች ድንበር ላይ መቆምን ውድቅ ያደርጋሉ፡፡ ወደ ህገ-ህግጋት እስኪመጥቁ አንድ ነጠላ ህግ ላይ ብቻ አይቆሙም፡፡ እንደውም እነዚህን ህግጋት ያወጣውንና ያቀናጀውን እጅ ለማየት ይቋምጣሉ፡፡ በአጠቃላይ ምጡቅ ህሊናዎች ሁሌም የሚያማትሩት ከከፍልፋይ እውነታዎች ጀርባ ያለውን ዝንተ-ዓለማዊና አጠቃላይ በሆነ እውነታ ላይ ነው፡፡»[91] እርሱም ጥራት የተገባው ጠቢቡ ፈጣሪ አላህ ነው፡፡

ድራዝ የአዕምሮንና የራዕይን ጣምራዎች በተመለከተ የደረሱበት መቋጫ «በእኩይና ሰናይ ተግባራት መሃል መለየት መቻል ሰማያዊ ድንጋጌ ከመሆኑ ቀደም ብሎ በሰው ልጅ ነፍስ ተፈጥሮ ውስጥ የተቀበረ ውስጣዊ ራዕይ ነው፡፡ አዕምሮና ራዕይ ለአንድ ርዕሰ-ጉዳይ ድርብ መሪ ብርሃናት እንጂ ሌላ አይደሉም፡፡ ለአንድ መሰረታዊ ተጨባጭ ድርብ ትርጉሞች ናቸው፡፡ ስረ-መሰረታቸውም ወደ ነገራት ምንጭ የተመዘዘ ነው፡፡»[92] ሆኖም መለኮታዊው ድንጋጌ «ተፈጥሯዊውን ስነ-ምግባራዊ ድንጋጌ ያሟላል፡፡»[93] ይላሉ፡፡

አንዳንዴ ከእውነትና ሰናይ ጉዳይ ኢጋጅ የሆኑ ረካካዎች ወይም ወደ መዋለልና አለመረጋጋት የሚወስዱ ፅልመቶችን ለመከላከል ይረዳው ዘንድ ተጨማሪ ወይም ቅጥያ ሳይሆን የሰው ልጅ የተፈጥሮው መሰረታዊ አስፈልጎት ይሆናል፡፡

ድራዝ ለዚህ የአምልኮ ተግባራትን እንደ ምሳሌ ይጠቅሳሉ፡፡ «ለእያንዳንዱ ሰው በነፍስ ወከፍ እነዚህን የአምልኮ ተግባራት የማድረግ መብቱ ለርሱ የተተወ ቢሆን ከሁለት አማራጮች ከአንዱ አይዘልም፡፡

- ምንም ማድረግ የማይችል ግራ የተጋባ ሆኖ ይቆያል ወይም
- በምናባዊነት እና ራስን ማስገደድ ሁኔታ ውስጥ ራሱን ያስገባ ነበር፡፡ »[94]

---

[91] ያለፈው ምንጭ ከገፅ 89-90
[92] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ 16
[93] ያለፈው ምንጭ ገፅ 36
[94] ያለፈው ምንጭ ገፅ 31

ስለዚህ ከድራዝ ጋር ዕውቅና ልንሰጥ የሚገባን ጉዳይ ቢኖር «ይህ ስሜት የዘነጋውና ልማድ የሚበክለው ተፈጥሯዊ ብርሃን ለሆነ ዓይነት ያለመረጋጋት አደጋ መጋረጡ አይቀሬ ነው፡፡ ሆኖም ግን በጥቅሉ ከቦታ፣ ሁኔታና ጊዜ አንፃር ካለ ልዩነት ጋር ከሁሉም አቅጣጫ የሚመጣን ተግዳሮት ያሸንፋል (መለኮታዊ ብርሃን)፡፡[95]

ከሰማይ ከሚመጣ የራዕይ ብርሃን ውጪ የሰው ልጅ መልካምና እኩይን በማወቅ ሂደት ውስጥ ዘላቂ በሆነ ልፊያና ትግል ውስጥ ይዘወትራል፡፡ «ስሜት ስሜትን እንደሚላተመው ሁሉ ህሊና ህሊናን ይናረታል፡፡» [96] የሰው ልጅ ታሪክ ይህን ወሰን የለሽ መደበላለቅ ከብዙ ምሳሌው ጋር አሳይቶናል፡፡ ከቡድሂዝም ራስን ከምድራዊ መጣቀሚያ በማገድ ከመጉዳት ‹ነርፋና› ስርዓት ጀምሮ እስከ ግሪክ ‹የስቶይክ ወሲባዊ ልቅነት› ድረስ አስነብቦናል፡፡ ይህ የተፈጥሮ ህግም ይሁን ሰማያዊ ሸሪዓን አውራጁ አምላክ እንደሻው የራዕይ ብርሃን እና ተፈጥሯዊ ዕይታ እኩል መራመድ እንዳለባቸው ህያው ምስክር ነው፡፡ ስንቋጨው «በአንድ ጉዳይ ብያኔ ላይ ፍልስፍና ብቻ ጎልቶ ከወጣ ለብቻው አይታመንበትም፡፡ ወሕይ እና አዕምሮ በአንድ ጉዳይ ተጣጥመው ከተገኙ የለሊት ላምባ ከቀን ወጋገን ጋር እንደተገናኙ ነው፡፡ አላህ ለከጀለው የሚመራው በብርሃን ላይ ብርሃን ይሆናል፡፡» [97]

---

[95] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 14
[96]ያለፈው ምንጭ ገፅ 32
[97] ድራዝ፣ አድ-ዲን 66

## ኃይማኖት እና ሳይንስ

ዘመናዊውን የኢስላማዊ አስተሳሰብ ሳሎን በማጣበብ ከተገዳደሩት ትላልቅ ጣምራዎች መሃል ኃይማኖትና ሳይንስ በዋነኝነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ናቸው፡፡ ካሉት ወሳኝ ልዩነቶቹ ጋር ከቀደመው የአዕምሮና አንቀፃዊነት ጣምራ የተመዘዘ ነው፡፡ የቀደመው ችግር ከአዕምሮ ሜካኒክስ ጋር የተያያዘ ሲሆን የዚህኛው ደግሞ ከአዕምሮ ውጤቶች ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ያለንበት አዲስ ዘመን የዕውቀት አድማስ ከከዚህ ቀደሙ ሰፍቶ የሰው ዘር አይቶት በማያውቀው ልኬት ተለጥጧል፡፡ የዘመኑ ሰው በራሱ የተብቃቃና የተሞላም ሆኗል፡፡ በራስ የመተማመኑ መጠንም ድንበር አልፏል፡፡ በዚህም የተነሳ የፈጣሪውን እዝነትና ርህራሄ ማጤንና መገንዘብ አቅቶታል፡፡ ዝንጋቴው ቁርአን መጀመሪያ አካባቢ ሲወርድ ከጠቀሳቸው የሰው ልጅ ባህሪያትም ነው፡፡

كَلَّا إِنَّ الْإِنسَانَ لَيَطْغَىٰ ۝ أَن رَّآهُ اسْتَغْنَىٰ

«በእውነቱ ሰው ወሰንን ያልፋል፡፡ ራሱን የተብቃቃ (ባለ ሀብት) ኾኖ ለማየቱ፡፡» (አል-ዐለቅ 6-7)

በቀደሙት እምነቶች ላይ የሳይንሱ ምጥቀት የከፍተትና ድክመት ጎናቸውን ገልጦባቸዋል፡፡ ይህን ያደረገውም የአመክንዮአቸውንና የእሳቤያቸውን ባዶነት ከሳይንስና ፍሬው ጋር ለቁሳዊው ገሃዱ-ዓለም ጋር መጣረሱን ግልፅ በማድረግ ነው፡፡ ክስተቱ ብዙውን የሰው ልጅ ክፍል በእምነቶች ላይ ያለውን ዕይታ፣ ከሰማይ በወረደው ራዕይ እና የሰው ልጅ ልብ በወለደው መሃል ሳይለይ በጎሪጥ የሚያይና ውድቅ አድራጊ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ብዙ የኢስላም ተጣሪዎች (ዱዓት)፣ ንቁአን እና ልሂቃን በአዲሱ ዘመን የተከሰቱ የእምነትና ሳይንስ ጉዳዮች ፍትጊያ መሃል በሎጂክ መተላለፍ እንዲሁም ከአድማስ ቅቡልነት አንፃር ብዙ ማስተካከሎችን ለማድረግ ተግተዋል፡፡

በዚህ ረገድ ከተጉት መሃል ዶክተር ድራዝ ውድ ዋጋ ያለው አበርክቶ ካላቸው ውስጥ የሚመደቡ ነበሩ፡፡ «አድ-ዲን» የተሰኘው መጽሐፋቸው አካቶ የያዘው እንዳለ ሆኖ ሌሎች ድርሳኖቻቸውም ላይ ርዕሰ-ጉዳዩን አመልክተዋል፡፡ በድራዝ ገለፃ መሰረት በሳይንስና ኃይማኖት መሃል ያለው ፍትጊያ ምክንያቱ ሁሌም የሳይንስ ወይም የኃይማኖት ብቻ አይደለም፡፡ በሳይንስና ኃይማኖት መሃል ያለውን ፍትጊያ በሶስት ሐሳቦች አሳጥረው ገልፀውታል፡፡

**የመጀመሪያው** ፡-አንዳንዴ የኃይማኖትም ይሁን የሳይንስ ስም ብዝበዛ ይበዛባቸውና፣ ለተለያዩ ፍላጎቶች፣ ለድብቅ ዓላማዎች ይውላሉ፡፡ ለምሳሌ የስም ማዳኛ፣ ንብረት ማካበቻ፣ ኃይል፣ ስልጣንና ጥቅማጥቅምን ለማጋበስ የቅርፅ ፍትጊያ የሚካሄድባቸው ማዕዘናት ይሆናሉ፡፡[98]

**ሁለተኛው**፡- «ወደ መስዋዕትነት፣.ነፍስን በፍትሕ ወደ መያዝ በሚወስደው በመጠቁ መንፈሶች ዝንባሌ ዘውታሪ እና ከተቃራኒው ወደ ነውጥ፣ ልቅነትና ራስ ወዳድነት በሚወስደው የቁስ ዝንባሌ መሃል የሚደረገው እውነተኛ ፍትጊያ መታያ መስክም ነው፡፡» [99]

**ሶስተኛው ደግሞ**፡- «በመልካም እሳቤ በሳይንቲስቱና በኃማኖተኞቹ ካምፕ መሃል የሚፈጠሩ የሃሳብ መጣረሶች፤ አንዱ አንዱ ዘንድ ያለውን ለማሳበልና ለማጣጣል የሚደረግ ፍትጊያ ነው፡፡» [100]

ድራዝ ለሁለቱ የአስተሳሰብ ቅርፆች መፍትሄ ለማግኘት ነፍሳቸውን አላስጨነቁም፡፡ ምናልባት የመጀመሪያው ያጋጠመው አስኳሉ ላይ የስነ-ምግባር ግድፈት ስለሆነ ስነ-ምግግራዊ እንጂ አስተሳሰባዊ መፍትሄ አያስፈልገውም፡፡

---

[98] ድራዝ፣ አድ-ዲን 68

[99] ያለፈው ምንጭ

[100] ያለፈው ምንጭ

ሁለተኛው ግን በመሰረቱ መፍትሄ ፍለጋም አያሻውም፡፡ ድራዝ ልዩ ትኩረት የሰጡት ሶስተኛው ቅርፅ ላይ ሲሆን እርሱም ንጹህ የአስተሳሰብ ልዩነት ላይ ነው፡፡ ከሁለቱም ጠርዞች ተነስተው ወደ እውነት ተጉዘዋል፡፡ እነዚህ በመልካም እሳቤ «በሁለቱ ካምፖች መሃል የሚነሱ የሳይንስና የእምነት የአስተሳሰብ ልዩነቶች ከሁለት ቅርፆች አንዱ ላይ ይወድቃሉ፡፡

***የመጀመሪያው ቅርጽ፡-*** የእምነት አናቅፅ ከሳይንሳዊ አዳዲስ ግኝቶች ጋር መጣረሱ ነው፡፡ «ከሚታወቁ ጉዳዮች ውስጥ ሳይንስም እምነትም የተለያዩ ብያኔ የሰጡባቸው ይኖራሉ፡፡ ይህ የሚከሰተው እምነቶች ከፊል የሳይንሳዊ ጉዳዮችን፣ አውነታዎችንና ዕታዎችን በመንፈሳዊ ጎናቸው ብቻ በመመዘንና በመፍረድ በአማኙ ላይ ግዴታ አድርገው የሚሄዱበት መንገድ ነው፡፡»[101]

ብዙ እምነቶችን በተከታዮቻቸው ልቦና ውስጥ ሞገስ ያሳጠውና ያወደመው በእምነቱ ቀኖና ውስጥ ያለው አንቀፅ የዘመናዊው ዓለም ሳይንስ ከደረሰባቸው ዕይታዎችና ግኝቶች ጋር ፊትለፊት ሲላተምና ሲጋጭ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በሳይንስና እምነት መኃል ያለው መጣጣምም ይሁን መጣረስ «በሁሉም እምነት ውስጥ ላሉ እውነታዎችም ይሁኑ ብከለቶች ከትክክለኛ ሳይንስ መደምደሚያዎች እና ጤነኛ አዕምሮዎች ጋር ከመጣጣም መጠኑ ጋር መለኪያ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡»[102]

በዚህ ጉዳይ ማጠቃለያው «እምነትም ይሁን ሳይንስ እውነታ ከሆኑ እውቅና ሊሰጣጡና ሊተጋገዙ ግድ ይላቸዋል፡፡ ነገርግን አንዱን አንዱ የሚያስዋሸውና የሚያሳንሰው ከሆነ ያለምንም ጥርጥር አንደኛቸው እብለትና ጥመት መሆኑ ግሞ ግድ ነው፡፡»[103] መቼም ቢሆን እውነታ ከእውነታ ጋር አይጣረስም፡፡

---

[101] ድራዝ፣ አድ-ዲን 70

[102] ድራዝ፣ አድ-ዲን 70

[103] ያለፈው ምንጭ

**ሁለተኛው ቅርፅ** ፡- በሳይንቲስቶችም ይሁን የእምነት ሰዎች ዘንድ የአስተሳሰብ መኩራራት ሲሆን አንዱ ጠርዝ የደረሰበትን እውነታ የማጣጣል ቅርፅ ያለው ነው፡፡ «ውድቅ በሚያደርግ መረጃ ወይም በሚደበዝዘው አሻሚ ነገር ሳይሆን፤ በማለፍ ወይም ስለሚያውቀው ነው፡፡ ሁሉም የሚያስበው በርሱ የቅኝት ከበብ ውስጥ፤ በወቅቱ ካልገባለት እውነታ የለውም ብሎ ይወስናል፡፡»[104]

ድራዝ በዚህ መገለጫ ላይ አስተያየት እንደሚሰጡት «ይህ የዕይታ እጥረት፣ አለፍ ሲልም ከመሃይምነትና ከንቱነት የሚነሳ ነው፡፡»

የሰው ልጅ በዕውቀቱ በሚያካብበው ጉዳይ ላይ ማስተባበሉን በሳይንስም ይሁን እምነት ዕውቀት ጠለቅ ያሉቱ አይስቱትም፡፡ እዚህ ላይ የሚወድቁት ከተርታው የተገኙ ወይም ጀማሪ ተማሪዎች ናቸው፡፡»[105]

ለዚህ አስተሳሰብ ከንቱነት በድራዝ ዕይታ ፍቱን መድሃኒቱ «ሁሉም ሰው የነፍሱን አቅም ችሎታና ልኩን ማወቁና ወሰኑ ላይ መቆሙ ሲሆን፤ በዚህም ጎዳና ላይ ማንኛውም ቡድን የደረሰበትን ማጽደቅና ያልደረሰበትን ደግሞ አለማጣጣል ነው፡፡»[106]

ሳይንስን ከመላተም አኳያ ከእምነት ከንቱነት ምሳሌዎች ውስጥ የአውሮፓ ህዳሴ ማልዶ በመጣበት ወቅት ቤተ-ክርስትያን አጥብቃ ይዛ የነበረቺው አቋም ይጠቀሳል፡፡ በተለይ በአጽናፈ-ዓለሙ የአካላዊ አወቃቀር ዙሪያ የተነሱ ሐሳቦችን እና ጋሊሊዮና መሰሎቹ የፈለክ እንዲሁም የፊዚክስ ሳይንቲስቶች የደረሱባቸውን አዳዲስ እውነታዎች መቀበልን ውድቅ ከማድረግ አልፋ ከጥላቻ እንዲሁም ውግዘት አልፋ ከነዚሁ ንቁአን ውስጥ ከፊሉን በሕይወት አቃጥላቸዋለች፡፡

---

[104] ያለፈው ምንጭ ከገፅ 68-69

[105] ድራዝ፣ አድ-ዲን 69

[106] ያለፈው ምንጭ

በእምነት ፊት የሳይንስ ትዕቢት መገለጫ ደግሞ ድራዝ ትኩረት ካደረጉባቸው ምሳሌዎች ውስጥ ከ1798-1857 ድረስ የኖረው ፈረንሳዊው ፈላስፋ ኦገስት ኮንት ያበሰረውን የአዎንታዊ እሳቤ መስመር ነው፡፡

ኮንት በዚህ ንድፈ-ሐሳቡ የሰውን ልጅ የእሳቤ የዕድገት እርከኖች ዘመንና ዝግመት ላይ በመመርኮዝ በሶስት ከፍሎታል፡፡

- የእምነት ፍልስፍና መዳበር
- የረቂቅ ፍልስፍና ማደግና
- የተጨባጭ ወይም ሳይንሳዊ ፍልስፍና መዳበር ናቸው፡፡

በዚህ በኮንት ዕይታ መሰረት የእምነት እሳቤ ዕድገት ምሳሌው «የሰው ልጅ በሕፃንነቱ ነገራትን ሲጀምር ያለው ሂደት ዓይነት፣ ከዚያም እያደገ ሲመጣ በታዳጊነቱ ያደርገው ከነበረውና ማህበረሰቡን ሲቀላቀል በአስተሳሰብ መለወጡን ነው፡፡ በስተመጨረሻ ያለው እርከን የተሞክሮ ነውና የፈርጣማነት፣ የአስተውሎትና ምሉዕነት ይሆናል፡፡»[107]

በዚህ እሳቤ መሰረት ሳይንስ የእምነትን ቦታ ይነጥቅና የአንቀሳቃሽነት ሚናውን ይሰልበዋል፡፡ እምነት ወዳለፈ ዘመን አማታሪና ባይተዋር እሳቤ ሲሆን ይሆናል፤ ሳይንስ ደግሞ የሰው ልጅ መፃዒ ጊዜ መሪና መረጃ አቀባይ አብሪ ይሆናል፡፡

ድራዝ የዚህን የዝግመተ-ለውጥ ንድፈ-ሐሳብ መሰረቶች በአሳማኝ መረጃዎች እንደሚከተለው በማብራራት በሚገባ ሐይሰውታል፡፡

**አንደኛ፡-** «ኮንት ያሰባቸው ሶስቱ ሁኔታዎች የተከታታይ ታሪክ አጋጣሚዎችን ወካይ አይደሉም፡፡ እንደውም በሁሉም ህዝብ ውስጥ በየወቅቱ የሚከሰቱ

[107] ድራዝ፣ አድ-ዲን ገፅ 77

የአዝማሚያዎችና መስመሮች ቅርፆች ናቸው፡፡»[108] በሁሉም ዘመናት ኮንት እንዳሰበው የዝግመተ-ለውጥን እሳቤ አመልካች የለም፡፡

**ሁለተኛ**፡- ለነዚህ ፌኖመናዎች ትክክለኛው ቅደም ተከተል ኮንት የመጨረሻ እርከን ያደረገው ግን የመጠቀውና መጀመሪያ መሆን የሚገባው የተጨባጭነት እርከን ነው፡፡ «የነፍስ የሕፃንነት እርከን እንጂ የሙብሰልና ምሉዕነት ደረጃ አይደለም፡፡ እርሱም ቀስቃሹ መንስኤ አስቸኳይ ጉዳዮችና የቀን ተቀን ሕይወት አስፈልጎቶች ናቸው፡፡ የስሜት ኃላፊነት እንጂ የአዕምሮም አይደለም፡፡ የተጋላጭነትና ውጥረት ይዘት እንጂ የአቅምና ውጤታማነት አይደለም፡፡»[109]

**ሶስተኛ**፡- እምነታዊ ዕይታ በተጨባጭ ከሰው ልጅ የአስተሳሰብ ቅርፆች ሁሉ ምጡቁ እና ክቡሩ ነው፡፡ እርሱም «የሚወለደው ነፍስ አድማሷ ሲሰፋ ሲሆን ፍጥረተ- ዓለሙን ገሃዱንም ይሁን ድብቁን አልፎ ከጀርባው ስላለው ማጤን ይጀምራል፡፡ በዕይታ ደረጃ ግን ዘርፉ የሰፋ እና የራቀ ነው፡፡»[110]

ድራዝ በዚህ መልኩ ኮንት በዘመን ያስቀመጠውን ጥቅል ከመሰረቱ ይሃይሱታል፡፡ ነገራትን በሚገባቸው ቦታቸው ላይ ያኖራሉ፡፡ በሰው ልጅ የእሳቤ ዕድገት ውስጥ የኮንት ንድፍ በዘመን እርከን መቀመጡ በሁሉም ዘመናት ምጥቀት አስፈላጊ ናቸው፡፡ «የስሜት፣ የሚታተርና የዘመን ተሻጋሪ አዕምሮ አስፈልጎት ነው፡፡» ይላሉ ድራዝ፡፡ [111]

የድራዝን አስተያየት ሚዛን እንዲደፉ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች ውስጥ በ20 እና 21ኛው ክፍለዘመን ያለው የሳይንስ እድገት ኮንትን በዘመን ከተጋሩት የ19ኛው ክፍለዘመን ሳይንቲስቶቸ አንፃር የበለጠ ልከኛና ያነሰ ጉረኛ አደረጋቸው፡፡

---

108 ድራዝ፣ አድ-ዲን 78

109 ድራዝ፣ አድ-ዲን ገፅ 79

110 ያለፈው ምንጭ

111 ያለፈው ምንጭ ገፅ 80

«በዘመናችን የሳይንስና ዕውቀት ማደግ የኃይማኖተኝነት ስሜት መጨመር ሰበብ ሆኗል፡፡»[112] እንጂ ልክ እንደ ኮንት ዘመን ከኃይማኖት የመውጣት እና የመላቀቅ ሰበብ አይደለም፡፡ «በሳይንስ ዘርፍ በፍጥነት ማደጋችን አላዋቂነታችንን በደንብ አጉልቶ ያሳየናል፡፡ ያም ፍጥረተ ዓለሙንና እያደር መስፋቱን በተመለከተ ሳይንስ የሚከፍተው አዲስ የመረጃና ምርምር በር ሁሉ አብሮት ሌላ ሰፊ የጥያቄ አድማስ ይከፍታል፡፡ በዚህ መሰረት የመረጃ ወሰን በሰፋ ቁጥር በራሱ የሚያሳየው የአለማወቅን ሰፊ መስክም ጭምር ነው፡፡»[113]

እዚህ ጋር ሳይንስና እምነትን በተመለከተ የመጣው የድራዝ ንግግር ጥልቅና ረቂቅ ነው፡፡ ኢስላማዊውን ተልዕኮ በተለየና ግልፅ በሆነ ቃል አልነጠሉትም፡፡ ስለዚህ ኢስላማዊው መልዕክት ከግዝፈቱና ከመለኮታዊ መሰረታዊነቱ ጋር ከ1400 ዓመታት በፊት ተብራርቶ በወረደው ቁርአን ከሪም ሳይንሳዊ ጉዳዮችን አመላካች፤ ዘመናዊ ሳይንስ በምርምር በደረሰባቸው እውነታዎች መሃል ያለውን ተመሳስሎሽ ማውሳታቸውን እንጨምርበት፡፡ ቁርአን ውስጥ ያሉ ሳይንሳዊ ተዓምራት ማጥናት በራሱ በዘመናችን ራሱን የቻለ የሳይንስ ዘርፍ ሆኗል፡፡

በነዚህ ተዓምራት በመመሰጥ ብዙ ቁጥር ያላቸው የምዕራቡ ዓለም ሳይንቲስቶች ወደ ኢስላም ገብተዋል፡፡ ተዓምራቱን ወደ የትኛውም ሰውኛ መነሻ ምንጭ ሊመልሱትም አልቻሉም፡፡ ከነዚህ ታዋቂ ሰዎች ውስጥ «ኦሪት፣ ወንጌልና ቁርአን በዘመናዊ ሳይንስ የዕይታ ብርሃን»[114] እና «አስተንትኖት በቁርአን»[115] የተሰኙ መፅሐፍትን የፃፈው ፈረንሳዊው የህክምና ዶክተር ሞሪስ ቡካይ ይጠቀሳል፡፡

---

[112] ድራዝ፣ አድ-ዲን ገፅ 81

[113] ያለፈው ምንጭ

[114] *Maurice Bucaille, le coran et la science: Les Ecritures saintes (paris: seghers 1976)*

[115] *Maurice Bucaille, Reflexions sur le coran (paris: seghers 1989)*

ድራዝ ቁርአን ውስጥ ሳይንሳዊ ተዓምራትን በመመራመር ላይ ብዙ ጊዜ የሚሰው ሰዎች ሳይቀሩ የዘነጉትን ወሳኝ ጉዳይ ያስጠነቅቃሉ፡፡ እርሱም «ኃይማኖት እና ሳይንስ ከይዘትና ግብ አንፃር መለያየታቸውን ነው፡፡ የእምነት ግቡ ፈጣሪን ማወቅና ከርሱም መቀናትን መቸር ሲሆን የሳይንስ ግቡ ደግሞ ፍጥረተ-ዓለሙን መመራመርና ለሰው ልጅ ምቹ ማድረግ ነው፡፡ እምነት ሳይንሳዊ ጉዳዮችን የሚያነሳው ለመዳረሻ መንገድነት እንጂ ግቡ ስለሆነ አይደለም፡፡»[116]

ለምሳሌ ያህል የሰውን ልጅ ወደ ፍጥረታት ውበትና የአሰራራቸውን ምጥቀት ወደ ማጤን ማዞሩ የፈጣሪን መኖር፣ አንድነቱንና እዝነቱን ለማሳየት ነው፡፡ በአንድ ዘርፍ ልዩ ሙያተኛ የሆነ ሰው በተግባራዊ ሳይንስ በመታገዝ በአንድ የእምነት ጉዳይ ላይ ምርምር ሲያደርግ ከሳይንስ ፍልስፍናዊና ስነ-ምግባራዊ ማመልከቻ ነው እንጂ ከራሱ ሳይንስ ውስጥ አንድ ክፍል አይደለም፡፡ የሳይንስ መስኩና ይዘቱ ቁስ ብቻ ነው፡፡ ያ ማለት በይዘት የተለያዩ መሆናቸው «የመጣረስ» ሳይሆን «የብዝሃነት» ልዩነት ይሆናል ማለት ነው፡፡ በሁለቱ እንደውም በሁሉም ዘርፎች ውስጥ የጋራና የአንድነት ዓላማ አለ፡፡ እርሱም እውነታን አስሶ መፈተሽና መመራመር ነው፡፡ እውነታ እውነታን አይጣረስም፡፡

ድራዝ በሰው ልጅ የሳይንሳዊ ግኝትና ዕውቀት መሃል ስልታዊ በሆነ መልኩ ልዩነት አኑረዋል፡፡ ወደ ፈጣሪ (ሱወ) በሚያቀርቡንና ከሚያደርሱን ልቅ የሆኑ እውነታዎች ጋር ካለን የቅርበት መጠን አንጻር ቅደም ተከተል አስይዘዋቸዋል፡፡ «ዝቅተኛው አገልጋይ እንጂ ተገልጋይ ያልሆነው ተከታዩ ደግሞ አንድ ላይ አገልጋይም ተገልጋይም የሆነ ነው፡፡ የላዕላይ ዕውቀት ይዘቱ ደግሞ አገልጋይ እንጂ ተገልጋይ እስከማይሆንበት ደረጃ እስኪደርስ ነው፡፡»[117] እርሱም አላህን (ሱወ) ማወቅ ነው፡፡

---

[116] ድራዝ አድ-ዲን ገፅ 70

[117] ድራዝ፣ አድ-ዲን ገፅ 67

ይህኛው «የላቀው ዕውቀት» እውነተኛውን እምነት ማወቅ ነው፡፡ ያለምንም ገደብ ከዕውቀቶች ሁሉ የላቀው እርሱ ነው፡፡ ያ የሆነበት ምክንያት ደግሞ የዓላማው ምጥቀት እና ከዘልዓለማዊ እውነታዎች እንዲሁም ከሕይወት ትርጉም ጋር ባለው ትስስር የተነሳ ነው፡፡ «ከዘልዓለማዊው እውነታ በላይ የሚያያዝ ማንኛውም የተመራማሪ ምኞትና ዓላማ ዱንያ ትወገዳለች እንጂ እርሱ (እውነታው) አይወገድም፡፡ ልቅ የሆነ መልካም ነገር ሌሎች ጉዳዮች ይመዘኑበታል እንጂ እርሱ በምንም ነገር አይለካም፡፡»[118]

የሰውን ልጅ የዕውቀት ደረጃ መለያየት፣ የዲንና ሳይንስን የይዘት፣ የግብና የህብር ልዩነት ከገለፁ በኋላ በሁለቱ መሃል ያለውን ግንኙነት በተስማሚ ቀመር ያሳዩናል፡፡ በዚህ ረገድ የድራዝ ዕይታ በእምነትና ሳይንስ መሃል ያለው ምርጥ ግንኙነት ትስስር ነው፡፡ መተባበሩ ካልተሳካ ግን ለሁለቱም ጥቅም ሲባል በትንሹ «የመልካም ጉርብትና እና አንዱ አንዱን የመገንዘብ»[119] ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል ይላሉ፡፡ በእምነት ትክክለኛ አቋም (አንቀፅ) እና በተረጋገጠ እውነተኛ ሳይንስ መሃል ያለ ፍትጊያን በተመለከተ የድራዝ ዕይታ ፈፅሞ የለም የሚል ነው፡፡

«መቼም ቢሆን እውነታ እውነታን አይጣረስም፡፡ ምክንያቱም አንድን ርዕስ ስለተጋሩ በሁለት ጉዳዮች መሃል መጣረስን መስጋት ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ »[120] ድራዝ ለሁለቱም ጠርዞች የጋራ ጥቅምና መልካም ፍሬ ሲባል የመልካም ጉርብትና፣ አንዱ ሌላውን የመገንዘብን አስፈላጊነት አብራርተዋል፡፡ እምነት ከሳይንስ የሚቀጥፈው ፍሬ ሳይንስ በገሃዱ ዓለም ውስጥ የተገኙ አዳዲስ ግኝቶችን ስለያዘ አዕምሮ ድብቁን ዓለም (ገይብ) ያምን ዘንድ ያመቻችለታል፡፡ «የማይታወቅ ጉዳይ ላይ ለመድረስ የሚታወቅን መንገድ ተጠቅሞ ነው፡፡ የሩቅ ሚስጥር በሚታየው ዓለም ምሳሌ አናሎጂ በማድረግ እንጂ አይታወቅም፡፡

---

[118] ድራዝ፣ አድ-ዲን ገፅ 66
[119] ያለፈው ምንጭ ገፅ 68
[120] ድራዝ አድ-ዲን 68

የላቁ እውነታዎችንም ለመውጣት በዱንያዊ እውነታዎች መሰላል ተጠቅሞ ካልሆነ በስተቀር ቀላል አይሆንም፡፡›[121] ይላሉ፡፡

ዲን (እምነት) ከሳይንስ የሚጠቀመው ትንሹ ነገር ከትክክለኛ አዕምሮ የመነጨ ሳይንሳዊ ተሻሽሎት ሲያሰራጭ እሱን መጠቀም ነው፡፡ ጥቅሙም አይጨበጤ የሆኑ አፈ-ታሪኮችን ለማስወገድና የእምነት ቅርፆችን መመርመሪያ መሳሪያ ይሆናል፡፡

የተፈጥሮና ሂዩማን ሳይንስ ‹‹አፈ-ታሪኮችን ጨለማ መግላለጡ፣ ነፍስ ውስጥ የሚረጨው ብርሃን፣ የማፅዳትና የማሳመር ስራን ይሰራል፡፡ ጤነኛ የሆነን እምነት ለመቀበል የተስተካከለ የአዕምሮን አድማስ ለማበጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ልብ ወደ አንድ ነገር ዘንበል ቢል፣ መዘንበሉ በግልፅ መረጃ ላይ የተመረኮዘ እንጂ በመሃይምነት ግፊት ውስጥ የታሸገና በአስመሳይ ታማኝነት የተጀቦነ አይሆንም፡፡››[122]

ሳይንስም ከእምነት የሚቀጥፈው ፍሬ የሚያንስ አይደለም፡፡ እርሱም ዲን የሳይንስን ጉድለት ይሞላል፡፡ ሳይንስ ለሰው ልጅ ሊያሳውቀውና ሊተረጉምለት የሚመክረውን ከቁሳዊው ፍጥረተ-ዓለም ጀርባ ያለውን ድብቅ ዓለም የዕይታ አድማስ ያሰፋለታል፡፡ ይህን በሳይንስና እምነት መሃል ያለውን የጋራ ጥቅምና ሰናይ ፍሬውን ለማሳካት የድራዝ ሐሳብ ‹‹የእምነቶች ግዴታ ሳይንስን ማቀፍ እንጂ መወርወር ካልሆነ፤ ለኛ መልካም የሚሆነው የሰውን ልጅ አጠቃላይ ዕውቀቶች ፍሬያማ አድርገን መታጠቃችን ነው፡፡ ለሳይንስም የሚሻለው በውስጡ ያለውን ክፍተት በመንፈሳዊ እውነታዎች እምነት ይሞላለት ዘንድ መስኩን መተው ነው፡፡

ሳይንስ ይህን ማድረግ የማይችል ከሆነ፣ ገለልተኛ መሆኑ የተሻለና እምነትን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ከማድረግ እንዲሁም ከመጥላት መቆጠቡ ትንሹ

---

121 ያለፈው ምንጭ

122 ያለፈው ምንጭ

ግዴታው ይሆናል፡፡ በድፍኑ እምነትን ውድቅ ማድረግ ሁሉም እምነቶች በውስጣቸው የያዙትን ተጨባጭ ጉዳዮች ግን ሳይንስ ስላልደረሰበት በሚል በሙሉ ውድቅ ከማድረግ የሚቆጠር ነው፡፡ «አዋጅ ያ ለላዕላዩ እውነታ ብቻ የሚገባ የማመን፣ የመቀደስና የማምለክ ተግባር ነው፡፡»[123]

እምነት የለሽ የተፈጥሮ ሳይንስ ሰዎች የማሰብ አድማሳቸው የተዘጋ ነው፡፡ ምክንያቱም እነርሱ «ለዚህ ለተፈጥሮ ሳይንስ ያላቸው ታማኝነት ድንበሯን አልፈው ዓይናቸው የማያውቀውን ጉዳይ ፈልጎ ማየትን ግን እምቢ አላቸው፡፡»[124]

ወንድሜ አንተ ከሚገረሙት ውስጥ ከሆንክ ወደ መኃይምነት በሚመራ ዕውቀት ተገረም፡፡ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ባለቤቱን የሚያደናብር ብርሃን!!!

---

[123] ድራዝ፣ አድ-ዲን ገፅ 70

[124] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዓዚም ገፅ 69

## አይቀሬ እድል እና ምርጫ

ሁሉም ሰማያዊ እምነቶች የሰውን ልጅ ክብር በማውሳት መርህ፣ ከገባበት አዙሪቱ ይወጣ ዘንድ በማስታወስና ራሱን እንዲሁም ተጨባጩን በመቀየር መሰረት ላይ የተጠነሰሱ ናቸው፡፡ ልክ እንደዚሁ «እምነቶች በሁሉም ቅርፃቸው በተስፋ እና ዕድል፣ በነፃነትና የምርጫ መርህ ማዕዘናት ላይም የቆሙ ናቸው፡፡»[125]

የሰውን ልጅ ከጥልቅ መንፈሱ የሚጠራው ይህ መለኮታዊ ድምጽ በሰማያዊ እምነቶች ውስጥ ቅርፅ ይይዛል፡፡ የሰውን ልጅ «ተፈጥሮውን ያሟላ ዘንድ ይቀሰቅሰዋል፣ ዙሪያው ባሉ ነገሮች ተብቃቅቶ መቀመጡን ጅማሬና መቋጫ ላይ ብቻ ማተኮሩን ይኮንንበታል፡፡»[126]

እምነት የሰውን ልጅ ተጠያቂነትንና ኃላፊነትን ያስተምረዋል፡፡ ኃላፊነት ደግሞ ነፃነትን ይጠይቃል፡፡ ሆኖም ግን «የነፃነትን ችግር ከድሮም ጀምሮ ተቃርኗቸው እጅግ የተራራቁ በሆኑ ሁለት ዕይታዎች በትንሹ ንፁህ መስክ ላይ ቀስቅሷቸዋል፡፡ ቁርጠኝነትንና ተቃራኒውን፡፡»[127]

ሰማያዊ እምነቶች የፈጣሪን (ሱወ) ችሎታና በዕውቀቱ እንዲሁም ቻይነቱ ሁሉንም ነገራት አካባቢነቱን፤ የሰው ልጅ ነፃነቱንና በስራዎቹም ተጠያቂነቱን ትኩረት ከመስጠት ጋር አፅድቀዋል፡፡ በነዚህ በፈጣሪ በማመን እና በተፈጣሪ ተጠያቂነት መሃል የተመሰረቱ መርሆችን በምን መልኩ ማስታረቅ ይቻላል ?

በዘመናት ውስጥ የሰውን ልጅ ፍልስፍናዊና ስነ-ምግባራዊ አዕምሮውን ያነወዙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የሙስሊምን አዕምሮ ያደነዘዘ፣ በኢስላም ውስጥም የተለያዩ ኑፋቄዎችንና የአስተሳሰብ መስመሮችን የፈለፈለ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ ድራዝ «ዱስቱሩል አኽላቅ ፊል ቁርአን» በተሰኘው መፅሐፋቸው ውስጥ ስነ-

---

125 ድራዝ፣ አድ-ዲን ገፅ 43

126 ያለፈው ምንጭ

127 ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ 181

ምግባርን ከግዴታ፣ ኃላፊነትና ምንዳ አንፃር ከግምት በማስገባት ብዙ ክፍሎች ላይ ዳስሰውታል፡፡ ሁሉም ጉዳዮች ከዕድልና ምርጫ ጋር የጠበቀ ትስስር አላቸው፡፡

የሞራል ግዴታዎች በኃይል የሚያዙ መሆን እንደሌለባቸው ጠቅሰው ግን ደግሞ እንደዚያ ከሆኑ «ስነ-ምግባራዊ መገለጫውን ይሰለባል፡፡»[128] በማለት ይገልፃሉ፡፡

አንድ ተግባርም ስነ-ምግባራዊ ነው ተብሎ ለመገለፅ ሰውየው ዘንድ የመተግበርም ይሁን የመተው ምርጫው ሲኖረው ነው፡፡ ነገርግን የሰው ልጅ በመስራትና መተው በእውነቱ ነፃ ነውን ?

የእርሱን ባህሪና አካሄድ መስመር አስይዘው፣ አስገድደው በሚወስኑለት የአካላዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች የተከበበ አይደለምን ?

እዚህ ላይ ፈላስፋዎችና የስነ-ምግባር ሰዎች በሁለት ዋና ዋና መንገድ የተከፈሉ ሲሆን እነርሱም የዕድል (ውሳኔ) እና ምርጫ የእሳቤ መንገዶች ናቸው፡፡

የተወሰነ ዕድል (የግዴታ) እሳቤ መንገድ ተከታዮች እንደሚሉት ከሆነ የሰው ልጅ ራሱን አታሎ መተናነስ እንጂ ነፃነት ያለው ፍጡር አይደለም ባዮች ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ ፈላስፋው ዴቪድ ሂዩም «የነፃነት ስሜታችን የማይጨበጥ ህልም እንጂ ሌላ አይደለም፡፡»[129] እስከማለት ደርሷል፡፡

ድራዝ የዚህን እሳቤ ተከታዮች «አይቀሬያውያን» በማለት ሰይመዋቸዋል፡፡ የአይቀሬያውያን ችግር የሰው ልጅ ፍጥረት ወጥነትና ግትርነት አለው ብለው ማመናቸው ነው፡፡ «አይቀሬያውኑ የአፈጣጠርን ተፈጥሮ ምንም ዓይነት ልዝብነትና ተለዋዋጭነትን ያላቀፈ፣ ጥግ ድረስ ግትር እንደሆነ አድርገው ያቀርቡልናል፡፡

---

[128] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 24

[129] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 182

ስንወለድ አብረው የመጡ የመልካም ወይም እኩይ የዝንባሌ የተፈጥሯችን ይዘቶች ናቸው፡፡ የእኛ የእጅ ስራ ባልሆኑ ተፈጥሮዎች እንዴት ተጠያቂዎች እንሆናለን? »ይላሉ፡፡[130]

እነርሱ በዚህ ሁኔታ የሰውንም ልጅ ከእንስሳት ጋር በስሜታዊና በአዕምሯዊ ሕይወቱ ያነፃፅሩታል፡፡ እንስሳ እንደሚታወቀው በአብዛሃኛው ጊዜ ከግላዊ ስሜት አድማስ የዘለለ አይደለም፡፡ ይህን ንፅፅር አስመልክቶ ፈላስፋው ሾፑንሀውር እንደገለፀው «ጥሩ ሰዎች እንዳሉት ሁሉ ሌሎች ደግሞ እኩያንም አሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ የተወለዱት በሰውኛ ስሜትና ቁመና ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በእኔነት ስሜት ነው፡፡»ይላል፡፡[131]

የምርጫ እሳቤ መንገድ ተከታዮች ደግሞ የሰው ልጅ የተሟላ የነፃነት ባለቤት እንደሆነ ያስባሉ፡፡ አላህ (ሱወ) ለርሱ ላሸከመው ኃላፊነት ብቁ ይሆን ዘንድ በዚህ መገለጫ ብቃት ነው የፈጠረው ይላሉ፡፡ የሰው ልጅ በነፃ የመምረጥ ነፃነት አቀንቃኞች «የማስፈፀም ነፃነት»ን ማለታቸው ሳይሆን እርሱ አንፃራዊ በጊዜና ቦታ የተወሰነ ስለሆነ ማለት የፈለጉት «የመወሰንን ነፃነት» ሲሆን ያለ ግዳጅ ስነ-ምግባራዊ ምርጫን ነው፡፡»[132]

የመጀመሪያው የኢስላም ትውልድ አባላት በግዳጅ (ዕድል) እና ምርጫ ክርክር ላይ ብቻ አልቆሙም፡፡ «ምክንያታዊም ጠቃሚም አይደለም፡፡»[133] ብለው ነበር ያሰቡት፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ ሁሉም ሙስሊሞች የሰው ልጅ ስለ ተግባራቱ ተጠያቂነት እንዳለበት ተስማምተዋል፡፡ ነገርግን ከሁለተኛው ክፍለዘመን መባቻ ጀምሮ፣ ባለፉ እምነቶችና በጥንታዊ ፍልስፍናዎች ውስጥ የተራረፉ ቀሪ ክርክሮች ወደ ኢስላማዊው አስተሳሰብ መስከ መሻገር ነው ለዚህ ጉዳይ መከሰትና የሐሳብ መንገዶች ቅርንጫፍ መብዛትን ያስከተለው፡፡

---

130 ያለፈው ምንጭ

131 ያለፈው ምንጭ

132 ድራዝ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፕ 182

133 ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 219

ፈገግ ከሚያስብሉ ነገሮች ውስጥ በነፃነትና ተጠያቂነት ጉዳይ የጠበቀ ንትርክ ከሚያደርጉት ቡድኖች ውስጥ «አል-ቀደሪያ» የሚለውን አንድ ዓይነት ስም የያዙ ግን ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ የሆነ የትርጉም ይዘት ያላቸውም ነበሩ፡፡ ከዚህ በኋላ በነበረው ጊዜ ግን የአንዱ ስያሜ ሙዕተዚላ የሌላው ደግሞ ጀህሚያ ሆነ፡፡

የሙዕተዚላ ቡድን የምርጫ እሳቤ መንገድን በመስራቹ ዋሲል ቢን ዐጧእ በኩል እንዲህ በማለት ገልጧል ፡-«በየትኛውም ጉዳይ የሰው ልጅ የተሰጠውን ችሎታና የማድረግ ብቃት በርግጠኝነት አላህ ምን ላይ ሊያውለው እንደሚችል ያውቀዋል፡፡ ከዚህ ጋር ግን እርሱን ከሙሉ ኃላፊነት መውሰድና ተጠያቂነት ጋር ያሻውን ይሰራ ዘንድ ይተወዋል፡፡» [134] ይላል፡፡

ዋሲል ከቀደመ መለኮታዊ ዕውቀት ግንዛቤ ጋር በሸሪዓዊ አናቅፅ የመጣውን የቀደርን ግንዛቤ በዚህ መልኩ ያመሳስለዋል፡፡ ወይም የሰውን ልጅ ተግባር በቁጥጥር ማዕቀፍ ውስጥ ከሚገድበው የተፈጥሮ ህግ ጋር ሲያጋምድ ግን ደግሞ ነፃነትና ፍላጎቱን ከማይነጥቀው ግንዛቤ ጋርም ያስተሳስረዋል፡፡

ጀህሚያ ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ መንገድ ስለ «ፍፁምና ቁርጥ ያለ ውሳኔ» ነው የሚናገረው፡፡ ከስሙ ስያሜዋን ያገኘቺው ይህቺ ቡድን መስራቿ ጀህም ቢን ሰፍዋን ሲሆን «ላይ ላዩን ካልሆነ በስተቀር በፈቃደኝነት የሚደረግ ተግባር፣ ካለ ፈቃድ ከሚሰራው ጋር ልዩነት የለውም፡፡ ያም የሆነበት ምክንያት የሰው ልጅ በዝቅተኛ እንቅስቃሴ አንኳ ለማድረግ ስለማይችል ነው፡፡ እርሱ በአላህ ፍላጎት ውስጥ በንፋስ እንደሚውረገረግ ላባ ቢጤ ነው፡፡»[135] ብሎ ያምናል፡፡

በዕድል እና ምርጫ ዙሪያ ያለው ክርክር ከርሱ በገዘፈና ጥልቀት ካለው ሌላ ክርክር የተመዘዘ ሲሆን እርሱም የመለኮታዊ ባህሪያት አርጊዩመንት ናቸው፡፡

---

[134] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ 208

[135] ድራዝ፣ ዱስቱሩል-አኽላቅ ገፅ 208

በሁለቱ መሃል ያለው የልዩነት መቅኒው መለኮታዊ ችሎታን ወይም ፍትህን ካለመቀበልና ካለማረጋገጥ የመነጨ ነው፡፡ የፍትሐዊነት ባህሪውን ወደ ጎን ብለው የችሎታ ባህሪው ላይ ብቻ ትኩረት የሰጡት የዕድል (ግዳጅ) ጎዳናን ሲጓዙ፤ የችሎታ ባህሪውን ደግሞ ተወት አድርገው የፍትሐዊነቱ ባህሪ ላይ ብቻ ያተኮሩት የነፃነትና ምርጫ ጎዳናን ተከትለዋል፡፡

ሁለቱም አባባሎች አንዱን መለኮታዊ ባህሪ በሌላው ላይ በማስበለጣቸው ድንበር ጥሰው የወጡ አደረጋቸው፡፡ በመሰረቱ አንድ አሐዳዊ የሆነ አማኝ ይህንን ጉዳይ ለሁለት ከፍሎ ማየት አይኖርበትም፡፡ ይልቁንም እያንዳንዱን እንደ አንድ አካል አድርጎ መያዝ ይጠበቅበታል፡፡ የግዳጅ (አቀሬያውያኑ) ጎዳና ግን ገና ከመሰረቱ ጥልቀት ባለባቸው ድክመቶች የሚሰቃይ ነው፡፡

ከነርሱ ውስጥ አንዱ የሳይንሳዊ ድክመት ነጥብ ሲሆን «የንፅፅር ሳይኮሎጂ እንዳረጋገጠው ከሆነ በተቃራኒ አቅጣጫ የሰው ልጅ ስሜት ከእንስሳቱ በተለየ መልኩ ሲበዛ ውስብስብ ስለሆነ በጣም ዝቅተኛ የፅናት ይዞታ ሲኖረው፤ ለመለወጥና ለመታነፅ ምቹና ተጣጣፊ ነው፡፡»[136]

የስነ-ምግባር ድክመት ነጥቡ ደግሞ «አስገዳጅ» የሚለው ቃል የማንኛውንም ስነ-ምግባራዊ ግዴታዎች መሰረት የሚንድ፣ የኃይልንና የጫካ ህግ አመክንዮ መስፈንን በር ከፋች ነው፡፡

ለሁለቱም ቡድኖች በተለይ ለሙዕተዚላዎቹ መልስ ለመስጠት አሽዓሪዎች ቀድመው ተነሱ፡፡ «ከስብ» (የእጅ ስራ ውጤት) በሚል ዕይታቸው ውስጥ «በአንድ ተግባር ላይ የመለኮታዊና ሰዋዊ ፍላጎቶች መጋራት» ወደሚል ድምዳሜ ላይ ደረሱ፡፡ ሆኖም ግን ከፊል አሽዓሪዮች አልፎ አልፎ ከሙዕተዚላዎች ጋር በሚያደርጉት የተካረረ ክርክር ንትርክ ውስጥ ገብተዋል፡፡ ድንበር ማለፍን በራሱ መሳይ ድንበር ማለፍ ለማከም ሞከሩ፡፡

---

[136] ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 184

በድራዝ አረዳድ አሸዓሪዎቹ ከሙዕተዚላዎቹ ከአስተያየት አሰጣጥ ተጣጥሞሻቸውና ድንበር ማለፍ «ስር የያዘና የተረጋጋ የፍልስፍና መሰረት ሊኖራቸው አልቻለም፡፡»[137]

ሆኖም ግን በሁሉም የእሳቤ መስመሮች ውስጥ ያለው ትልቁ ኪሳራ ለዚህ ፍልስፍናዊና ስነ-ምግባራዊ ችግር ጠንካራ የሆነ የቁርአናዊ መፍትሄ የማግኘት ምርምር አለመደረጉ ነው፡፡ ለዚህ ሐሳብ እሳቤያቸውን ከቁርአን እና ሸሪዓዊ አናቅፅ የገነቡት ድራዝ ለጉዳዩ ልዩ ይዘት ወዳለው ድምዳሜ ደርሰዋል፡፡ በርሳቸው እሳቤ ጉዳዩን ለሁለት ከፋፍሎ ማየት ፈፅሞ አይበጅም፡፡ ምክንያቱም ቁርአን የነፃነትንም የተጠያቂነትንም፣ የመምረጥንም የዕድልንም የፍትህንም የመቻልንም ግንዛቤዎች አንድ ላይ በራሱ አሰዳደር ሰብስቦ ይዟቸዋል፡፡ ልክ እንደዚህ «ቁርአን አላህ ፊት ተጠያቂነታችንን ባወጀበት አንቀፅ ላይ ሰዋዊና መለኮታዊ ፍላጎቶችን በተሟላ መልኩ አጣምሮ በያዘ ሁኔታ ሲገልፅ እናገኘዋለን፡፡

يُضِلُّ مَن يَشَاءُ وَيَهْدِي مَن يَشَاءُ ۚ وَلَتُسْأَلُنَّ عَمَّا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ

«የሚሻውን ሰው ያጠማል፡፡ የሚሻውንም ሰው ያቀናል፡፡ ትሠሩት ከነበራችሁትም ሁሉ በእርግጥ ትጠየቃላችሁ፡፡» (ነህል 96)[138]

ስለዚህ በመጀመሪያ ዕይታ ተቃራኒ በሚመስሉ ሐሳቦች የፍትሐዊነትንም ይሁን የችሎታን ባህሪ ግንዛቤ ውድቅ የሚያደርግ መፍትሄ ላይ መድረስ በፍፁም መቅረት አለበት፡፡ አንዱንም ሳይዘነጋ ተጣራሽ ባህሪያትን አጣጥሞ አንዱ ላይ ድንበር ሳያልፍና ሌላው ላይ ደግሞ ሳይተማመን እውነተኛና ገንቢ ወደሆነ ቁርአናዊ መፍትሄ መድረስ ግዴታ ነው፡፡»[139] ይላሉ፡፡

---

[137] ያለፈው ምንጭ

[138] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 221

[139] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 67

ድራዝ የሚያቀርቡት የተለየና ሚዛናዊው መቋጫ መፍትሄ የሚሆነው የአላህን (ሱወ) ችሎታ አረጋጋጭ የሆኑ አናቅፅ የታሰሩ ናቸው፡፡ ቁርአን እንደሚያስተምረን

اللَّهَ يَحْكُمُ مَا يُرِيدُ

‹‹አላህ የሚሻውን ይፈርዳል፡፡›› (ማኢዳ 1) ነገርግን

وَاللَّهُ يَقْضِي بِالْحَقِّ

አላህም በእውነት ይፈርዳል፡፡ (ጋፊር 20) በሚለው ይለየዋል፡፡

ቁርአን

عَذَابِي أُصِيبُ بِهِ مَنْ أَشَاءُ

ቅጣቴ በእርሱ የምሻውን ሰው እቀጣበታለሁ፡፡ (አል-አዕራፍ 156) ሲያውጅ ግን ደግሞ

مَّا يَفْعَلُ اللَّهُ بِعَذَابِكُمْ إِن شَكَرْتُمْ وَآمَنتُمْ ۚ وَكَانَ اللَّهُ شَاكِرًا عَلِيمًا

‹‹ብታመሰግኑና ብታምኑ አላህ እናንተን በመቅጣት ምን ያደርጋል= አላህም ወረታን መላሽ ዐዋቂ ነው፡፡ (ኒሳእ 147) በሚለው ይነጥለዋል፡፡

ቁርአን

يُضِلُّ بِهِ كَثِيرًا

‹‹በርሱ (በምሳሌው) ብዙዎችን ያሳስታል›› ብሎ ሲያረጋግጥ

وَمَا يُضِلُّ بِهِ إِلَّا الْفَاسِقِينَ

«በርሱም አመፀኞችን እንጅ ሌላን አያሳስትም፡፡» (በቀራ 26) ሲል ደግሞ በዚያው አንቀጽ ይለየዋል፡፡

በነዚህ ሶስት ምሳሌዎች ውስጥ የመጀመሪያው አንቀፅ ጠቅላይ ሆኖ ያለ ምንም ገደብ ልቅ ችሎታን አመላካች ሲሆኑ፤ ሁለተኛው አንቀፅ ደግሞ የችሎታን ትርጉም በፍትሕ ትርጉም ለይቶ ሲያስረው እናያለን፡፡ ይህ ችሎታና ፍትሕ፣ በጥቅልና ልዩው መሃል አዋህዶ መገንዘብ በቁርአን አናቅፅ መሃል አጣጥመን እንድሄድ ያስችለናል፡፡ በተጨማሪም በመገደድና በምርጫ ጉዳይ መሃል ልዩና ሚዛናዊ የሆነ መፍትሄ ይዘን እንወጣ ዘንድም ያግዘናል፡፡ ከፊል ተናጋሪዎች የ«ዕድል» (ግዴታ የሚፈፀሙ) ጋር የመደቧቸው የቁርአን አናቅፅ «በመስፈርት የታጠሩ» ናቸው፡፡ ከዚያ አመክንዮ ርቀው ግን አጠቃላይና ልቅ ክስተቶች ላይ መጣል አይገባቸውም፡፡

ይህን አስመልክቶ ድራዝ «(ቁርአን) አላህ (ሱወ) ሰዎች በአጠቃላይ መልካሞቹንም ይሁን እኩዮቹን ማጥፋት እንደሚችል ሲያውጅ

فَمَن يَمْلِكُ مِنَ اللَّهِ شَيْئًا إِنْ أَرَادَ أَن يُهْلِكَ الْمَسِيحَ ابْنَ مَرْيَمَ وَأُمَّهُ وَمَن فِي الْأَرْضِ جَمِيعًا

‹የመርየምን ልጅ አል-መሲሕን እናቱንም በምድር ያለንም ሁሉ ለማጥፋት ቢሻ ከአላህ ማዳንን የሚችል ማነው፡፡› (ማኢዳ 17) ወይም በዚህ ፍጥረተ-ዓለም ውስጥ በኛ ላይ ግድ የሆኑና የተፈተንባቸው ከባድና ውስብስበ ኹነቶችን በተቃራኒ መምጣት አይችልም፡፡

وَلَوْ شَاءَ اللَّهُ لَأَعْنَتَكُمْ

«አላህም በሻ ኖሮ ባስቸገራችሁ ነበር፤» (በቀራ 220) ታዲያ እነዚህ በመስፈርት የታጠሩ ቅርፆች እንዲሁ ወደ አሁን ክስተትነት» መቀየር እንደማይቻሉ አመላካች አይደሉምን?[140]

እዚህ ላይ የድራዝ አስተያየት ውድ ዋጋ ያለው ነው፡፡ ኢስላም ውስጥ በደንብ እንደሚታወቀው አላህ (ሱወ) ነቢ ዒሳን እና እናቱን (ዐሰ) አላጠፋቸውም፡፡

ነገርግን አንቀፁ የወረደው ልኬት የለሹን የመለኮታዊ ችሎታ ባህሪን ለማረጋገጥና ለማሳየት ነው፡፡ ለዚህም በአንቀፁ መቋጫ ላይ

وَلِلَّهِ مُلْكُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا ۚ يَخْلُقُ مَا يَشَاءُ ۚ وَاللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ

«የሰማያትና የምድር የመካከላቸውም ንግሥና የአላህ ብቻ ነው፡፡ የሚሻውን ይፈጥራል፡፡ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡» (ማኢዳ 17) የሚል መጥቷል፡፡ በሐሳብ ደረጃ የችሎታ ባህሪ ዒሳንም ይሁን እናቱን ማጥፋት እንደሚችል ካመላከተ በኋላ፣ ግን አላህ (ሱወ) ያመኑ ባሪያዎቹን በዚህ የሚያስፈራራ ከሆነ፤በተግባር ግን ይህ እንዳይከሰት የፍትሕና ጥበብ ባህሪያቱ ይከለክሉታል፡፡ እርሱ (አላህ) እውነተኞችን ከማጥፋትና ትጉሃንን ከማስጨነቅ ከፍ ያለ፣ ሲበዛ ፍትሐዊ፣ ጠቢብና ወዳጅ አምላክ ነው፡፡

ድራዝ የሰበሰቧቸውን ቁርአናዊ አናቅፅ እና የማብራሪያቸውን የቅደም ተከተላዊነት (መስፈርታዊነት) መቋጫ ደግሞ እነሆ ፡-«በዚህ ዘርፍ ቅደም ተከተላዊ መሆናችን ምንም አያጠራጥርም፡፡ ቁርአን ራሱ የመስፈርታዊነትን መርህ

إِنَّ اللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوْمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُوا مَا بِأَنفُسِهِمْ

[140] ያለፈው ምንጭ

አላህ በሕዝቦች ዘንድ ያለውን በነፍሶቻቸው ያለውን (ኹኔታ) እስከሚለውጡ ድረስ አይለውጥም፡፡ (ረዕድ 11) በማለት ያቀርብልናል፡፡

ስለዚህ ነገሩን አላህ (ሱወ) በኛ ፍላጎት ላይ ተጭኖ የሚበይንብን እርሱ ነው ብለን ስንደመድም የመስኩ ጥናታችንን ልቀት ያደበዝዘዋል፡፡ ምክንያቱም ሲጀምር አላህ (ሱወ) አያደርግም፡፡ ይልቁንም እንደተጓዳኝ እርምጃና አሰራር ዓይነት ሆኖ እንዲሄድ ያደርገው ይሆናል፡፡ እነዚህ ሁሉ ተፅዕኖዎች ከተፈጥሮ በላይ ከሆነ ላዕላይ ኃይል በጣልቃ ገብነት በኩል እንደሚመጡ ስናውቅ፤ የቀደመቺው ግን ከፍላጎታችን የመነጨች ናት፡፡ ወደ ብርሃን መቅጣጨትን የጀመርነውም ጀርባም የሰጠነው እኛው ነን፡፡

وَمَن يَعْشُ عَن ذِكْرِ الرَّحْمَٰنِ نُقَيِّضْ لَهُ شَيْطَانًا فَهُوَ لَهُ قَرِينٌ

«ከአል-ረሕማን ግሣጼ (ከቁርኣን) የሚደናበርም ሰው ለእርሱ ሰይጣንን እናስጠጋለን፡፡ ስለዚህ እርሱ ለእርሱ ቁራኛ ነው፡፡» (ዙኽሩፍ 36)

አዕምሯችንን በወጋገን የምንሞላውም ይሁን የምናጸልመው እኛ ነን፡፡

كَلَّا ۖ بَلْ ۜ رَانَ عَلَىٰ قُلُوبِهِم مَّا كَانُوا يَكْسِبُونَ

«ይከልከል፤ ይልቁንም በልቦቻቸው ላይ ይሠሩት የነበሩት (ኀጢአት) ደገደገባቸው፡፡» (አል-ሙጦፊፊን 12)

ስሜታችንን ተቆጣጥረናል ወይም ተከትለነዋል፡፡

وَلَوْ شِئْنَا لَرَفَعْنَاهُ بِهَا وَلَٰكِنَّهُ أَخْلَدَ إِلَى الْأَرْضِ وَاتَّبَعَ هَوَاهُ

«በሻንም ኖሮ በእርሷ ከፍ ባደረግነው ነበር፡፡ እርሱ ግን ወደ ምድር ተዘነበለ፡፡ ፍላጎቱንም ተከተለ፡፡» (አል-አዕራፍ 176) [141]

---

[141] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ ገፅ 212

ቁርአን ውስጥ ያሉ የፍትሐዊነትን እና ችሎታን አመላካች አናቅፅ ስብጥር ጠቅለል ስናደርጋቸው መሰረታዊው ጉዳይ የሰው ልጅ ለነፍሱ የሻውን የመወሰን ነፃነት እንዳለው ነው፡፡ ከዚህች ነፃነት ውጪ ስነ-ምግባራዊ ተጠያቂነት ትርጉም አይኖረውም፡፡ ሆኖም ግን መለኮታዊው ችሎታ የሰው ልጅ በመረጠው እውነትና ፍትሕን ለመረጠ ለማፅናትና ለማረጋገጥ እንዲሁም በደልና ጥፋትን ለመረጠ ደግሞ ለማሳነስ ጣልቃ ይገባል፡፡ በዚህ ትርጉም መሰረት ቀደር ምድር ላይ ፈጣን የክፍያ ዓይነት ነው፡፡ ድራዝ ከላይ ካሰፈሩት በተጨማሪ ይህን ትርጉም ያዘለ ቁርአናዊ አንቀፅ

وَيَزِيدُ اللَّهُ الَّذِينَ اهْتَدَوْا هُدًى

«እነዚያንም የቀኑትን ሰዎች አላህ ቅንነትን ይጨምርላቸዋል፡፡» (መርየም 76) እና

وَنَذَرُهُمْ فِي طُغْيَانِهِمْ يَعْمَهُونَ

«በጥመታቸውም ውስጥ የሚዋልሉ ሲኾኑ እንተዋቸዋለን፡፡» (አንዓም 110) የሚል እናገኛለን፡፡ መሰል አናቅጽ ቁርአን ውስጥ ብዙ ናቸው፡፡

በሐሳብ ደረጃ አላህ (ሱወ) ሌሎች ብዙ ፍጡራንን በተፈጥሮ ህግ መሰረት በግዳጅ እንደመፍጠሩ ሰውንም በዚያው ህግ ቢፈጥረውም፤ በገቢር ደረጃ ግን አይደለም፡፡ ይልቁንም ስለ ተግባራቱ ተጠያቂና ነፃ አድርጎ ነው የፈጠረው፡፡ የግዳጅና ችሎታ አናቅፅን በመስፈርት ከታሰሩ ትርጉሞች ጋር መመደብ ግድ ይላል፡፡ የፍትሕና ነጻነት አናቅፅን ደግሞ በሕይወት ውስጥ ከሚሳኩና ገቢራዊ ትርጉሞች ጋር ማቆራኘት ያሻል፡፡ ያኔ ነገራት ይገጣጠማሉ፣ ችግሩም ይወገዳል፡፡

## ሱና እና ቢድዓ

ከአላህ (ሱወ) ለሰው ልጅ የእዝነት መገለጫዎች ውስጥ መደምደሚያውን መልዕክት (ሪሳላ) ንፅህናውንና ፅዳቱን በአስተማማኝ ሁኔታ እንደጠበቀ ይቆይ ዘንድ በተለያዩ መጠበቂያ መንገዶች ጥብቅ ማድረጉ፤ እስከ ዝንተ-ዓለሙም ፍጡርን በተመለከተ የፈጣሪ መረጃ ሆኖ መቆየቱ አንዱ ነው፡፡

ኢስላማዊውን መልዕክት ከመጠበቂያ መንገዶች ውስጥ በኢስላማዊው የዕውቀት ባህል ስነዳ ውስጥ በሱና እና ቢድዓ መሃል ግልፅ የሆኑ መለያዎች አዕማዶች መኖራቸው ነው፡፡ ግልፅ ይሆን ዘንድ የኢስላም ሊቃውንት ከፍተኛ ጥረትና ትጋት አድርገዋል፡፡ የቀደሙት ሰማያዊ እምነቶች ግን ታሪካቸው እንደሚያሳየው ከሆነ በዋናው መልዕክትና በሃይማኖተኞች በተቀጣጠፉ እንዲሁም በተፈጣጠሩ መጤ እሳቤዎች መሃል አስደንጋጭ የሆነ መደባለቅ ተፈጥሯል፡፡ በቢድዓ ገለባና በልማድ ጥርቅም የተነሳ የዋናው መልዕክት መንፈስም ጠፍቷል፡፡

ሱና የሚለው ቃል በኢስላማዊው የዕውቀት ተርሚኖሎጂ ውስጥ ትርጉምና አመላካችነቶች አሉት፡፡ በሐዲስ የጥናት ዘርፍ ሱና ሐዲስ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ማለትም የነብዩ (ሰዐወ) ተግባራት፣ ንግግሮችና ማፅደቆች ነው፡፡ በፊቅህ ደግሞ ሸሪዓዊ ድንጋጌነት ያለው፤ ግን ደግሞ አስገዳጅ ያልሆነ የሚል ይዘትም አለው፡፡ በስነ-መለኮት (ዐቂዳ) ጥናት ደግሞ በእምነትም ይሁን ተግባር ደረጃ የተስተካከለ መንገድ ማለት ነው፡፡

ዛሬ ላይ ካሉ የሱኒ መዝሃብ ተከታዮች ሚዛናዊ አቋም ከሌላቸው እሳቤ ውስጥ አንዳንዴ ራቅ የሚለው ግንዛቤ በአንገብጋቢነት ደረጃ የሕብረት (ጀመዓ) ግዴታ ከመከተል (ኢቲባዕ) ያላነሰ ዋጋ እንደሌለው ነው፡፡ ቡድንተኝነትና የሕብረትን ገመድ መበጣጠስ አስኮናኝ የሆነ ቢድዓ ነው፡፡

ቀደምት አበው ለዚህም ነበር ልከኛ የሆነውን መንገድ «መንሐጁ አህለ ሱና ወል ጀመዓ» በሚል የሰየሙት፡፡ በክቡሩ ሱና (ሐዲስ) ውስጥ እንደመጣው ከሆነ «ሱናን መተው ከጀመዓ (ሕብረት) መውጣት ነው፡፡»[142] ይላል፡፡

ሙስሊሞች ይህን ሐዲስ የዓይናችን ማረፊያ አድርገንና የተግባር ማዕከላችን ቢሆን ኖሮ ዛሬ ላይ አጥፊ የሆኑት የቡድንተኝነትና ጠርዘኝነት ንፋሶች ባልወዘወዙን ነበር፡፡ በሱና እና ቢድዓ መሃል የመለየት ችሎታ ቀላል ጉዳይ አይደለም፡፡ ብዙ ዓሊሞች ሐሳባቸው ተለያይቶበታል፡፡

ከነርሱ ውስጥ ከሸሪዓ የላቁ ግቦች አንጻርና አካቶ ውስጥ ከመነጩ ማንኛውም ስራ ላይ የአተገባበር ቅርፁ መጤ ቢሆንም አንኳ፣ ምንም ቢድዓ የለበትም ከሚለው በስፋት ተመልካች ሱፊው ጀምሮ ሱና ማለት በቀደመ የአተገባበር ታሪካዊ ቀርፅ ብቻ ያለው ነው እስከሚለው አንድ አቅጣጫ ተመልካቹ ሰለፊ ድረስ ነው፡፡ እዚህ ላይ የድራዝ ጥረት የተለየ ነው፡፡ ብዕራቸውን በመጠቀም «አል-ሚዛኑ በይነ ሱነቲ ወል ቢድዓቲ» በተሰኘው ድርሳናቸው እነዚህን ግንዛቤዎች ለመግለጽ ጥረዋል፡፡ የድርሳኑ የይዘት «አል-ኢዕቲሷም» የተሰኘው የኢማም አሽ-ሻጢቢ መፅሐፍ ቅጣይ ነው፡፡ ድራዝ በርሱ ሲበዛ ተመስጠውበታል፡፡ በተመሳሳይም በሌላው በአሽ-ሻጢቢ «ሙዋፈቃት» የተሰኘ መፅሐፍም ተማርከዋል፡፡

ድራዝ ሁለቱን ጣምራዎች መዳሰስ የጀመሩት ከሰፊ አድማስ በመነሳት ነው፡፡ ቀድመው ግንዛቤዎቹን በታሪክ አውድ ላይ አኖሩ፡፡ በመጀመሪያው የኢስላም ትውልድ ተርሚኖሎጂ መሰረት «ሐቅ» እና «ባጢል» ከሚሉት ቃላት ጋር በትንሹ የሚቀራረቡ ፅንሰ-ሐሳቦች ናቸው፡፡ «ሱና የሚለው ቃል በመጀመሪያው ትውልድ ውስጥ በሸሪዓ እውነታው ከእምነት ጉዳዮች ውስጥ እውነትንና ትክክለኛ ነገርን እንጂ አያጠቃልልም፡፡

[142] አሕመድ ኢብኑ ሐንበል ሸይባኒ፣ ሙስነድ አሕመድ 535/6

ያንንም መንገድ ያሰመሩልን የአላህ መፅሐፍና የመልዕክተኛው (ሰዐወ) ሐዲስ በአንቀፅና ማመላከቶች ማብራሪያ ነው፡፡ ቢድዓ የሚለውም ቃል በውስጡ የሚይዘው ከንቱና እርባና-ቢስ ጉዳዮችን እንጂ ነው፡፡ በአላህ (ሱወ) መጽሐፍም ይሁን በመልዕክተኛው (ሰዐወ) ሱና ውስጥ ሰነድ የሌለው ሆኖ ግን ሁለቱ ከሚያመልክቷቸው ነገሮችም ተፈልቅቆ ያልወጣ ሲሆን አዲስ የተፈጠረ ይሆናል፡፡ ውግዘቱ በተደጋጋሚ አጠቃላይና ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የመጣው ለዚህ ነው፡፡ «አዲስ የተፈጠሩ ነገሮችን አደራ (ራቁ)፡፡ ማንኛውም (በዲንና አምልኮ ውስጥ) የሚፈጠር አዲስ መጤ ነገር ሁሉ ቢድዓ ነው፡፡ ሁሉም ቢድዓ ደግሞ ጥመት ነው፡፡»[143]

ድራዝ ቀጥለው ከነብዩና ባልደረቦቻቸው ዘመን በኋላ የሁለቱን ግንዛቤዎች ዕድገት ፋና ያጤናሉ ፡-«ከመጀመሪያው ትውልድ በኋላ (በጉዳዩ ላይ) የኢስላም ልሂቃን በሁለት ጎራ የተከፈሉ ናቸው፡፡ አንደኛው ጎራ ይህንኑ ሸሪዓዊ ትርጉም ያለምንም ጭማሬና መቀነስ የተጠቀመው ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ የሱና ትርጉምን ሄዶበት ሶስተኛ ዕይታም ያመጣ ነው፡፡ እርሱም ወደ ቋንቋዊ ትርጉሙ በቀረበ መልኩ አጠቃላይና ሰፋ ወዳለ ትርጉም የቀረበ ነው፡፡

በነዚህ ሰዎች ዘንድ ሱና ማለት በነብዩ (ሰዐወ) ዘመን ሲሰራበት የነበረ ዲናዊ መስመር ሲሆን፤ ቢድዓ ደግሞ በነብያዊው ዘመን ምንም ዓይነት የቀደመ ቅርፅ የሌለው ግን በሶሐቦች ዘመንም ይሰራበት አይሰራበት ከግምት ሳይገባ ማንኛውንም አዲስ ጉዳይ በሙሉ ያጠቃለለ ነው፡፡»[144]

ከዚህ ሁሉ የግንዛቤ መሻሻል፣ በዕይታና ንድፈ-ሐሳብ ዙሪያ ገለፃ ካደረጉ በኋላ በጠባቡ የቋንቋ ገለፃም ይሁን ሌላ ሁሉም ቢድዓ ጥሜትና የተወገዘ እንዳልሆነ ያብራራሉ፡፡

---

[143] ድራዝ፣ አል-ሚዛን በይነ ሱነቲ ወል ቢድዓቲ ገፅ 43
[144] ድራዝ፣ በይነ ሱነቲ ወል ቢድዓቲ ገፅ 43

በዚህ ጉዳይ ላይ የተነሱ የዑለሞችን ልዩነቶች በመተው ሱና እና ቢድዓን በመተርጎም ሂደት ውስጥ የተወሱት (ዓይነት) የቃላት አጠቃቀም ነው፡፡»[145]

በመጀመሪያው ትውልድ ዘንድ የተሰራጨውና ሁሉም ቢድዓ ጥመት ነው የሚል ሐዲሳዊ ድጋፍ ያለውን ሙያዊ ቃል በተመለከተ «አንድ ሙስሊም በነዚህ ጉዳዮች የፀደቁትንና ያልፀደቁትን ለይቶ ያውቅ ዘንድ ከሙስሊም ሊቃውንት መያዝ (መከተልን) ችላ ማለት አይሆንለትም፡፡ ከነዚህ ውስጥ በኢብኑል ማጂሹን ዘገባ መሰረት የኢማሙ ማሊክ ንግግር ይጠቀሳል፡፡ (ኢስላም ውስጥ አንድን ነገር መልካም መስሎ ስለታየው ብቻ ከፈጠረ ሙሐመድ (ሰዐወ) የኢስላምን መልዕክት ክደዋል ብሎ እንዳሰበ ነው፡፡ ምክንያቱም አላህ (ሱወ)

الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا

«ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡» (ማኢዳ 3) ስለሚል ነው፡፡ ያኔ ዲን ያልነበረ ጉዳይ ዛሬ ላይ ፈፅሞ ዲን ሊሆን አይችልም፡፡»[146]

ከመጀመሪያው ትውልድ በኋላ የተወሰነ የግንዛቤ ለውጥን በማስፋትና መጥበብ ያጋጠመው የሱና እና ቢድዓ ቃል ፣በድራዝ ዕይታ ሁሉም ቢድዓዎች በሸሪዓ ውግዝ አይደሉም፡፡ ከዚህ ዕይታ በመነሳት «አዲስ የሚፈጠሩ ነገሮች መልካምና እኩይ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ የሚታወቅና በሸሪዓ ከግምት ክልል ውስጥ የሚገባ፣ መረጃ ያልደገፈው ሁሉ ያመጣው አካል በአሻሚና አታላይ ነገሮች ቢያሸበርቀውም ውግዝ ቢድዓ ነው፡፡

---

145 ድራዝ፣ አል-ሚዛን 43

146 ድራዝ፣ አል-ሚዛን ገፅ 44

ከቁርአንና ሱና ወይም ኢጅማዕ በኩል በቂያስ ድጋፍ ያለው ሁሉ አሊያ ኪታብና ሱና ከሚያመለክቱት በኩል ከታገዘ ምንም አንኳ በነብያዊው ጊዜ የተገኘ ባይሆንም መልካም ነው፡፡»[147]

በዚህ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ቀደምት ሊቃውንት ብዙ ብለዋል፡፡ ከነርሱ ውስጥ ከኢማሙ አሽ-ሻፊዒ (ረዐ) የሚከተለው ተገኝቷል፡፡ «አዲስ ነገሮች ሁለት ዓይነት ናቸው፡፡ አንደኛው ዓይነት ቁርአንን፣ ሐዲስን አሰርንና ኢጅማዕን ተጣርሶ የተፈጠረ ሲሆን ይህ ዓይነቱ ጠማማ ቢድዓ ሲሆን፤ እነዚህን ሳይቃረን ደግሞ የተፈጠረ አዲስ ነገር ምስጉን ቢድዓ ነው ይባላል፡፡»[148]

ከርሳቸው በተገኘ ሌላ ንግግራቸው ደግሞ «ቢድዓ ሁለት ዓይነት ነው፡፡ ምስጉን እና ውግዝ ይባላሉ፡፡ ከሱና ጋር የገጠመው ምስጉን ሲሆን የተጣረሰው ደግሞ ውግዝ ነው፡፡»[149]

ዒዘዲን ኢብን ዐብዱሰላም (በ660 ነው የሞቱት)፣ ሺሐቡዲን አል- ቀራፊ (684 ነው የሞቱት) እና መሰል ሊቃውንትም የሻፊዒን የሐሳብ ፈትሎችን ነጣጥሎና ለይቶ የማየት መንገድን ተከትለው አስፍተው ቃኝተውታል፡፡ ሌላው ቀርቶ ቢድዓን እስከ አምስት ዓይነት ከፋፍለውታል፡፡ ለምሳሌ

- (በወቅቱ) ቁርአንን መሰብሰብ የግዴታ ቢድዓ
- ሶላት አት-ተራዊህ ሱና የሆነ ቢድዓ
- የመመገቢያ ማዕድ ላይ ብዙ ዓይነት ምግቦችን መመገብ የሚፈቀድ ቢድዓ
- መስጂድን ከመጠን ባለፈ ሁኔታ ማስዋብ የሚጠላ ቢድዓ እና
- ምናኔ (ዓለም በቃኝ ማለት) ሐራም የሆነ ቢድዓ በማለት ከምሳሌዎች ጋር አስቀምጠዋቸዋል፡፡[150]

---

[147] ድራዝ፣ አል-ሚዛን ገጽ 45

[148] በይሃቂ በሻፊዒ መናቂብ ላይ የጠቀሱት፣ የሶሒሕ አል-ቡኻሪ ሸርሕ በሆነው ፈትሑል-ባሪ ላይ ሰነዱን ኢብኑ ሐጀር ሰሒሕ ያሉት ነው፡፡

[149]አቡ ነዒም አል-አስፈሃኒ በሒልየቱል አውሊያእ ወጦበቃቱል አስፊያእ ላይ ዘግበውታል፡፡

ቢድዓን በተመለከተ በአስፌና አጥባቢ የአስተሳሰብ ትምህርት ቤቶች መሃል ያለው ልዩነት በውስጣዊ ይዘቱ በድራዝ ዕይታ የቃላት ነው፡፡[151] በጽንሰ-ሐሳቡና ብያኔው ላይ ግን ልዩነቱ ቀጥሏል፡፡[152] ድራዝ ማንኛውንም ከሸሪዓ ጋር የተጣረሰ ሁሉ ቢድዓ ነው ብለው አያምኑም፡፡ «እነዚህን መጣረሶች ግን እምነት አድርጎ መያዙ ነው ቢድዓ የሚባለው፡፡»[153]

«አንድን አመጽ በእምነት ቅኝት ዳስሶ ወደ ሸሪዓ አጥር ጊቢ ያስገባ ሰው በርግጥ በዲን ውስጥ ቢድዓ ሰርቷል፡፡ ምንም እንኳን ስራው ከመሰረቱ ሐራም ወይም የሚጠላ ባይሆንም የሸሪዓን ከባቢ እስከመቀየር የሚያደርስ ከሆነ ቢድዓ ነው፡፡ ለምሳሌ ሙባሕ የሆነን ለመቃረቢያነት፣ ቁርባውን ወደ መንዱብነት አሊያ ተቃራኒውን ዋጂብ አድርጎ መቀየርን የመሰሉት ይጠቀሳሉ»[154]

በቢድዓና ኃጢአት መሃል በልቁ ጥቅልና ልዩ የሆኑ ልዩነቶች እንዳሉ ኡሱሊዮች ይናገራሉ፡፡ ማንኛውም ቢድዓ ወንጀል ቢሆንም፣ ሁሉም ወንጀል ግን ቢድዓ አይደለም፡፡ ድራዝ በሁለቱ ግንዛቤዎች መሃል «ስሜቱን ወይም ውስጣዊ ግፊቱን ታዞ ያልተፈቀደለትን ወንጀል የሚፈፅም ሰው የቢድዓ ሰው ሳይሆን ወንጀለኛ ነው የሚባለው፡፡ ሌላው ቀርቶ ይህ ወንጀልና አመጽ በህዝቡ ውስጥ ቢሰራጭና የተለመደ ቢሆን ሰዎች እንደ ድንጋጌ ወይም እንደ እምነት ተግባር ለመያዝ ካልተዘነበሉ በስተቀር ቢድዓ የሚለውን ስያሜ አይይዝም፡፡ ወይም በዲን ውስጥ አርአያ ተደርገው የሚያዙ ሰዎች ከተገበሩት፣ ከመኮነን ይልቅ እየቻሉ ዝምታን ከመረጡ፣ አላዋቂ የሆነ ሰው እንደሚፈቀድ እስኪያስብ ድረስ ወደ ኢስላም የሚገቡ ሰዎችና በኢስላም ውስጥ የሚያድጉ ታዳጊዎች

---

150 ድራዝ፣ አልሚዛን ገፅ 46

151 ያለፈው ምንጭ

152 ያለፈው ምንጭ

153 ያለፈው ምንጭ ገፅ 49

154 ያለፈው ምንጭ

ያለማንም ኮናኝ እያዩት ከእምነት አንድ ክፍል መስሏቸው ካደጉበት በዚህ ጊዜ ቢድዓ የሚልን ስምና ብያኔ ይሸከማል፡፡» ይላሉ፡፡[155]

በድራዝ እሳቤ ኢስላም በሁለንተናዊና ሰፊ ድንጋጌው ለሰው ልጅ በሁሉም ሕይወት ዘርፎች የሚያስፈልገውን ቅን መመሪያ ችሮታል፡፡ የተሻለ ሕይወትም ይኖር ዘንድ ይዘቱ አጠቃሎ ይዟል፡፡ ከሸሪዓ ሁለንተናዊነት ጋር በተጣጣመ መልኩ ለቢድዓም ሁለንተናዊ ግንዛቤን መከተል ይኖርብናል፡፡ ቢድዓ በአምልኳዊ ተግባራት ብቻ የታጠረ አይደለም፡፡ ከርሱ በተጨማሪም የመኗኗር እና ተግባራዊ ሕይወትንም ጭምር ያጠቃልላል፡፡ ዒባዳዎችና ሙዓመላዎች ለአንድ ወጥ የሆነ ሸሪዓ የተቅጣጩ ናቸው፡፡ ሸሪዓ ለሁለቱም ድንበሮችን አኑሯል፡፡ «በዚህም ይሁን በዚያኛው ክፍል ውስጥ የሚከሰት ማንኛውም ለውጥ በዲን ውስጥ ከሚደረግ ቢድዓ እውነታ ላይ የሚደመረው በነዚህ ድንበሮች ላይ ለውጥ መደረጉ የተረጋገጠ ጊዜ ነው፡፡»[156] ይላሉ፡፡

በዚህ ረገድ ድራዝ ቢድዓን በመተርጎም ሂደት የማስፋትን ዘዴ ከኢማሙ አሽ-ሻጢቢ ጋር ተመሳሳይ መንገድን ከተከተሉት የሚመደቡ ናቸው፡፡ «በዒባዳዎች ውስጥ የቢድዓ መከሰት የማይታሰብ ከሆነ በልማዶችም ላይ ይፈጠራል፡፡ ምክንያቱም ልዩነት ስላልነበራቸው የተደነገጉ ጉዳዮች አንዳንዴ አምልኳዊ ሌላ ጊዜ ደግሞ ልማዳዊ ይሆናሉ፡፡ ሁለቱም ከደንጋጊው በኩል የተደነገጉ ናቸው፡፡ ከሁለት በአንዱ ውስጥ ቢድዓ ሲከሰት በሌላውም ላይ ይከሰታል፡፡»[157]

ሻጢቢ ይህን በተመለከተ ምሳሌ ይሰጣሉ፡፡ «በሰዎች ላይ ቋሚና የማይቀየር ጉዳይ አድርጎ በየተወሰነ ጊዜ በተቀመጠ ሁኔታ ከዘካ ጋር በማይነፃፀር ክፍያ ገብርን መጫን ፡፡»ን ይጠቅሳሉ፡፡[158]

---

155 ያለፈው ምንጭ

156 ያለፈው ምንጭ

157 ሻጢቢ አል-ኢዕቲሷም 74/2

158 ያለፈው ምንጭ

ድራዝም ሰው ሰራሽ ህጎችን አስመልክተው «ሰዎች ሰማያዊ ድንጋጌዎች ናቸው ብለው እስካላመኑ ድረስ፡፡»[159] ቢድዓዎች ናቸው ብለው ከመሰየም ተቆጥበዋል፡፡ ካመኑ ግን «ግልፅ፣ ግዙፍና የሚኮነን ወንጀል፡፡»[160] አድርገው ነው የሚያስቡት፡፡

ምንም ይሁን ምን ግን በዚህ ወቅት ድራዝ የቢድዓን ትርጉም ዛሬ በዐቂዳና አምልኳዊ ተግባራት ላይ ብቻ ካጠሩት ጋር አይስማሙም፡፡ ይልቅ ግንዛቤው ከዚህ የሰፋ እንደሆነ ያስባሉ፡፡

ስለዚህ በግንዛቤው ውስጥ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ቢድዓዎችን ማካተት ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ ድራዝ የቢድዓን በሽታ በመለየቱ ሂደት ሚዛናዊ መንገድን ተጉዘዋል፡፡ እርሳቸው ማንኛውንም አዲስ ነገር የተባለ ሁሉ ውግዝ ቢድዓ እንደሚሉት አጥባቢያንም ይሁን ቢድዓን አስፍተው ከነምናምኑ እንደሚቀበሉ አግራሪያንም አይደሉም፡፡ እርሳቸው (ድራዝ) ጉዳዩ ረቂቅ ጥናት እንደሚያሻው እንዲሁም በሸሪዓዊ ግንዛቤና በታሪካዊ የቃላት አጠቃቀም መሃል በግልፅ መለየትና መፈተሽ እንዳለበት ያምናሉ፡፡

---

159 ድራዝ፣ አል-ሚዛን ገፅ 51

160 ያለፈው ምንጭ

## ሠላምና ጦርነት

ባለፉት ዓመታት ኢስላም ውስጥ ስለ ሠላምና ጦርነት ማውራት በዝቷል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ሙስሊሙ ኡማ እየዋኘበት ካለው አድማ ቀዘፋ በመነሳት፣ ከፊል የኡማው መሪዎች ከሚሄዱበት አስቃቂ የፖለቲካ ስርዓት፣ ብዙ አገራት በደረሰባቸው አረመኔያዊ ወረራ የተነሳ፤ ሚዛናዊ የሆኑ ዕውቀታዊ ድምፆች ከጩኸቱ፣ ንትርኩና ፕሮፓጋንዳው ውስጥ ተሸንፈው መሸፈናቸው ነው፡፡

አጋጣሚው ታዲያ ሸይኽ ድራዝ የተለየ አበርክቶ ሊያደርጉበት የሚገባው ሁነኛ ጊዜ ነበር፡፡ እናም በዚህ ረገድ የሸይኹ ሐሳብ በጥልቀቱና ኦሪጂናሊቲው የተለየም ነበር፡፡ ድንበር ከማለፍም ይሁን ማሳነስ የራቀ ሆኖ ሚዛናዊ ጎዳናን የተከተለ ነው፡፡

ፈረንሳይ 1939 በተደረገ የዓለም እምነቶች ኮንፈረንስ ላይ ባቀረቡት ኢስላም ከሌሎች የተለያዩ እምነት ተከታዮች ጋር ያለው ግንኙነት፤ ሰላም እና ጦርነትን አስመልክቶ ስላለው እሳቤ ባስረዱበት ንግግራቸው ድራዝ በሚገባ ገልፀውታል፡፡ በፈረንሳይኛ ቋንቋ «በኢስላም ውስጥ የዓለማቀፍ ህግጋት አጠቃላይ መርሆች» በሚል ርዕስ እምቅ ይዘት ያለው ጥናትም ፅፈዋል፡፡

በግብፅ የዓለም ህግጋት ጋዜጣ ላይ የታተመ ሲሆን 1952 ወደ ዓረብኛ ተተርጉሞ በአዝሃር መፅሔት ተሰራጭቷል፡፡

ርዕሱ «መድኸል አለል ቁርአኒል ከሪም» በተሰኘ መፅሐፋቸውም ውስጥም ይሁን ሌሎች ቦታዎች ላይ ጥልቀት ያለው ዳሰሳን በርዕሱ ዙሪያ አድርገዋል፡፡

ድራዝ ርዕሱን ለሁለት ከፍለውታል፡-

- ንድፈ-ሐሳባዊ እና
- ተግባራዊ በማለት

ኢስላም በዚህ ዘርፍ የተከተለው ንድፈ-ሐሳባዊ መሰረት ከአራት ምሰሶዎች የተወጠነ ነው፡፡

**አንደኛው**፡-ኢስላም በተለያዩ እምነቶች መሃል ያለውን መንፈሳዊ መቀራረብ አንክሮ መስጠቱና ወደርሱም አቅጣጫ መጣራቱ ነው፡፡«የቀደሙ እምነቶች ተከታዮችን አንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ ይመሰርቱ፣በወረዱ ሁሉም መፅሐፍትና ያለምንም መርጦ መቀበል በሁሉም ነብያት ወደ ማመን ተጣርቷል፡፡»[161]፡፡

**ሁለተኛ**፡- ነብዩ (ሰዐወ) «ያለፈውን በሚያፈርስ አዲስ ነገር እንዳልመጡ፤ ግን ከርሳቸው በፊት የነበረንና የነተበን ሊያድሱ፣ የተደበቀን ግልፅ አድርገው ሊያብራሩና የተዛባን ሊያቃኑ፡፡»[162] እንደመጡ ገላጭ ሰነድ በጥብቅ መኖሩ፡፡ ይህን እውነታ ከሚያፀኑት መካከል «ኢስላም» የሚለው ቃል ቁርአን ውስጥ መነሳቱ «ከላይ በተወረዱ እምነቶች መካከል የጋራ ትርጉም እንደሆነ»[163] አመላካች ነው፡፡

**ሶስተኛ**፡- በኃይማኖት ማስገደድ ውድቅ መደረጉ፡፡ «የመልዕክተኛው (ሰዐወ) ሚና ሰዎችን በእምነትና ኃይማኖት ማስገደድ እንዳልሆነ፣ ማስተማርና ማስጠንቀቅ ከዚያም ጉዳያቸውን ወደሚቆጣጠረው አላህ አሳልፎ መተው እንደሆነ፡፡»[164] የሚገልጽ ህግ ነው፡፡

**አራተኛ**፡- በዚህች የምድር ሕይወት ውስጥ የልዩነትን መብት ዕውቅና መቸር ያሻል፡፡ እርሱም በነዚህ ልዩነቶች ላይ ቁርጥ ያለውን ነገር እስከ ፍርዱ ቀን በማዘግየት፣ ሁሉም ሙስሊም መቀናትን ከመመኘቱ ጋር መልዕክቱን የማድረስ ግዴታውን በመወጣት በምድር ላይ የሰው ልጅ እስካለ ድረስ ግን በኃይማኖቱ እንደሚለያይ በመቀበል ነው፡፡

---

161 ድራዝ፣ ዲራሳት ኢስላሚያ ፊል ዓላቃት ደውሊያ ወል ኢጅቲማዒያ 221-222

162 ድራዝ፣ ዲራሳት ኢስላሚያ ገጽ 222

163 ያለፈው ምንጭ ገጽ 223

164 ያለፈው ምንጭ ገጽ 222

ከነዚህ አራት ምሰሶዎች ውስጥ ኢስላማዊው የተግባር ጎዳና በሰላምም ይሁን ጦርነት ጊዜ ግልጽ በሆኑ ምልክቶችን አጉልቷል፡፡

ሲጀምር ጦርነትን ከመፈለግና መሞከር መታቀብ፤ ከተተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ ከአስቀያሚ ውጤቱ ጋር ከመኗኗር ረገድ ድራዝ በአራት አሳጥረው ከላይ ወደታች ዘርዝረውታል፡፡

- መልካም በመዋልና በፍትሕ መርሆች ላይ በመመርኮዝ በእምነት ከሚለያዩ አካላት መሃል የግንኙነትና ትስስር ካስማዎችን መትከል፣ እነርሱም ላይ ድንበር ከማለፍ መታቀብና በእምነት መለየትን ብቻ ለጦርነትና ጥላቻ መነሻ አድርጎ አለመያዝ፡፡
- ጥላቻና ተቃርኖ ምን ያህል ቢሰፍኑም እንኳ ወደ ጦርነት እሳት እንዳይቀየር ለመጠንቀቅ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ፡፡ ምንም አንኳ የጠላትን ተንኮል ማመን ባያሻም ሙስሊሞች የሰላም ጥሪንና እንቅስቃሴዎችን ይቀበሉ ዘንድ ማነሳሳት፡፡ ይህን አስመልክተው ሁለት ቁርአናዊ አናቅጽ ተከታትለው መጥተዋል

وَإِن جَنَحُوا لِلسَّلْمِ فَاجْنَحْ لَهَا ۚ

«ወደ ዕርቅም ቢያዘነብሉ ወደ እርሷ አዘንብል፡፡ » (አንፋል 61)

ቀጥሎ የመጣውም

وَإِن يُرِيدُوا أَن يَخْدَعُوكَ فَإِنَّ حَسْبَكَ اللَّهُ ۚ

«ሊያታልሉህም ቢፈልጉ አላህ በቂህ ነው፡፡» (አንፋል 62)

- ጦርነቱ ከተከሰተ በኋላ አስፈሪ ገጽታውን መቀነስና ስነ-ምግባራዊ ደንቦችን ማስቀመጥ፣ ተዋጊ ያልሆኑ አካላት የእሳቱ ነበልባል እንዳይነካቸው መጠንቀቅ «ሴት በቤቷ፣ መኖክሴ በምኩራቡ፣ ገበሬ በእርሻው አይገደሉ ዘንድ መከልከሉ.....በዚያው መስከ ሌላው ቀርቶ ሆድ እቃን ከመክፈት፣ከመቆራረጥና ከማቃጠል ኢስላም ከልክሏል፡፡ »[165]

[165] ያለፈው ምንጭ ገፅ 225

- የጦርነቱ አቧራ ከተወገደና የድንበር አላፊው ጠላት ወሽመጥ ከተሰበረ በኋላ «ቸርነት፣ ያለፈን ይቅር ማለት፣ ሰላም ፈልገው የሸሹትንና የሰላም ቃል የሰጡትን ከመከታተል መታቀብ፡፡»[166] ግዴታ ነው፡፡

ይህ መካ የተከፈተች ዕለት የመልዕክተኛው (ሰዐወ) የሕያው ተግባር ተምሳሌት ነበር፡፡ ድራዝ የሁሉም ቤተ-እምነት መሪዎች የሰብዓዊነት ህመሞችን ለማስታገስ በትጋት መስራት እንዳለባቸው አደራ ይላሉ፡፡ «የሁሉም እምነት መሪ ስብዕናዎች በሁለንተናዊ ስነ-ምግባር ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ፣ በተከታዮቻቸው ውስጥም በእምነቱ ስም የሰብዓዊነት ወንድማማችነትን ስሜት ማሳደግና ማስፈን ያሻቸዋል፡፡»[167]

ስነ-ምግባርና የሰብዓዊነት ውበት በተዘነጋበት እና ከእምነት ውስጥ የቀኖና ጉዳይ ብቻ ቦታ ባገኘበት፣ በእምነቶች መሃል ከሚያቀራርቡ ሰበቦች ይልቅ የልዩነት ነጥቦች የጉላት ብርሃን ባነጣጠረበት ወቅት የዚህ ምክር ዋጋው የላቀና ውድ ነው፡፡

ድራዝ የአገራትን በኢስላም የመከፈት ታሪክ ከሰላምና ጦርነት ጉዳዮች ጋር ስላለው ቁርኝት በግልፅ ማብራራትን አልዘነጉም፡፡ «መድኸል አለል ቁርአን» በተሰኘ ድርሳናቸው ውስጥ ለዚሁ ርዕስ ክፍል ሶስትን ለይተውለታል፡፡ የአገራት በኢስላም መከፈትን ሲያነሱ ብዙ የታሪክ ሰዎችን አፍ ስላስያዘው ፍጥነቱና ድሉ ብቻ ሳይሆን የነበረውን ልዩ ባህሪም በማጉላት ነው የጀመሩት፡፡ ዛሬ ድረስ ስላለው መልካም ተፅዕኖም አኑረዋል፡፡ አዎንታዊ ተፅዕኖው የህዝቦችን ለፍጥረተ-ዓለሙና ለሰው ልጅ ያለውን ዕይታ የቀየረ ነው፡፡

በድራዝ እሳቤ መሰረት ከፊል የታሪክ ተመራማሪዎች አገራት በኢስላም የመከፈታቸውን ሂደት በግሪክ ዘመን ከነበረው የመቅዶኒያው እስክንድር ድሎች ጋር ማነፃፀራቸው ስህተት ነው፡፡

---

[166] ያለፈው ምንጭ

[167] ያለፈው ምንጭ ገፅ 227

የእስክንድር የድል መከፈቶች በአገራቱና ህዝቡ ስነ-ልቦና ላይ በጥቂት ቅምጥል ከተሜዎች ላይ ካልሆነ በስተቀር የግሪክ ባህል የተወው አንድም መልካም አሻራ ተፅዕኖ አልነበረውም፡፡ እንደውም «ምስራቁ የዘመተበትን አንበረከከ፡፡»[168] ማለት በሚያስችል ደረጃ ድል አድርገው የገቡት ግሪካውያን በተቃራኒው በድል ተደራጊዎቹ ህዝቦች ተፅዕኖ ስር ገብተዋል፡፡

አገራት በኢስላም መከፈታቸው ግን የደረሰበትን የትኛውንም የምድር ክፍልና ህዝብ በሙሉ ቀይሯል፡፡ ለውጡም በፖለቲካዊና የኢኮኖሚ ተተቋማት ላይ ብቻ የታጠረ አልነበረም፡፡ ይልቅ ለውጡ «የሰዎችን መንፈስ፣ ቋንቋ፣ አስተሳሰብ፣ ቀኖና፣ ህልም፣ ስለ ፍጥረትና ፈጣሪ ያለ እሳቤን በሙሉ የዳሰሰና ያጠቃለለ ነበር፡፡»[169]

ይህ ዘላቂና አሻራው አይጠፌ የሆነ ጥልቅ ተፅዕኖ ምዕራባውኑ እንደሚሉት ኢስላም በሰይፍ እንዳልተስፋፋ አሳማኝ ማስረጃ ነው፡፡ ነፍሶች በውዴታ ጠጡት፤ በሰዎች ልቦና ውስጥም ተዋሃደ፡፡ ድራዝ በትክክል እንደገለፁት ወደ «መንፈሶች የተደረገ ዘመቻ ነበር፡፡» የኢስላም የብርታት ምንጩና የዘውታሪነቱ ምስጢርም ይኸው ነው፡፡

ድራዝ ኢስላም ከሌሎች እምነቶችና የስነ-ምግባር ፍኖቶች መሃል በሰላምና ጦርነት ጉዳዮች ላይ በሚዛናዊነት የተለየ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

ያለምንም ሙብት የኩራትን፣ ብክለትንና የሰዎችን ደም በከንቱ የማፍሰስን መንገድ በሙሉ ኢስላም ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከመሆኑ ጋር ለተከታዮቹ ደግሞ ለበደል እጅ መስጠትንና መዋረድንም አይወድላቸውም፡፡ ወይም ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ ወንዶችን፣ ሴቶችንና ህፃናትን ለበደለኛ ጭሬ ትቶ ችላ

---

*[168] Dr Mohamed Abdullah Draz, Initiation aux koran, resume par Mohamed Abdel-Azim Aly 28-29*
[169] *ያለፈው ምንጭ*

ማለትንም ይጠላባቸዋል፡፡ ኢስላም ለዚህ ነው የታወረ የሆነ የእምነት ወገንኝነትንም የማይቀበለው፡፡[170]

ከነብዩ (ሰዐወ) ባህሪያት ውስጥ ለግላቸው መበቀልና ቂመኝነት አልነበረም፡፡ መስህብ ያለው የሕይወት ታሪክና ፋናቸው እንደሚሳየው ከሆነ እንደውም አስገራሚ የሆኑ፣ መበቀልን ከመቻላቸው ጋር ይቅር ማለት አንዱ ነው፡፡ ከነዚህ በተግባር ከታዩ ምሳሌዎች ውስጥ ከመካ መዲና ድረስ እርሳቸውን የመግደል ዓላማ አንግቦ የመጣውን ቁረይሽ በይቅርታ ማለፋቸው፣ በኸይበር ዘመቻ ወቅት ምግባቸውን የመረዘቺውን አይሁዳዊት ሴት ይቅር ማለታቸው፣ ሴት ልጃቸው ዘይነብ (ረዐ) ላይ ድንበር አልፎ ለነበረ ሰው ይቅርታ ማድረጋቸው ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህ ሁሉ ደግሞ በጣም የሚገርመው፣ በቸርነት መዓዛ የታሸውና መካ የተከፈተች ዕለት ሁሉንም ከመካ ያሳደዷቸውን፣ ለዓመታት በመዲና የተዋጓቸውን ቁረይሾች ይቅር ማለታቸው ይታወሳል፡፡»[171]

ነገርግን ነብዩ (ሰዐወ) ለባልደረቦቻቸው የትም ቦታ ሆነው የተበደለን አካል ለመርዳት ጀግንነትንና ጥንካሬን አስተምረዋቸዋል፡፡ «መድኸል ኢለል ቁርአኒል ከሪም» በተሰኘ መፅሐፋቸው ድራዝ ፈረንሳዊው ኦሬንታሊስት ጋውተር (አኽላቁል ሙስሊሚነ ወ አዕራፊሂም)[172] በተሰኘ መፅሐፉ ውስጥ «ዓረቦች ሌላው ቀርቶ የእምነት ስሜታቸው ከፍታው ባየለበት ወቅት እንኳ የሌሎችን እምነቶች ደም በለበሰ እልቂት ሊያጠፉ አልተንቀሳቀሱም፡፡» ማለቱን እንደ ዋቢ አስረጂ ያቀርቡታል፡፡

እውነታው ግን የመጀመሪያውን አገራት በኢስላም የመከፈት ፓኬጅ ከታሪክ አንፃርና ፍሬውን ስናጤነው ከእምነትና የፖለቲካ ተፅዕኖ ነበልባላዊ እሳት ለመሸሽ፣ ነፃነትን ለተጠማ ህዝብ ለማድረስ የተደረገ ትልቅ የነፃነት እንቅስቃሴ ነበር፡፡ በነዚህ ዘመቻዎች የነበሩ መቻጋገሮችና መስዋዕትነቶች ታዲያ ከፍሬው

---

[170] ያለፈው ምንጭ ገፅ 38

[171] *Draz, initiation aux Koran 32*

[172] በፈረንሳይኛ ‹Gautier, Les Moeurs et coutumes des Muslumans

ጋር ሲነፃፀር እጅግ ቀላል ግን ፈጣንና የጎመራ ነበር፡፡ ሌላው ይቅርና በድል የመከፈቱን ሒደት ቀለል ባለ ምሳሌ ስናየው አንድ ሰው «በሮቹ በግማሽ ያህል የተከፈቱ ነበሩ፡፡ ድል አድርገው ከፋቾቹ ሲገቡ በትንሹ ገፋ ከማድረግ የዘለለ ምንም ሚና አልነበራቸውም፡፡»[173] ብሎ ሊያስብ ይችላል ይላሉ ድራዝ፡፡

በርግጥ በመጀመሪያ አካባቢ የነበረው በድል አገራትን በኢስላም የመከፈት ሂደት ቅርፁን እንደያዘ ብዙ ቀጥሏል ማለት አይደልም፡፡ የመጀመሪያዎቹ ከፋቾች ህዝብን ከርሱ ነፃ ሊያወጡበት የተንቀሳቀሱለት የስርወ-መንግስታት ክፉ ትህዋስ ወደ ሙስሊሙም መንደር ዘልቋል፡፡ ግፊቱ ታማኝ የሆነውን የኢስላም አቅጣጫ ጠቋሚ ያሳተ ስለነበር ሐዲድም ስቷል፡፡ ድራዝን ያስጨነቃቸው የኢስላምን ታሪክ ጀስቲፋይ ማድረግ ሳይሆን የኢስላምን የተልዕኮ መቅኒ ማብራራት ነው፡፡

ድራዝ ጂሃድ የኢስላም የላቀ ሻኛው እንደሆነ የሚገነዘቡ ሲሆን፣ ግን በተጨማሪ ኢስላም ውስጥ የጦርነት ስነ-ምግባርም እንዳለ ያሳስባሉ፡፡ እነዚህ ስነ-ምግባራት ናቸው ኢስላምን ከሌሎች የሚለዩት፣ ምግባራዊ ንፃትንና ሰብዓዊ ተልዕኮን በማካተቱ ይለየዋል፡፡ ድራዝ የነዚህን ስነ-ምግባራት መሰረቶች፣ ከሰናይና ፍትህ እንዲሁም የተበደለን አካል ከማገዝ በማጠናቀር ምልከቶቹን አጉልተው አሳይተዋል፡፡

ድራዝ በብዕራቸው፣ ልሳናቸውና ትጋታቸው ለሕዝብና አገራቸው ታግለዋል፡፡ በካይሮ ሬዲዮ ሞገድ ውስጥ ህዝባቸውን ወራሪ ፅዮናውያንና አጋር አገራትን ይፋለም ዘንድ ቅስቀሳ አድርገዋል፡፡ በተደጋጋሚም ለጠላት እንደ አንድ እጅ ሆኖ የመቆምንና የመታገልን አስፈላጊነት አስተላልፈዋል፡፡ እንዲህም ይላሉ፡- «በደለኞች ከፊሉ ለከፊሉ ወዳጅና ረዳት ከሆኑ፤ የተበደሉ አካላት ለምንድን ነው ከፊሉ ለከፊሉ ረዳት የማይሆኑት !» ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡»[174]

---

[173] Draz, Initiation aus Koran 41

[174] ድራዝ፣ ሚን ኹሉቂል ቁርአን ገፅ 50

# ክፍል ሶስት

# በድራዝ እሳቤ ውስጥ

# የተሐድሶ ማዕዘናት

ዶክተር ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ ልህቀታቸው የተስተዋለበትን «ዱስቱሩል አኽላቅ ፊል ቁርአን» የተሰኘውን ስራቸውን የከፈቱበት መቅድም በ1077 በሞቱትና የአዝሃር ልሂቅ በነበሩት ሸምሰዲን አል-ባበሊ ጥበባዊ ይዘት ያለው ንግግር ነው፡- «ማንም ሰው መፅሃፍን የሚፅፈው ከሰባቱ አንዱን ሚና ለመወጣት ነው፡፡

1- ዘርፉን በመጀመሩ ሂደት ውስጥ ማንም ያልቀደመው አዲስ ጸሃፊ
2- የጎደለ ጉዳይ ኖሮ ለመሙላት የሚፅፍ
3- የተሳሰረ ንድፈ-ሐሳብ ካለ ለማፍታታት
4- ያለምንም ትርጉም ይዘት ለውጥ የረዘመን ጉዳይ ለማሳጠር
5- የተደበላለቀ ነገር ኖሮ ደርዝ ለማስያዝ
6- የቀደመ ደራሲ የሳታቸውን ነጥቦች ለማብራራት ወይም
7- የተበታተነ ጉዳይ ከነበረ ለመሰብሰብ ናቸው፡፡»[175]

በርግጥ ባበሊ ያሰቡት ጠቃሚ የሆነን ድርሰት ነው፡፡ ሜዳው ላይ ካሉት የዕውቀት ዓይነቶች ሌላ ዘርፎችን አዲስ እሳቤን በመፍጠር ወይም ሜዳው ላይ ላሉት እሳቤዎች በሌላ የዕይታ መነፅር የመመልከት መቻልን መንገዶች በማግኘት መጨመርን ነው፡፡ መደጋገምና ፕላጃሪዝም ድርሰት በሚለው ስያሜ ጥላ ስር አያርፉም፡፡ ለዚህም ነው «ከርሷ ውጪ ያለው ደራሲነት አይሰኝም፡፡» ያሉት፡፡

ድራዝ ይህቺን አባባል የዓይናቸው ማረፊያ አድርገው ነበር «ዱስቱሩል አኽላቅ ፊል ቁርአን» የተሰኘ ስራቸውን የጻፉት፡፡

---

175 ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ 1

ስራቸው እንደጠለቁ ልሂቃን ለመፅሐፋቸው አንባቢ ይህቺን የባበሊን የጥበብ ጥሪ ምን ያህል እንደመለሱ ይረዳል፡፡ ሲቋጩም ታዲያ በጥረቱ በሚተማመን በሐዳሲ ልሂቅ ንግግር ነበር «ስለ ቁርአን በዚህ አዲስ ድርሰት ውስጥ የጀመርነው ጉዞ ጊዜ የምናጠፋበት ቧልት ሆኖ አንባቢ ላይ ተጨማሪ ሸክምና የመፅሐፍት መደርደሪያችን ፈጽሞ መጨናነቅ እንዲገጥመው  አይደለም፡፡ ስራችን በምስራቁም ይሁን በምዕራቡ ዓለም አዲስ ነገር ይዞ ካልመጣ ጊዜ ማጥፊያ፣ ማጨናነቅና ሸክም እንጂ ሌላ አይደለም፡፡»[176] ይላሉ፡፡

ድራዝ ዛሬ ላይ በላይኛው ዓለም ጉርብትና ቢሆኑም በዚህኛውም ይሁን ሌሎች ስራዎቻቸው ላይ ምንም ዓይነት ብክነት እንዳላደረጉ ሊረጋጉ መብታቸው ነው፡፡

እንደውም የአላህን መፅሐፍ ለመረዳት፣ መለኮታዊ ምንጭን ለመግለፅ፣ በትርጉሙ ውስጥ ለመስመጥ ተጨማሪ ዋጋ ያለው ቁልፍ ነው ሰርተው ያለፉት፡፡ የድራዝ ስራ ለሁለት የቁርአን ሳይንስ ዘርፎችም መሰረት ያኖረና ከጫፍ እስከ ጫፍ ደርዞቹን ያካበቡበት ነው፡፡

ዶክተር ድራዝ ከአባታቸው ሸይኽ ዐብደላህ ድራዝ የዚህን የተሐድሶ የጉዞ አቅጣጫ ጠቋሚ፣ ይዘቱ በዳጎሰና እርባና-ቢስ እሳቤዎች መሃል የመለየትን ክህሎት፣ መደጋገምና ተመሳሳይ ነገር ከመስራት መራቅን የወረሱ ይመስላሉ፡፡ የድራዝን አባት አካሄድ «ሙዋፈቃት» የተሰኘውን የሻጢቢ መፅሐፍ ባብራሩበት መግቢያ ላይ እናገኘዋለን፡፡ አብራሪው ይህ መፅሐፍ ከይዘቱ ልቀት አንፃር ሰዎች ዘንድ ያልታወቀበትን ምስጢር ይጠይቃሉ፡፡ መልሱንም ራሳቸው ሲያኖሩ የሌሎች ድርሰቶች መታወቅ ዋጋና ይዘታቸውን አመላካች ነው ይላሉ፡፡ «ስንቱ በጎ ተደብቆ ገለባው ታውቋል፡፡» ይላሉ፡፡ ከኡሱል መፅሐፍት መሃል «ጀምዑል ጀዋሚዕ» የተሰኘው ድርሳን በዘርፉ ከርሱ የተሻሉ ስንት ድርሳናት

---

[176] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ 1-2

እያሉ ጥቅሙ ያን ያህል፣ አልፊነቱ ግን ብዙ ከመሆኑ ጋር ለዘመናት ኀልቷል፡፡ [177]

እንዳየነው ከሆነ «ዱስቱሩል አኽላቅ ፊል ቁርአን» የተሰኘው የድራዝ ድርሰት ከስራዎቻቸው ሁሉ አውራው፣ ዛሬ ድረስ ቦታ ለሚሰጠው አካል ወደ ኢስላማዊው እሳቤ የመጣ የላቀና ተጨማሪ ድልብ ነው፡፡ ከዚህ መፅሐፍ በተጨማሪ «አን-ነበኡል ዐዚም» «መድኸል ኢለል ቁርአኒል ከሪም» እና «አድ-ዲን» በተሰኙት ድርሳናት የድራዝ የተሐድሶ ቀንዲልነት ኀለቶ የታየባቸው ናቸው፡፡ በቁርአንና የሌሎች እምነቶች ሳይንስ የዕውቀት ባት ከፍታቸውን ያሳያሉ፡፡ በእውነቱ የድራዝ ሁሉም ስራዎች ከላቁ የእሳቤና ተሐድሶ (አል-ፊክሩ -ወ- ተጅዲድ) ስራነት የራቁ አልነበሩም፡፡ የእሳቤያቸውንም መሰረት ያኖሩት በኢስላማዊው ስልጣኔ ጉበን እና በምዕራቡ ላይ ጭምር ነው፡፡ የርሳቸው የእሳቤ ስራዎች ግን ኀልተው የታዩትና የወጡት በቁርአናዊ ጥናት ላይ ነው፡፡

በዚህ ዘርፍ ያለምንም ግነት ድራዝ የሁለት አዳዲስ እውቀቶችን መሰረት አኑረዋል፡፡ እነርሱም «አኽላቀል ቁርአን» እና «መስደሩል ቁርአን» ናቸው፡፡ የአስተሳሰብና ስደት ጓደኛቸው፣ ህሊናዊና ጥልቅ መንፈሳዊ ትስስር ካላቸው ወንድማቸው ማሊክ ቢን ነቢ ጋር በጋራ የ«መስደረል ቁርአን» ዘርፍን መሰረት አኑረዋል፡፡ በ«አኽላቀል ቁርአን» ዘርፍ ግን ድራዝ ዛሬም ድረስ የቀደማቸው ወይም የቀረባቸው ማንም የለም፡፡ በዚህ ክፍል በድራዝ እሳቤ ውስጥ የተሐድሶ ኮርነሮችን ለማየት እንሞክራለን፡፡ ቀጥለንም የምንቋጨው የቁርአንን ምንጭ ያጠኑበትን መንገድ ከባልደረባቸውና ወዳጃቸው ማሊክ ቢን ነቢ መንገድ ጋር እናነፃፅራለን፡፡

---

[177] አሽ-ሻጢቢ፣ ሙዋፊዋት በአባት ድራዝ ማብራሪያ የተሰራለት መቅድም ላይ፡፡

## የአኽላቁል ቁርአን ሳይንስ

ዶክተር ድራዝ ስለ ቁርአናዊ ስነ-ምግባር ከርሳቸው በፊት በምስራቅም ይሁን በምዕራብ የተፃፉ ወሳኝ መፅሐፍትን አንብበዋል፡፡ በተጻፉት ስራዎች ከተለመደው ሁኔታ በተሻለ የሕዳሴ እሳቤያቸውን ገልጠው የሚያሳዩ አስተያየቶችን ሰጥተዋል፡፡ የአኽላቅ ሳይንስን አስመልክቶ በኢስላማዊ ድርሳናት ውስጥ የተፃፉትን ከይዘትና ከተከተሉት ሜትዶሎጂ አንፃር በሶስት ከፍለውታል፡-

- አንደኛው ለሰዎች ተግባራዊ ምክር ለጋሽና የላዕላይ ተምሳሌትን ይከተሉ ዘንድ ለማሳመን የሚተጉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የኢብኑ ሐዝም «ሙዳዋቱ ኑፉስ» ይጠቀሳል፡፡
- ሁለተኛው ዓይነት ደግሞ የሰውን ልጅ ነፍስ ባህሪያት ገላጭና ተፈጥሯቸውንም የሚመድብ፣ በአርስቶትልና ፕሌቶ ማኗሎች መሰረት የከፍታን ማማ አመላካች ነው፡፡ «ተህዚቡል አኽላቅ» የተሰኘው የኢብኑ መስከዊ ድርሰት ይጠቀሳል፡፡
- ሶስተኛው ደግሞ ሁለቱን ሜትዶሎጂዎች በአንድ ላይ ሰብስቦ የያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ የአስፈሃኒ «አዝ-ዘሪዓ» እና ብዙዎቹ የኢማም አቡ ሐሚድ አል-ገዛሊ መጽሐፍት በተለይ ደግሞ የፊቅህና አኽላቅ ኢንሳይክሎፒዲያው «ኢሕያእ - ዑሉሙዲን» ይጠቀሳል፡፡»[178]

በሶስቱም ሁኔታዎችና የድርሳናት ዝግጅት ውስጥ ድራዝ የምንጭ ድርቀት፣ ከቁርአናዊ አናቅጽ ያለመምዘዝ ድክመት፣ ለግሪክ እሳቤ የሜትዶሎጂ ተከታይነትን አስተውለዋል፡፡ የቁርአናዊ ስነ-ምግባርን በጥልቀት ለመረዳትም ጥም ቆራጭ ሆነው አላገኟቸውም፡፡ ምክንያቱም ደግሞ ከቁርአን ከሪም ተስፈንጥረው የማይነሱና እርሱንም በአስተማማኝና በቂ ደረጃ በዋስትና ደረጃ አልተደገፉም፡፡ ሆኖም ድርሳናቱ «ንፁህ የሰው እሳቤ፣ ፀሃፍቱ ነፍሳቸውን ያስጠበቡበት የትጋት ውጤት፣ የጥልቅ አስተንትኖታቸውንና ፍልስፍናዊ

[178] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ 4

ትምህርቶቻቸውን ፍሬ ነው የሰደሩባቸው፡፡ ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ቁርአናዊ አናቅጽ የሉም፡፡ ካሉም በሁለተኛ ደረጃ ምንጭነት ነው፡፡»[179] ይላሉ፡፡

ድራዝ ብዙ ቁጥር ያላቸው ሙስሊም ንቁአን በንድፈ-ሐሳብ ደረጃ «አኽላቁል ቁርአንን» አስመልክቶ ለማቅረብ መትጋታቸውን አልካዱም፡፡ በሉሱልና ተውሂድ ሳይንሶች ውስጥ የማሳመርና የማጠልሸት ጉዳዮች፣ በፊቅህ መጽሐፍት ውስጥ ያሉ የኃላፊነት መስፈርቶች፣ በተሰውፍ ድርሳናት ውስጥ የታቆቱት የኒያና ኢኽላስ ጥናቶች ሁሉ ከቁርአን አኽላቅ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አላቸው፡፡ ነገርግን በዚህ ዘርፍ የነጎዱ ልሂቃን ያጠኗቸው ከፍልፋይ በሆነ ከጠባብ ማዕከል በተቀዳ ሁኔታ ነው፡፡ በተሟላ ዕይታ ከአሸናፊው መፅሐፍ ጥቅል ይዘት ጋር የተመረኮዘና ምሉዕ አልነበረም፡፡ ይባስ እንደውም በነዚህ ግንዛቤዎች ውስጥ ሰንጥቀው ተጓዦች ወደ ቁርአን አላስጠጉትም፡፡ «በአሚይነት ወይም ከርሱ ተቀድሞ ከተመዘዙለት እሳቤ በማብራሪያነት ወይም በመስካሪነት ሁኔታ ሲቀር»[180] ሲሉ ይጠቅሱታል፡፡

ቁርአናዊ ስነ-ምግባርን በንድፈ-ሐሳብ ደረጃ ካበረከቱት ሰዎች በላቀ ሁኔታ ብዙ ቀደምት ዓሊሞች በተግባራዊ ጎኑ፤ ማለትም ተግባራዊ የሆኑ የስነ-ምግባር ትዕዛዛት ጋር ትስስር ያላቸውን አናቅጽ መሰብሰብና መጻፍ ላይ አበርክቶ አላቸው፡፡ ድራዝ በተለየ ሁኔታ «ጀዋሂረል ቁርአን» የተሰኘውን የኢማም አቡ ሐሚደል ገዛሊን መፅሐፍ «የቁርአንን መቅኒ በሁለት መሰረታዊ ኤለመንቶች» ለመተንተን የሄዱበትን መንገድ አጉልተዋል፡፡

እነርሱም «አንደኛው ከዕውቀት ጋር የተያያዘ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከተግባራዊ ምግባር ጋር የተቆራኘ ነው፡፡»[181] ይላሉ፡፡

የኢማም አቡ ሐሚደል ገዛሊ ጥረት ልክ እንደ አል-ቃዲ ኢብኑል ዐረቢ፣ ጀሳስ እና መሰሎቻቸው የቁርአንን ብያኔዎች የማጉላት ቢጤ ነው፡፡[182]

---

[179] ያለፈው ምንጭ
[180] ያለፈው ምንጭ ገጽ 5
[181] ያለፈው ምንጭ ገፅ 5

ከፊል የኢማሚያ ሺዓዎች ለምሳሌ አርዲቢሊይና አልጀዛኢሪ በድራዝ ጥልቅ ዕይታ ለቁርአን ትዕዛዛት የሎጂክ ተርታን ያለመጠበቅ ጉድለት አስተውለዋል፡፡ እሳቤያቸው በሙሉ የተጨመቀው በንፁህ የፊቅህ ክፍሉ ላይ ብቻ እንጂ ስነ-ምግባር ላይ አይደለም፡፡ ይህ በኢስላማዊው ድርሳናት የቁርአን አኽላቅ ጥናት ዘርፍ ያለው ሲሆን፤ የምዕራቡና የኦሬንታሊስቱን ዓለም ደግሞ ድራዝ በጥልቀት ተገንዝበውት ስለ ቁርአን ስነ-ምግባር አለማወቅ ህመም በስር-ሰደድ ስቃይ እንደሚንገላታ ደርሰውበታል፡፡ የጉድለቶቹን አቅጣጫዎች በነዚህ ሶስት ቁጥሮች አስቀምጠዋቸዋል፡፡

**አንደኛው**፡- የቁርአንን ስነ-ምግባራዊ ንድፈ-ሐሳቦች በምዕራቡ ዓለም አሳቢያን መጽሐፍት ውስጥ ሆን ብሎ መዘንጋት፡፡ መዘንጋቱ ደግሞ የመጣው ኢስላምንና ስልጣኔውን በተንሸዋረረ እይታ ከማየት ሲሆን ፀረ- ኢስላም ውርስም ጭምር ነው፡፡ እነዚህ መፅሐፍት «በአጭሩ ወይም በተጨማሪ የስነ-ምግባር መርሆችን የግሪክ ጣዖታዊነት በሳየቺው መልኩ ቀጥሎ የአይሁድና ክርስትና እምነቶች ባወሱት መልኩ ይሰድራሉ፡፡ እነዚህን ሶስት እርከኖች ሲያጠናቅቁ ግን ቁርአን ውስጥ የተዳሰሱትን የስነ-ምግባር መመሪያዎች ሆን ብለው ዘለውት በፍጥነት ወደ አዲሱ የአውሮፓ ዘመን ይዘዋወራሉ፡፡»[183]

**ሁለተኛው**፡- የምዕራቡ ኦሬንታሊስት ልሂቃን ቁርአን ውስጥ ያሉትን የስነ-ምግባር መርሆዎች የዳሰሱበት የተገደበ ዕይታ ሲሆን፤ የስነ-ምግባርን ዕውቀት ከቁርአን በተሟላ ይዘት ማውጣትና የንድፈ-ሐሳብ አቅጣጫውን ከመዘናጋት የተነሳ ነው፡፡ እንዲሁም ከፊል ኦሬንታሊስቶች የቁርአንን ስነ-ምግባራዊ አናቅፅ በጥልቀት ካለመረዳት ለመገደብና ለማራቆት የሄዱበት ርቀትም አብሮ ይነሳል፡፡

**ሶስተኛ**፡- የቁርአን ቋንቋ ከሆነው ዐረብኛ ጋር ያለ የተበላሸ ግንኙነት፣ ምዕራባውያን ኦሬንታሊስቶች ያላቸው የቋንቋው ደካማ ከርዳዳ አረዳድና

---

182 ያለፈው ምንጭ

183 ድራዝ፣ዱስቱሩል አኽላቅ 2

ዕይታ በድራዝ ትዝብት የቁርአን ስነ-ምግባር ጥናት ዘርፍ ትክክል ባልሆነ ትርጉም ወይም በአስቀያሚ ማጠቃለያ ሰበብ አንድ ላይ ሆነው ብዙ ችግር ገጥሞታል፡፡ ከዚህ የምስራቅና የምዕራቡ ድርሳናት ዳሰሳ በኋላ ድራዝ ወደ አመክንዮአዊ ውጤት ደርሰዋል፡፡ እርሱም «ከንድፈ-ሐሳባዊም ይሁን ተግባራዊ የአትኩሮት አቅጣጫ በሙስሊሞችም በኦሬንታሊስቶችም ዘንድ የቁርአን ስነ-ምግባር ለጥናትም ይሁን ደረጃ ለመስጠት ዋነኛ ይዘት አልነበረም፡፡» «ልክ እንደዚሁ ደግሞ እስከምናውቀው ድረስ እስከዛሬ ከቁርአን ውስጥ በአጠቃላይ ስነ-ምግባራዊ ድንጋጌዎችን ፈልፍሎ ያወጣ የለም፤ ወደርሱ ከማይቀረብበትና በዘርፉ ብቸኛ ከሆነው የቁርአን መርህና መሰረቱን በተሰናሰለ ገንቢ ቅርጽ ለማቅረብ የሚሞክርም አልተገኘም፡፡ በምንችለው አቅም በዚህ ስራ ውስጥ የድርሻቸውን ልንሰጥ የምንሞክረው ይሆናል፡፡»[184] ይላሉ፡፡

ድራዝ የጀመሩት መንገድ ያልተሞከረና የቁርአን ስነ-ምግባር ሳይንስን መስራች እንደሆኑ፣ በዚህ ረገድም አበርክቷቸው ዋጋው የጎላ እንደሆነ ተረድተዋል፡፡ የብርቱ ትጋት መድረስና የጥልቅ እሳቤ ስጦታቸውም ነው፡፡ ይህን የሚረዳው ግን «ዱስቱሩል አኽላቅን» ከአንድ ጊዜ በላይ ደጋግሞ ያነበበው ሰው ነው፡፡ የድራዝ ተሐድሶ የ«አኽላቀል ቁርአንን» ሳይንስ በሁለት ጎን ነበር የመሰረተው፡፡

*የመጀመሪያው፡- **የአቀራረብ ዘዴ***

እርሱም የስነ-ምግባር ሳይንስ የፍልስፍና ቅርንጫፍ ከመሆኑ ጋር ወደ ኢስላማዊው አስተሳሰብ እርግብግቢት ውስጥ ሲያስገቡት በቁርአናዊ ይዘቶች ቀይሰውታል፡፡ ይህን አስመልክቶ «እዚህ ጋር አቀራረባችን ከሌላው የተለየ ነው፡፡ እርሱም የመጀመሪያዎቹ ዑለሞቻችን ቅድሚያ ትኩረታቸው የነበረው ኢኮኖሚያዊና ህጋዊ ክፍሉ ብቻ የነበር ሲሆን እኛ ግን በስነ-ምግባር ጎኑ ብቻ ላይ ትኩረት በመስጠት ከሁሉ በፊት ነን፡፡ ሁሉንም ጉዳዮች በዘመኑ የስነ-

[184] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ

ምግባር ባለሙያዎች ዘንድ የተቀመጡትን ሙያዊ ንድፎች ለመቅረጽ ነው የምንተጋው፡፡»[185] ይላሉ፡፡

*ሁለተኛው፡- የይዘት*

በድራዝ አስተዋይ ዕይታዎች ውስጥ የቁርአንን የተለዩ ግን ዋናዋና የሚባሉ የስነ-ምግባር የዕውቀት ግንዛቤዎች ይተነትናሉ፡፡ እነርሱም

- ግዴታ
- ተጠያቂነት
- ምንዳ
- ተነሳሽነትና ጥረት ናቸው፡፡

ቀጥለው ከአድማስ በሰፋ፣ ጥልቀት ባለው ሚዛናዊ በሆነ፣ የቁርአን አስተምህሮት በዚህ ዙሪያ በሚለይበት ሰላማዊ ተፈጥሮ ጋር በሚጣጣም መልኩ ገለጻ ያስከትሉበታል፡፡

**የቁርአን ምንጭ ሳይንስ**

በእውነቱ ከሆነ «የቁርአን ስነ-ምግባር ዕውቀት» መስራች እንደሆኑት ሁሉ ድራዝ በቁርአን ጥናት ዘርፍ ሌላም ተጨማሪ «የቁርአን ምንጭ ዕውቀት» ብለን ልንጠራው የምንችለውንም መስራች ናቸው፡፡ የቁርአን ምንጭ ዕውቀት ከ«ቁርአን ተዓምራት» ሳይንስ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው ሲሆን በቋንቋ ምጥቀት ትርጓሜው ካለፉት ዑለሞቻችን ብዙዎቹ ባቂላኒ፣ ራዚ፣ ሱዩጢ፣ እንዲሁም ከቅርቦቹ ደግሞ ራፊዒ እና ማሕሙድ ሻኪር በዘርፉ ብዙ ፅፈውበታል፡፡ ሆኖም ግን የቁርአን ምንጭ ሳይንስ አድማሱ የሰፋ፣ ከኢስላማዊው መልዕክት ሉላዊነት ጋር የተጣመረ ነው ቀጥለን እንደምናየው፡፡ በዚህ ዘርፍ የድራዝን የተሐድሶ አበርክቶ በሶስት ማጠቃለል ይቻላል፡-

---

[185] ድራዝ፣ ዱስቱሩል አኽላቅ 13

**የመጀመሪያው፡-** «የቁርአን ተዓምራዊነት» የሚባለውን ግንዛቤ ወደ አዲስና ሰፊ ግንዛቤ ማስፋት ሲሆን፣ ያለፉት ዑለሞች የትኩረት አቅጣጫ አድርገው ይዘውት የነበረን የቋንቋዊ ቅኝት አጥር ማለፍ ሲሆን፤ እንደውም የተልዕኮውን መለኮታዊነት እና ምንጩ ሰዋዊ ነው የሚለውን አሻሚ ድርም ገፋፊ ነው፡፡

**ሁለተኛው፡-** የቁርአንን መለኮታዊ ምንጭነት የማጣቀሻ ዘዴውን፣ ጥናቱም በወረደበት የታሪክና ባህለ ዘውግ የተደራጀ ይሆን ዘንድ ማስተካከል ነው፡፡ «ታሪካዊ የአቀራረብ ስፋትና የንፅፅር ትንተና»[186] የቁርአንን መልዕክት ትክክለኛነትና መለኮታዊ ምንጭነቱን ይገልጣል፡፡

**ሶስተኛ፡-** ይህን ጉዳይ ለመዳሰስ አዲስ ዘዴን መጠቀም፡፡ እርሱንም እዚህ ጋር «የአመክንዮ መከበብ» በማለት የሰየምኩት ሲሆን ትክክለኛ ቁርአናዊ ዘዴም ነው፡፡ ድራዝ ይህን ዘዴ የተጠቀሙበትን ቦታ ቀጥለን እናያለን፡፡ ድራዝና ማሊክ ቢን ነቢ የቁርአንን መለኮታዊ ምንጭነት ለማረጋገጥ ባመጡት በዚህ የዘዴ መለወጥ ላይ ጥቂት እንመልከት፡፡

በመሰረቱ የኢስላም ምሁራን የቁርአንን መልዕክት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ቋንቋውን እንደ መግቢያ ማብራሪያ አድርገው ነበር፡፡ ድራዝ የተነሱት የቁርአንን ትንታኔ ለመስጠት ከተለያዩ ማዕዘኖች መመንጠቅ እንደሚያስችል በማወቅ ነው፡፡ «ሆኖም ሁሉም በሁለት መሰረታዊ ምሰሶዎች ላይ ያበቃሉ፡፡ «ቋንቋ እና እሳቤ» ቀጥለውም የቁርአን ጥናታቸው «ከቋንቋዊ ዘርፍ የተነጠለ»[187] እንዲሆን ወሰኑ፡፡ ይህ ታዲያ የቁርአንን መልዕክት ለማረጋገጥ በውርስ ከመጣው ዘዴ አዲስ መለያ ቅያስ ነበር፡፡

ከዚህ ዘዴ የመቀየር ምክንያቶች ውስጥ ድራዝ በፈረንሳይኛ ቋንቋ «መድኸል ኢለል ቁርአን» የተሰኘውን ድርሳናቸውን ሲሰድሩ አውሮፓውያን አንባቢዎችንና ባጠቃላይ የዐረብኛ ቋንቋ ተናጋሪ ያልሆኑትን የሰው ልጆች

---

[186] መድኸል ኢለል ቁርአኒል ከሪም በተሰኘው የድራዝ መጽሐፍ ውስጥ ያለን ንዑስ ርዕስ ለማመልከት ነው፡፡

[187] ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝ፣መድኸል ኢለል ቁርአኒል ከሪም ዐርዱን ታሪኺዩን ወ ተሕሊሉን ሙቃረን

የቋንቋዊ ተዓምር ብቻ የቁርአንን መልዕክት ትክክለኛነት ለመረዳት በቂ፣ አሳማኝና፣ አርኪ አለመሆኑን መገንዘባቸው ነው፡፡

የኢስላም ምሁራንም እነዚህን አካላት በሚያናግሩበት ወቅት ሌላ የንግግር ቅርፅ እጅጉኑ እንደሚስፈልጋቸው ስለወሰኑም ጭምር ነው፡፡ እነዚህ አካላት ደግሞ ከሰው ልጅ ብዙሃኑን የሚሸፍኑ ናቸው፡፡

እዚህ ጋር ወሳኙ ማስታወሻ ድራዝ የቁርአንን ቋንቋዊ ተዓምር ችላ ብለውም ይሁን ውድቅ አድርገውት አይደለም፡፡ «አን-ነበኡል ዐዚም» የተሰኘ የቀደመ ስራቸው ላይ በዚህ ርዕስና ይዘት ፅፈዋል፡፡ በዚሁ ስራቸው ብዙ ገጾችን በቁርአን የአገላለጽ ተዓምራት ላይ አውለዋል፡፡ አስተውሎት የዳመነባቸውን ጥልቅ ዕይታዎች አኑረውበታል፡፡ «ቅላፄያዊ ፅሁፍ»[188] «ቆርቋሪ ውበት»[189] የሚሉ አገላለፆችን ለቁርአን ከሪም ተጠቅመዋል፡፡ «ቁርአን ከንባብ ሞገሱንና ድምቀቱን፣ ከግጥምም ውበትና አርኪነትን ወስዷል፡፡»[190] ይላሉ፡፡

የቁርአን ቅኝቱንም «አሰልቺ ከተሜ ወይም ኀርባጭ ገጠሬ አይደለም፡፡»[191] ይላሉ፡፡ «በውስጡ የሚከላከልበት የሆነ ተፈጥሯዊ ኃይል ያለው ሲሆን ዛሬም ድረስ እጃቸውን ለመስደድ የሚሞክሩትን ከመከላከል አልቦዘነም፡፡»[192] ይላሉ፡፡

የቁርአንን «ቅላፄያዊ ምት» ለመገንዘብና ጣዕሙን ለመቅመስ ቆንጆ ተግባራዊ ተሞክሮንም የጠቆሙ ሲሆን፣ ድራዝ የተሸከሙትን በሙከራ የታመቀ ህሊና አመላካች ነው፡፡»[193]

ድራዝ የገለፁትና የቁርአን ተዓምራዊ ገለፃ ቀድሞም የተቆረቆረ በር ሲሆን፣ ከዚህ ቀደም የነበሩ የቋንቋና ሰዋሰው ሰዎች ጽፈውበታል፡፡ በድራዝ አገላለጽ

---

[188] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም 101

[189] ያለፈው ምንጭ

[190] ያለፈው ምንጭ

[191] ያለፈው ምንጭ

[192] ያለፈው ምንጭ

[193] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም ከገፅ 101-102

«ከቁርአን ውበት የላይኛው ንጣፍ፡፡»[194] ማንኛውንም ልሳን ተናጋሪ ሰው ወደ ሚረዳው የትርጉምና ይዘት ተዓምራዊነት መሸጋገርን ነው፡፡

ከዚህ አዲስ ዘዴ መልካም ፍሬዎች ውስጥ ቁርአንን ከዐረባዊ የእውቀት ባህል ቅኝት ብቻ መንቀልና በዓለማዊነት ዘውግ ላይ መትከል ዋነኛው ነው፡፡ «የቁርአንን እሳቤ ከልባሱ መጠቅለልና ካለበት አካባቢ (ዘውግ) አውጥቶ ከዐረብኛ ቋንቋ ሩቅ ለሆነው አውሮፓዊ እሳቤ ህሊና ቅርብ ማድረግ ነው፡፡» [195] ይላሉ፡፡

የቁርአንን መልዕክት ኦሪጂናሊቲ ለማረጋገጥ በዐረብኛ ቋንቋ አገላለጽ ብቻ ወስጥ የገደቡት የተልዕኮውን የቦታ ዓለማዊነትም ለሰው ሁሉ ቅርብ ከመሆን አቅበውታል፡፡ ድራዝ ቁርአንን የተመለከቱባቸውን ማዕዘናት ሶስት አድርጎ መከፈል ይቻላል፡፡

*አንደኛው፡- __ታሪካዊ ማዕዘን__*

ድራዝ በዚህ ውስጥ የመልዕክተኛውን (ሰዐወ) ከነብይነት በፊትና በኋላ ያለውን ዝርዝር ሕይወታቸውን ተከታትለው ይናገራሉ፡፡ ለውጫዊ ተፅዕኖዎችም ትኩረት ከመስጠት ጋር ግን በነብያዊው ስብዕናና ሕይወት ውስጥ የእውነተኝነትና ኢኽላስን ተፈጥሮም ለማረጋገጥ ነው፡፡ ድራዝ ቀጥለው የቁርአንን ሰነድ ዛሬ ድረስ ከትውልዳዊ የቅብብሎሽ ትስስር ሰንሰለት ውስጥ ለማረጋገጥ የቁርአንን መሰብሰብ ታሪክ ያትታሉ፡፡

*ሁለተኛ፡ __የትንታኔ ማዕከል__*

ድራዝ ቁርአን ራሱ የዐቂዳና አኽላቅ ይዘቱንና ተልዕኮውን እንዲናገር አድርገውታል፡፡ በዚህም የተልዕኮውን ምጥቀት፣ በሰው ልጅ ማንነት ውስጥ በጥልቀት መስረጉን፣ በጥልቅ እና ፈጠን ባለ ታሪካዊ ይዘቱ በህዝቦች ሕይወት

---

[194] ያለፈው ምንጭ

[195] ድራዝ፣ መድኸል ኢለል-ቁርአኒል ከሪም 14-15

ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ አጉልተዋል፡፡ ቅዱስ ምጥቀቱ ከፍጥረተ-ዓለሙ ፈጣሪ እንጂ ከየትም ሊመጣ እንደማይችልም አመላካች ነው፡፡

*ሶስተኛ፡- <u>የአመክንዮ ማዕከል</u>*

በዚህ ክፍል ደግሞ ድራዝ ከመለኮታዊ ምንጭ መቀዳቱን አረጋጋጭ ቁርአናዊ ዘዴን ይፋ ያደርጋሉ፡፡ በተልዕኮው ይዘትና በመልዕክተኛው (ሰዐወ) ከመላካቸው በፊትም ይሁን በኋላ በስነ-ምግባር ዙሪያ ሙሽሪኮችንና የመፅሐፍ ባለቤቶችን ይከራከራቸዋል፡፡ የቁርአንን ኦሪጂናሊቲ ከራሱ ቁርአን የተሻለ ምንም አረጋጋጭ አስረጂ የለም፡፡ የመጡትን የድራዝ አሳማኝ መረጃዎች በሶስት መክፈል ይቻላል፡-

- የመልዕክተኛውን (ሰዐወ) ስብዕና የሚተንትን
- ከመልዕክቱ ይዘት ጋር የተሳሰረ እና
- ከታሪካዊ አውድ የተጠቃለሉ ናቸው፡፡

እኛ እነዚህን ማስረጃዎች የተሟላ ቅርፅ ይሰጣል ባንልም በርዕሱ ዙሪያ አንባቢ የድራዝን መጽሐፍት ወደ ማንበብ ይሄድ ዘንድ ጥቂት እንቀነጭባለን፡፡ ድራዝ ልሳነ-ምጡቅና በመረጃቸውም አቀራረባቸውም ብርቱ ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን በተመለከተ የመልዕክቱን ተሸካሚ ስብዕና በማጥናት ትክክለኛነቱን መበየን ይቻላል፡፡ በእውነተኛና አስመሳይ ሙናፊቅ፣ በተረጋጋ እና በተቀባዠረ ሰው መሃል ያለው ልዩነት ግልጽ ነው፡፡ ዐብደላህ ኢብኑ ሠላም (ረዐ) ከነብዩ (ሰዐወ) ፊት ላይ ድንገት እንዳያቸው ነበር የውሸታም ፊት እንዳልሆነ መበየን የቻለው፡፡

ኢብኑ ሠላም (ረዐ) «መልዕክተኛው (ሰዐወ) መዲና እንደደረሱ ሰዎች በቡድን እየሆኑ ወደርሳቸው ጎረፉ፡፡ መልዕክተኛው (ሰዐወ) መጡ እየተባለም መወራት

ጀመረ፡፡ እኔም ከሰዎች ጋር ሆኜ ላያቸው ሄድሁ፡፡ ፊታቸውን ስመለከተው የሐሰተኛ ፊት እንዳልሆነ አወቅሁ፡፡»[196] ይላል፡፡

የኢብኑ ሠላምን (ረዐ) ፈራሳ ያልተለገሱት ደግሞ ሎጂካል የሆኑ ምክንያትና ውጤት ያላቸው ማስረጃዎችን ይሹ ነበር፡፡ ወደነዚህ ዓይነቶቹ ደግሞ ድራዝ «ነበኡል ዐዚም» እና «መድኸል አለል ቁርአኒል ከሪም» በተሰኙ ድርሳኖቻቸው ዙረዋል፡፡ የነብዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) ሕይወት ከመላካቸው በፊት በእውነተኝነትና በባለአደራነት የታወቀ ነው፡፡ ይህንን ወዳጅም ይሁን ጠላት፣ የቅርቡም ይሁን የሩቁ መስክሮላቸዋል፡፡ የዚህ ታሪካዊ አመክንዮ ውጤት የስብዕና ነፀብራቃቸው ስር ሰዶ ቦታ ከያዘና ከተላኩ በኋላ እውነተኛ መሆናቸውንም እንቀበል ዘንድ ያስገድዳል፡፡ «ክቡር የሆነውን የሕይወት ታሪካቸውን፣ እንቅስቃሴና ስክነታቸውን በጥልቀት ያጤነው፣ ማመላከትና አስተምህሮታቸውን ሲደሰቱም ይሁን ሲቆጡ፤ ለብቻቸው ሲገለሉም ይሁን ከሌሎች ጋር ሆነው ያስተዋላቸው፤ ከብልሽትና አጠራጣሪነት የራቁ እንደሆኑ ምንም አይምታታም፡፡ ውስጣዊ ማንነታቸውም ይሁን በውጭ የሚያሳዩት ተግባር በእውነታ ረቂቅነትም ይሁን ቁራጥነት በላቁ ጉዳዮችም ይሁን አነስታዎች ላይ እኩል ሆነው ያገኛቸዋል፡፡ ወዳጅም ይሁን ጠላት ዛሬ ድረስ እንደሚመሰክርላቸው ከነብይነት በፊትም ይሁን በኋላ ይህ ልዩ ባህሪያቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ሰማዕቱና ገጣሚው ሶሐባ ዐብደላህ ኢብኑ ረዋሐ እንደገለፃቸውም፡-

ገላጭ ተዓምራት በይቆራኙትም

ውስጣዊ ነገሩ ያሳይሃል መልካም፡፡[197] ናቸው፡፡

የቁርአንን መልዕክት ትክክለኛነት ከሚያሳዩ ትላልቅ መረጃዎች ውስጥ መልዕክቱ ከመልዕክተኛው (ሰዐወ) ስብዕና የተብቃቃና ራሱን የቻለ መሆኑ

---

[196] ሙሐመድ ቢን ዒሳ አት-ቲርሚዚ፣ ሱነኑ አት-ቲርሚዚ 562/4

[197] ኢብኑ ሐጀር፣ አል-ኢሷበቱ ፊ ተምይዚ ሶሐበቲ

አንዱ ነው፡፡ ሰውኛ የሆኑ ሰነዶች (አናቅፅ) ብዙውን ጊዜ የባለቤቱን ተፅእኖ ተሸካሚ ናቸው፡፡ በሰውየው ነፍስና ፍላጎት ቀለም የሚፈሱም ናቸው፡፡ መለኮታዊ ተልዕኮዎች ግን እንደዚያ አይደሉም፡፡ ከመልዕክተኛው ስብዕና እና ነፍስም ከፍ ያሉ ናቸው፡፡ [198]አመክንዮአቸውን ግድ ያደርጉበታል፡፡ በምሪታቸውም ይነዱታል፡፡

ፈጣሪያችን (ሱወ) ቁርአን በነብያችን (ሰዐወ) ግዴታና የተጣለባቸው ነው አላለምን ?

إِنَّ الَّذِي فَرَضَ عَلَيْكَ الْقُرْآنَ لَرَادُّكَ إِلَىٰ مَعَادٍ

‹‹ያ ቁርአንን የተከፋፈለ ኾኖ ባንተ ላይ ያወረደው (አምላክ) ወደ መመለሻ (ወደመካ) በእርግጥ መላሽህ ነው፡፡›› (አልቀሶስ 85)

إِنَّا سَنُلْقِي عَلَيْكَ قَوْلًا ثَقِيلًا

‹‹እኛ ባንተ ላይ ከባድ ቃልን እንጥላለንና፡፡›› (ሙዘሚል 5)

ቁርአናዊው ተልዕኮ ከነብያዊው ስብዕና ራሱን የቻለ እንደሆነ ከሚያሳዩ መገለጫዎች ውስጥ

**አንደኛ፡-** መልዕክተኛው (ሰዐወ) መውረዱን እጅግ ፈልገውና በጣም አንገብጋቢ በሆነባቸው ወቅት የወሕይ መዘግየት ተከስቶባቸዋል፡፡ እንደሚታወቀው የወሕይ መገለጫ ግልጽ ነው እንጂ ‹‹የራሳቸው ፈጠራና ልፋት ቢሆንማ ጥቂት የእጃቸው ልፋት ብቻ በቂ ነበር፡፡ ሌላ ቁርአን ለማምጣት አዲስ ቀንም ይሁን የረዘመ ጊዜ ሳይጠብቁ ያመጡት ነበር፡፡››[199] ይላሉ ድራዝ፡፡

---

[198] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም 22
[199] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም 71

በዓኢሻ (ረዐ) ላይ የተቀጠፈባቸው ወሬ ለዚህ ጉዳይ በቂ ምሳሌ ነው፡፡ «በሁኔታው ልቦች ጉሮሮ እስኪደርሱ፣ ሰዎች በጉዳዩ ላይ ሲዳከሩ ወሕይ በጣም ዘግይቶ ነበር፡፡»[200]

የክብር ዋጋ ከሌሎች እሴቶች ከፍታ በነበረበት የዐረብ ማህበረሰብ ውስጥ መልዕክተኛው (ሰዐወ) እና ጥብቂት እንዲሁም ብፁዕ ባለቤታቸው ያጋጠማቸውን የስነ-ልቦና ጫና እስኪ ለአፍታ አስቡት !

ከራሳቸውም ይሁን ከጥብቋ ባለቤታቸው ክብር ላይ መከላከል አልቻሉም፡፡ ብቸኛ መፍትሔያቸው የነበረው በትዕግስት ባልደረቦቻቸውን እያማከሩ የአላህን (ሱወ) ብያኔ መጠባበቅ ብቻ ነበር፡፡ መልዕክተኛው (ሰዐወ) ለአንድ ወር ሙሉ የዓኢሻን (ረዐ) ንፅህና በመመስከር ወሕይ እስኪወርድ ድረስ ያን ሁሉ ህመም ምን አሸከማቸው? ብለው የሚከተለውን አሳማኝ ጥያቄ ያቀርባሉ፡ -«ቁርአንን እርሳቸው የሚቀጣጥፉት ቢሆን ኖሮ ክብራቸውን መከላከያ የምትሆን፣ የወረኞችን ዝርግ ምላስ መሰብሰቢያና የሚስታቸውን ክብር ለመጠበቅ አልፎም ከሰማይ መጣች የሚሏት ሐረግ እንዴት አጡ?» ይላሉ፡፡[201] ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ይህን ያደረገው እውነተኝነት፣ ኢኽላስ እና መለኮታዊ መልዕክቱ ከሰዋዊ ስብዕናቸው የተብቃቃ ስለሆነ ብቻ ነው፡፡

**ሁለተኛ**፡- ወሕይ ነብያችን (ሰዐወ) ከሚከጅሉትና እንዲወርድ ከሚመኙት ተቃራኒ ሆኖ መውረዱ፡፡ እንደውም ቁርአን አንዳንዴ «የርሳቸውን የግል ምልከታ ሲያርም፣ ፍፁም መዘንበል የለለባቸውን አቅጣጫ ሲፈቅድላቸው፣ ትንሽም ዘግየት ካሉ ቁርአን በጠንካራ ነቀፌታ፣ በአሳማሚ ውግዘት እና በመራር ትችት ይመጣቸዋል፡፡»[202] ለዚህ ምሳሌ

---

[200] ያለፈው ምንጭ
[201] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም 24
[202] ያለፈው ምንጭ

عَفَا اللَّهُ عَنكَ لِمَ أَذِنتَ لَهُمْ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَكَ الَّذِينَ صَدَقُوا وَتَعْلَمَ الْكَاذِبِينَ

«አላህ ከአንተ ይቅር አለ፡፡ እነዚያ እውነተኛዎቹ ላንተ እስከሚገለጹልህና ውሸታሞቹንም እስከምታውቅ ድረስ ለነርሱ (እንዲቀሩ) ለምን ፈቀድክላቸው? » (ተውባ 43)

وَتُخْفِي فِي نَفْسِكَ مَا اللَّهُ مُبْدِيهِ وَتَخْشَى النَّاسَ وَاللَّهُ أَحَقُّ أَن تَخْشَاهُ

«አላህ ገላጩ የሆነን ነገር በነፍስህ ውስጥ የምትደብቅና አላህ ልትፈራው ይልቅ የተገባው ሲሆን ሰዎችን የምትፈራ ሆነህ» (አህዛብ 37)

أَمَّا مَنِ اسْتَغْنَىٰ 5فَأَنتَ لَهُ تَصَدَّىٰ

የተብቃቃው ሰውማ፤ አንተ ለእርሱ (ለእምነቱ በመጓጓት) በፈገግታ ትቀበለዋለህ፡፡ (ዐበሰ 5-6)

يَا أَيُّهَا النَّبِيُّ لِمَ تُحَرِّمُ مَا أَحَلَّ اللَّهُ لَكَ ۖ تَبْتَغِي مَرْضَاتَ أَزْوَاجِكَ ۚ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ

«አንተ ነቢዩ ሆይ! አላህ ለአንተ የፈቀደልህን ነገር ሚስቶችህን ማስወደድን የምትፈልግ ስትኾን (ባንተ ላይ) ለምን እርም ታደርጋለህ? አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው፡፡» (ተህሪም 1)

እነዚህን ቁርአናዊ ማንኳኳቶች ቁሳዊ ዝንባሌን የጠገበና ኢ-አመክንዮአዊ የታሪክ መዛባት ዘመቻ ሰለባ የሆነ የኦሬንታሊስት አዕምሮ አይገነዘብም፤ የመልዕክቱ ከመልዕክተኛው ስብዕና የተብቃቃና ኦሪጂናል እንደሆነ ማስረጃ አድርጎም አይቀበልም፡፡ ከፊል ኦሬንታሊስቶች እነዚህን መገለጫዎች ነፍስን የመሸወድ ትርጉም መስጠት ነው ወደሚል ድምዳሜ ደርሰዋል፡፡ ነብዩ (ሰዐወ) ራሳቸውንና ውስጣቸውን የሚወቅሱበት የተለየ አካሄድ ነው ብለው መልሰውታል፡፡ ድራዝ ለዚህም ልብ አርኪ የሆነ መልስ ሰጡ «እስኪ እነዚህ

አሳማሚ የሆኑ ቁርቆራዎች ከራሳቸው የወጡ፣ ከእሳቤያቸው ጋር የተጣረሰ ጉዳይ ሲገጥማቸው ፀፀትና ማንነታቸውን ወቃሽ የሆኑ ገላጭ ነገሮችን በዚህ አስደንጋጭ እና አስኮናኝ በሆነ መልኩ በግልጽ ያወጡታል ?! ራሳቸውን ለመሸፈንና የሐሳባቸውን ክብር ለማቆየት ሲሉ እንኳ ቢያንስ ዝምታን አይመርጡምን ?![203]

ሌላው ኦሬንታሊስቶቹ ከነዚህ ቁርአናዊ አናቅጽ ጀርባ ያሉ ካልተረዷቸው ጥበባት ውስጥ «የመለኮት እና የባርነት ቦታ፣ የሚወዱትን ስርዓት የማስተማር የከፍታን መንገድ፡፡» [204] ገላጭና አብራሪ ነው፡፡

ከዚያም ደግሞ የነዚህ አናቅጽ በቁርአን ውስጥ መኖር መልዕክቱ ከመልዕክተኛው (ሰዐወ) ማንነትና ከጃሎት ራሱን የቻለ ዝንተ-ዓለማዊ ለመሆኑ ምጡቅ መረጃ፤ የቁርአን ምንጭ ከሰውኛም ይሁን ምድራዊ ግምቶች በላይ የሆነው የላዕላዩ ኃያል ጌታ ለመሆኑ ጭምር ጠንካራ ማስረጃ ነው፡፡ «ውስጣዊ ፍላጎትም ይሁን ጉዳይ የማይቆጣጠረው፣ ይባስ እውነትና ሐሰትን በመለየቱ ረገድ ቆራጭና ገላጩ ለጥሩና መጥፎ ሚዛኑ፣ ሰዎች ወደዱም ጠሉም፣ አመኑም ካዱም ከማይጨንቀው ኃይል የመጣ ቃል ነው፡፡ የታዛገሮች ትጋት አይጨምረውም የአመፀኞች ወንጀል አያጎድለውም፡፡ በገዢና ተገዢ፣ በባሪያና አሳዳሪ መሃል ምን ያል ክፍተት አለ !»[205]

## ሎጂካዊ ከበባ

ጉዳዩ ምንም ይሁን ምን የቁርአንን ምንጭ በሎጂክ ከሶስት ቢሆናሎች የግድ ከአንዱ አይወጣም፡፡

- ከነብዩ (ሰዐወ) አዕምሮና ልቦና የመነጨ

[203] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም 26
[204] ያለፈው ምንጭ
[205] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም 28

- ከርሳቸው በፊት ከነበረ ወይም ዘመን ከተጋራቸው ሰውኛ ምንጭ የተዋሱት
- የጊዜና ቦታ ድንበር ከማይገድበው መለኮታዊ ምንጭ የተወረደላቸው የሚሉ ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ቢሆናል «ቁርአን የነብዩ (ሰዐወ) እጅ ስራ ነው » የሚለው ሲሆን ይህን በተመለከተ የመልዕክቱ ተሸካሚ ስብዕና ዙሪያ ያጠለሉ ታሪካዊ ምስክርነቶች ፈጽሞ የማይቀበሉት ነው፡፡

መልዕክተኛው (ሰዐወ) መፃፍም ይሁን ማንበብ በማይችሉ ህዝቦች መሃል የነበሩና እርሳቸውም እንደዛው የነበሩ ናቸው፡፡

በተጨማሪ የመልዕክቱ ይዘት የያዛቸው ሳይንሶችና ጥበባት በግለሰባዊ ዕይታ እና ከትምህርት የተገኘ ነው ለማለት ፈፅሞ አያስደፍርም፡፡ ሌላው ቀርቶ ተሸካሚው በዘመን ከተጋሩት የተሻለ በዕውቀት የመጠቀ፣ በንባብና መፃፍ የተካነ ነው ብንል አንኳ ፈፅሞ አይሆንም፡፡ ቁርአን የያዛቸው የሩቅ ሚስጥራት (ገይብ) ዕውቀቶች አንዳንዶቹ ተከስተው ሰዎችም ተመልክተዋቸዋል፡፡ በነብዩም ዘመን ይሁን በሌላ ማንኛውም ዘመን ወደ ሰዋዊ ምንጭ ሊያስጠጓቸው የማይቻሉ ነበሩ፡፡ በድራዝ አባባል «የገይብ ጉዳይ ላይ ፊራሳም ይሁን የአዕምሮ ምጥቀት አቅም የሚገደብበት ነው፡፡»[206]

የቁርአን ቅኝታዊ ትንታኔዎች የነብዩ (ሰዐወ) ጽሁፍ እንዳልሆነ በሚገባ በመግለፅ ምንም የጥርጣሬ ክፍተትን ሳያስቀር ይዘጋል፡፡ በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ የነብያችን (ሰዐወ) የሐዲስ ንግግሮች ቢደርሱንም አንዱም ከቁርአን ጋር በቅኝቱ፣ በአሰባጠሩና ቃሉ የሚመሳሰል አላገኘንም፡፡ እንደውም «የቁርአንን ዘዴ አንድ ምስል፣ የነብዩን መንገድ ሌላ ሆነው በአንድ ዐውድ ሲፈሱ አናያቸውም፡፡»[207]

---

206 ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም 55
207 ያለፈው ምንጭ ሰ

ይዘቱ እና የአጠራር ዘዴው የቁርአን ተልዕኮና መልዕክቱ ከሙሐመዳዊው እገዛ ራሱን የቻለ እንደሆነ መስክሯል፡፡

ሁለተኛውን ቢሆናል በተመለከተ ደግሞ «ቁርአን ከደበዘዙበት ያለፉ እምነቶችና ተልዕኮዎች የተቀዳ ነው» የሚል ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በመሰረቱ ታሪክም ይሁን አመክንዮ የቁርአንን ተልዕኮ ካለፉ መልዕክቶች ጋር ማነፃፀርን አይፈቅዱም፡፡ ምክንያቱም በቁርአን ከሪም ውስጥ እና በአይሁዳውያኑ ወይም በክርስትና መፅሐፍት ውስጥ ብዙ የይዘት መመሳሰሎች አሉ፡፡ ይህንን ደግሞ ራሱ ቁርአን ከሪምም ያረጋግጠዋል፡፡

ጉዳዩ ታዲያ የመፅሐፍቱ ባለቤቶች እንደሚሞግቱት ካለፉት ድርሳናት መቀዳትን ያሳያል ወይስ ሙስሊሞች እንደሚያረጋግጡትና ትኩረት እንደሚሰጡት የመለኮታዊ ምንጫቸውን አንድነት ያሳያል? መረጃዎች ሁሉ የሚጠቁሙት የሁለተኛውን ልከኝነትና የመጀመሪያውን ቅጥፈትነት ነው፡፡

ቁርአን እንዳመለከተው ከሆነ ከቀደሙት መፅሐፍት ጋር ያለው ቁርኝት የ«ማረጋገጥ» እና የ«ተቆጣጣሪነት» ግንኙነት ነው፡፡

وَأَنزَلْنَا إِلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ الْكِتَابِ وَمُهَيْمِنًا عَلَيْهِ

«ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በእውነት አወረድን፡፡» (ማኢዳ 48)

ቁርአን እነርሱ ውስጥ ላሉ እውነታዎች ዕውቅና ይሰጣል፣ ላጋጠማቸው መዛባትም ማስተካከያን ያደርጋል፡፡ በተቀባይ ተማሪ እና በላቀ መምህሩ መሃል ያለው ልዩነት የሰፋ ነው፡፡

ድራዝ ቁርአን የመፅሐፉን ባለቤቶች እምነቶችና አጓጉል እሳቤዎች ያስተካከለባቸውን አናቅፅ ረዥም ዝርዝር ጠቅሰዋል፡፡ በእጃቸው ውስጥ ያለው ቅዱስ የሚሉት መፅሐፍ ውስጥ ያሉ የታሪክና የሳይንስ ግድፈቶችን

ያስተካከለበትንም ገልፀዋል፡፡ ከዚያም «በዚህ ሁሉ ውስጥ የቁርአን ባለቤት ዕውቀቱን ከነርሱ የሚወስድበት ምክንያትና የመምህርነታቸው ቅርፅ ይታይሃልን? ወይስ በተቃራኒው ከነብዩ (ሰዐወ) ስህተቶቻቸውን የሚያርምና የከፉ ሁኔታቸውን የሚገልፅላቸው መመህር ይታይሃል?[208] ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡

ቀጥለውም «በመካው ዘመን የወረዱትን ነህልና ነምል ምዕራፎች ውስጥ ያሉ የመፅሐፉ ባለቤቶች ያልተስማሙባቸው ግን ከኢስላም መሰረታዊ ዓላማዎች ያደረጋቸውን አናቅፅ ተመልከት፡፡»[209] መልዕክተኛው (ሰዐወ) የተወለዱበትና ያደጉበት የጣዖታዊ ባህል ተጨባጭ ደግሞ ቁርአን በምዕራፎቹና አናቅፁ የገለጣቸውን የላቁ የእሳቤና መርህ ለማበልፀግ ችሎታ የሌለውና የራቀ ነው፡፡

ቁርአን መለካት በማይቻል መልኩ የወቅቱን መንፈስ፣ የዕውቀት እንዲሁም ባህል ደረጃ አሻቅቦ በከፍታ ያለፈ መፅሐፍ ነው፡፡ በዐረቦችም ይሁን ሌሎች መልዕክቱን በተጎነጩ ህዝቦች ላይ የተፈጠረው የመንፈሳዊና ማህበረሰባዊ አብዮት ምስጢሩም ይህ ነው፡፡ ሆኖም ቁርአንን የዘመኑ መንፈስ ወይም ደግሞ የከባቢው ውጤት ነው ብሎ የሚናገር ማንም አካል እውነታን የማይቀበል ጉረኛ ወይም ቁርአን በሚወርድበት ወቅት የዓረቦችን ነባራዊ ታሪክና ተጨባጭ የማያውቅ መኃይም ብቻ ነው፡፡

ድራዝ ቁርአን የወቅቱን ከባቢ የሚወክል ነው ብለው በሚናገሩት ላይ «ትክክለኛው ወካይ ምሳሌ ይህን ተናጋሪው ነው፤ ከዚያ ግን አንሻፎ ምሳሌ ሰጠ፡፡»[210] ብለው ያሾፉበታል፡፡

ቀጥሎ ቁርአናዊው መልዕክት ቅኝትና የቋንቋ ተዓምራዊ አብነቱም ተገዳዳሪ ሆኖ መጣ፡፡ ነብያችን (ሰዐወ) ከአላህ (ሱወ) በሆነ ትዕዛዝ መላውን የሰው ልጅም ይሁን አጋንንት የቁርአንን መሳይ ወይም ከርሱ አንዲትን ምዕራፍ

---

[208] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም 61
[209] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም 62፡፡ ድራዝ እዚህ ጋር ማለት የፈለጉት ከሱረቱን-ነምል 76ኛውን አንቀፅና፤ ከሱረቱ ነህል ደግሞ 63-64 ያሉትን አናቅፅ ነው፡፡
[210] ድራዝ፣አን-ነበኡል ዐዚም 59

ያመጡ ዘንድ ተገዳደሩ፡፡ «ለተዓምር ከመሸነፍ የበለጠ ምን ምስክርነት አለውን ?»[211] ይላሉ ድራዝ፡፡

ይህ ዓይነቱ መገዳደር ባለቤቱ ከራሱ ልቦና ያወጣውና የፈጠረው የሚወጣ አይደለም፡፡

ነገርግን «የራሱን አቅም የሚያውቅ ሰው የሚንደረደርበት ጀብዱ ሳይሆን፤ በሰማያዊ ዜናዎችና ልዩ ኃይል እጆቹን ያስታጠቀ ሰው ተግባር ብቻ ነው፡፡»[212] ይላሉ ድራዝ፡፡ ሁለቱ ቢሆናሎች ከተነቀፉና ውድቅ ከተደረጉ በኋላ የሚቀረው እውነታን ብቻ ለሚፈልግ አካል አንድ የመጨረሻ አማራጭ ነው፡፡ እርሱን መቀበል ግዴታ ይሆናል፡፡ እርሱም ቁርአን ከሪም የዘመንና ቦታ ድንበር ከማይገድበው አዋቂ ፈጣሪ (ሱወ) ወደ ታማኙ ነብይ (ሰዐወ) ልቦና የተወረደ መሆኑን ተቀብሎ ማመን ነው፡፡

በዚህ መልኩ ነበር ድራዝ በመረጃ በፋመውና በሎጂካዊ ከበባ ብዬ በጠራሁት ዘዴ የቁርአንን መለኮታዊ ምንጭነት እጅ ወደ መስጠት የመሩን፡፡ ከፊትለፊታች ከርሳቸው ጋር «ይህ ቁርአን በተፈጥሮው የሰው ልጅ የስራ ውጤት መሆንን አይቀበልም፡፡ በሁኔታዊ የቋንቋ ጥሪው የቀዷ ቀደር መልዕክት እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ሌላው ቀርቶ ምድረ-በዳ ወይም በረሃ ላይ ተጥሎ ቢገኝ እንኳ፣ በጥልቀት የተመለከተው ሁሉ የዚህ መፅሐፍ መፍለቂያና መብቀያው የምድር አፈር ሳይሆን ከሰማያት አድማስ ውስጥ ብቅ ያለና የወረደ መሆኑን እርግጠኛ ይሆናል፡፡»[213] ብለን ከመቀበል ውጪ ምርጫ የለንም፡፡ ቁርአን ከወረደበት የታሪካዊ ዳራ እና የመልእክቱ ይዘት የሚጠቁሙት እና ከመልዕክቱ ተሸካሚ ሕይወት ዙሪያ የሚገኙ አስረጂዎች የሚደግፉት ብቸኛው ቢሆናል ይህ ነው፡፡ ቁርአን የሰውን ልጅ የፈጣሪን አፈጣጠር ዝንብን እንኳ በመፍጠር ወይም ቁርአንን መሳይ አንዲት ምዕራፍ በመፃፍ ይመሳሰሉና ይፎካከሩ ዘንድ

[211] ያለፈው ምንጭ
[212] ያለፈው ምንጭ
[213] ድራዝ፣ አን-ነበኡል ዐዚም 77

ተገዳድሯል፡፡ በአፈጣጠርና ጉዳዮቹ የፈጣሪን አንድነት አመላካች የሆኑ ዝንተ-ዓለማዊ ተግዳሮቶች መኖራቸው ምንኛ ከባድ ነው !

أَلَا لَهُ الْخَلْقُ وَالْأَمْرُ ۗ تَبَارَكَ اللَّهُ رَبُّ الْعَالَمِينَ

«ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡» (አል ዕራፍ 54)

**የአዕምሮ መቀራረብ**

በዚህ ጥናት መቅድም ላይ በዶክተር ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝና በፈላስፋው ማሊክ ቢን ነቢ መሃል ያለውን የአስተሳሰብ ቅርርቦሽ ጠቁመን ነበር፡፡ አሁን ደግሞ በዚህ ቅርርብ ስልታዊ መሰረቶች ዙሪያ በዝርዝር ልናይ ነው፡፡

የነዚህ ሁለት የላቁ አሳቢያን ትልቁና ዋነኛ ጭንቀት ቁርአን ከሪም በአመክንዮ ወደ ሰው ልጅ ምንጭነት የሚጠጋ እንዳልሆነ መግለፅ፣ ጤናማ የሆነ አዕምሮም ከመለኮታዊ ምንጭ እውነታው መሸሽ እንደማይችል ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሁለቱም ተመሳሳይነት ያለውን ስልት ነው የተጓዙት፡፡ የዚህን ዕውቀት አስኳል የድራዝ ባልደረባና የሕይወት ጉዞዎች ሁሉ ጓደኛቸው ማሊክ ቢን ነቢ በፈረንሳይኛ ቋንቋ በፃፈው «አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ» መግቢያ ላይ በግልጽ እንዲህ ሲሉ ፅፈውታል፡፡ «በጥቃቱ ውስጥ ዋናው ጉዳይ የቁርአን እውነተኛ ምንጭ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ከተላከው ሰው ዕውቀትና ምርምር ተጨምቆ ወጣ ? ወይስ የዚህ ተቃራኒ ነው ? የሚለውን እናውቅ ዘንድ ነው፡፡ ምንጩ

ላዕላይ መለኮት እንደሆነ እናምን ዘንድ የሚያስገደዱን አያሌ ምክንያቶች ስላሉ ነው፡፡»[214]

ቀደም ሲል ያየናቸው ሶስት ቢሆናሎች ሁለቱን ተራና ውድቅ አድርገው የሶስተኛውን እውነተኝነት «አን-ነበኡል ዐዚም» እና «መድኸል ኢለል ቁርአኒል ከሪም» ላይ ድራዝ በሚገባ ገልፀዋቸዋል፡፡ እነርሱን ማሊክ ቢን ነቢ ጠንከር አድርጎና በጥልቀት በ«አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ» መፅሐፉ ላይ በተመሳሳይ መንገድ ደስሷቸዋል፡፡

ማሊክ ቢን ነቢ በዚህ ጉዳይ ላይ ድራዝ ቀደም ብለው የፃፉትን አንብቧልን ? ወይስ እንደ ሰኮና የሀሳብ ውልብታዎቹ ተመሳስለው ወድቀው ነው ? እንዲሁ ስናየው የሚሆነው ሁለተኛው እንጂ የመጀመሪያው አይደለም፡፡ የሁለት ፈረሶች እኩል እርምጃ ዓይነት ነው፡፡ ድራዝም ይሁኑ ማሊክ ቢን ነቢ ተመሳሳይ የእሳቤ ተግዳሮቶችን አስተናግደዋል፡፡ ተመሳሳይ የአየር ንብረት ያለው የዕውቀት ከባቢ ውስጥ ኖረዋል፡፡ እርሱም የፈረንሳይ የእውቀት ባህል ነዋሪና የኦሬንታሊዝሙን ዓለም በጥልቀት ያነበበና ያጤነ ነው፡፡ የቁርአንን ትክክለኛነት ለማምታታት የተባሉ ዋናዋና አሻሚ ሐሳቦችን ፈትሸዋል፡፡ ሁለቱም የሰሉ ብዕሮቻቸውን እና ብሩህ አዕምሯቸውን እነዚህን ማምታቻዎች ውድቅ ለማድረግ አስግረዋቸዋል፡፡ ተመሳሳይና አንድ ዓይነት ወደ ሆነ ወጤትም ደርሰዋል፡፡

ድራዝ የማሊክ ቢን ነቢን ጥናት በሚያምር ውዳሴ እንዲህ ነበር ያሉት «የጥበብህ ስልነት፣ የእምነትህ ሙቀት፣ የቋንቋ አጠቃቀም ብቃትህ፣ የቅኝትህ ውበት (ይገርማል)፡፡ እነዚህ ሁሉ የጎሉ ባህሪያት ናቸው፡፡ ግን ደስታዬን ለመግለፅ እንኳ አልደረስኩም፡፡»[215] ይላሉ፡፡ ቀጥለውም በቁርአን ምንጭ ሳይንስ እያደረጉት ካለው ጥረት ጋር እንዴት ተመሳስሎሽ እንዳለውም

[214] ማሊክ ቢን ነቢ፣ አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ 15፡፡ ድራዝ ለመፅሐፉ ከፃፉት መቅድም
[215] ቢን ነቢ፣ አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ 11

አውስተዋል፡፡ በዚህ[216] ረገድ ማሊክ ቢን ነቢ ከድራዝ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የእሳቤ ድምዳሜና ፍሬ ላይ እስኪደርስ ምን ዓይነት መንገድ ቢከተል ነው ? ከዚህ በፊት ማሊክ ቢን ነቢ ልክ እንደ ድራዝ የቁርአንን ተልዕኮ ትክክለኛነት ለሌሎች ለማረጋገጥ መከተል የሚኖርበትን ዘዴ እንደገና መታየት እንዳለበት አንገብጋቢነቱን ተረድቷል፡፡ «በአጠቃላይ ለተለያዩ ምክንያቶች ቢሆንም ከፊሉ በዓለመል ኢስላም ከተፈጠረው የእውቀት ባህል ዕድገት ጋር የሚገናኝ ሲሆን የተቀረው ደግሞ የተዓምራት ዕይታችን የመሻሻል ችግር ብለን ስም ልንሰጠው የምንችለው ነው፡፡»[217]

በመሰረቱ የመጀመሪያው ምክንያት የሚሰራው በሙስሊም አዕምሮ ላይ የምዕራቡ ዓለም ባህል ካሳደረው ጥልቅ ተፅዕኖ ጋር ነው፡፡ «ስለዚህ ጉዳዩን አንድ ሙስሊም እያለፈባቸው ካሉ አዳዲስ ነገራት ከባቢዎችና በእምነትና መንፈስ ደረጃ ከሚገጥሙን ችግሮች አንፃርም ዳግም ማየቱ ግዴታ ነው፡፡»[218] የዘመኑን አዕምሮ መጠይቆች፣ በሁሉም እምነቶች ውስጥ እንግዳ ለሆነና በሰው ሰራሽ ህግ ገመዶች ላይ ለተንጠለጠለ ህሊና ሁሉ መልስ ሊሰጡ የሚችሉ አዳዲስ ስርዓተ-ትምህርታዊ ዘዴዎችን መገንባቱ ግድ ይላል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ በዚህ ዘመን ሰዎች የቁርአንን ቋንቋ በጥልቀት አለማወቃቸው ነው፡፡ ዓረብ ካልሆኑ ከሌሎች ሙስሊሞች በባሰ ሁኔታ በተለይ ደግሞ በዘመኑ ዐረብኛ ተናጋዎች ዘንድ እንግዳ የቋንቋ ማዳቀልና መደባለቅ ከተፈጠረ በኋላ ነው ችግሩ የባሰው፡፡ «በእውነቱ ከሆነ ዓረብ ያልሆኑ አገራት ያለ ሙስሊም (ጥቂቱ ሲቀር) የቁርአን አንቀፅና በጃሂሊ የስነ-ጽሁፍ ሪትም የተወቀረ ጽሁፍ ቢቀርብለት መለየት እስኪያቅተው የሚያስችለው ሚዛን ሊያጣ ችሏል፡፡ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ የዓረብኛን ቋንቋ ንፁህ ሪትም ስነ-ፅሁፋዊ ሚዛንና ልየታ በሚያስችል መልኩ አንዳይኖረን ያደረገ (አደጋ) ገጥሞናል፡፡ እንዲሁም

[216] ያለፈው ምንጭ
[217] ቢን ነቢ፣ አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ 53-54
[218] ያለፈው ምንጭ

እምነታችንን በርዕሰ ህሊናችን አሰርተን ከመያዝ ይልቅ ጭፍን ተከታይ ከሆንን ቆየን፡፡››[219] ይላል ማሊክ፡፡

በዚህ መልኩ ነው ማሊክ ቢን ነቢ የቁርአንን ቋንቋዊ ተዓምራዊ ዘውግ ብቻ ይዞ ሙጥኝ ማለትና በርሱው መብቃቃት የዘመኑ ሙስሊም ጉድለት እንደሆነ የደረሰበት፡፡

የቁርአን ተዓምራዊነት ጊዜያዊና ማብቂያ ያለው አይደለም፤ እንዲሁም መረዳቱ በዓረብኛ ስነ-ፅሁፍ በመጠቁና አገላለፁን በቀመሱት ላይ የተገደበ አይደለም፡፡

የቁርአን ተዓምራዊነት በመልዕክቱ አጠቃላይነት መጠን እውነተኛ የቁርአን እና ዘውታሪ ድንቅ ተዓምር ነው፡፡ ማሊክ ቢን ነቢ ዛሬ ላይ የቁርአንን ተዓምራዊነት በዚህ መልኩ እንረዳ ዘንድና በሶስት መስፈርቶችም የሚገለፅ መሆን እንዳለበት ነው ያስገነዘበው፡፡

**አንደኛ**፡- በሁሉም አረዳድ ልክ መሆኑ፣ መረጃነቱ ከተገዳዳሪ ግንዛቤ በላይ መሆኑ ሎጂካሊ ዋጋ የለውም፡፡[220]

**ሁለተኛ**፡- ‹‹ከሁሉም ችሎታ በላይ ከፍ ያለ መሆኑ››[221] ተዓምር ተገዳዳሪን ማድከም ግዴታው ነው፡፡

**ሶስተኛ**፡- ‹‹ተፅዕኖው በእምነቱ ውስጥ የመኖሩን ያህል እኩል ሲሆን፡፡››[222]

ለዘልዓለማዊው መልዕክት ተዓምራዊነት የጊዜም ይሁን የቦታ ገደብ ምንም ተፅዕኖ አያደርግበትም ለማለት ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ነበር ማሊክ የጥናቱን ማጠንጠኛ ወደ ገነባበት የላቀ ውጤት ላይ የደረሰው፡፡ እርሱም ‹‹የቁርአን ተዓምራዊነት እንደ ዑመር (ረዐ) ወይም ወሊድ ያለው ንፁህ ዓረባዊ ተፈጥሮ ያለው በልሳነ- ጥዑሙ አሊያ ደግሞ በዕውቀታዊ ዘዴ እንደ ጃሒዝ ያለው

[219] ቢን ነቢ፣ አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ
[220] ቢን ነቢ፣ አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ
[221] ያለፈው ምንጭ 64
[222] ያለፈው ምንጭ 65

የሚረዳው የሆነ ከዘመናትና ትውልዶች ውስጥ የሚያልፍና የተቆራኘ መሆኑ ግድ ሆኖ ግን፤ ዛሬ ላይ ያለው ሙስሊም የጃሂሊያውን ዘመን ተፈጥሮም ይሁን በዓባሲው ስርወ-መንግስት ዘመን የነበረን የቋንቋ ድርና ማግ ልሂቅ ችሎታ አጥቷል፡፡ እንዲህ ቢሆንም ቅሉ ቁርአን አስኳሉ እንጂ ተከታዩ ስላልሆነ ተዓምራዊነቱን አያጣም፡፡ ሙስሊም ቁርአንን በሌላ ቅርፅና ሁኔታው ይኗኗረው ዘንድ ይገደዳል፡፡

ከቋንቋዊ አገላለፅ ውቅሩ ይልቅ ከዓላማውና ስነ-ልቦናዊ አወቃቀሩ አንፃር አናቅፁን ይኗኗራል፡፡ በትምህርት ዘዴውም ለውስጣዊ ንቃተ-ህሊና ትንታኔ በተግባር ያወርደዋል፡፡»[223]

በዚህ መልኩ ማሊክ ቢን ነቢ የቋንቋዊ ምጥቀት ተዓምርን ብቻ ወደ ጎን ተወት አድርጎ፣ በሌላ የተዓምራዊነት ቅርፆች ለወጠው፡፡ ከአድማሱ ስፋትና ርዝመት አኳያ «የቁርአን ምንጭ ሳይንስ» ብለን በሰየምነው ውስጥ የሚካተትም ሆነ፡፡ የቁርአንን ምንጭ መለኮታዊነት ከሚያረጋግጡ ሳይንሳዊ ተዓምራት፣ ታሪካዊና ስነ-ልቦናዊ ትንታኔዎች እንዲሁም ከሌሎች እምነቶች ጋር ንፅፅርን በሙሉ አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

ጥናታቸውን ሲሰሩ «ከቋንቋ የተብቃቃ»[224] እንዲሆን ወስነው «መድኸል አለል ቁርአኒል ከሪም» በተሰኘው መፅሐፋቸው ወደ ዘርፉ ድራዝ ቀዳሚ ነበሩ፡፡ ነገርግን ማሊክ ቢን ነቢ መንገዱን በመከተል እስከ ጥግ አድርሶታል፡፡ ከቁርአን ውስጥ ሱረቱ ዩሱፍን እና ብሉይ ኪዳንን በአስገራሚ ንፅፅር አሳይቷል፡፡[225]

ኡስታዝ ማሕሙድ ሙሐመድ ሻኪር የማሊክ ቢን ነቢን መፅሐፍ አስመልክተው ዳጎስ ባለ መቅድሙ ላይ እንደጻፉት «ራሱን የቻለ ዘርፍ የያዘ

[223] ቢን ነቢ፣ አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ 67
[224] ድራዝ፣ አል-መድኸል ኢለል ቁርአኒል ከሪም 13
[225] ቢን ነቢ፣ አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ 211-254

መፅሃፍ ላይ መቅድም መፃፍ ለኔ ከባድ ነገር ነው፡፡ ከዚህ በፊት መሰሉን የፃፈ አለ ብዬ አላስብም ቀዳሚም ነው፡፡»[226] ይላሉ፡፡

ይህ ጥናት የድራዝ ብቻ ስለሆነ የማሊክ ቢን ነቢን መፅሐፍት ይዘት ከዚህ በላይ መቀንጨብና ማምጣት አልቻልንም፡፡ «አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ» የተሰኘው የማሊክ መፅሐፍ በዚህ ጥናት ጫፍ ላይ መቀንጠብ ክብሩ አይደለም፡፡ ይዘቱ ጥልቅ ስለሆነ የማሊክን እሳቤዎች ለመዳሰስ በሌላ ጥናት እንመለስ ይሆናል፡፡

እዚህ ጋር የፈለግነው በሁለቱ ሰዎች መሃል ያሉ መመሳሰሎችን መንቀስ ነው፡፡ በሁለቱ መሃል ያለው የአዕምሮ መመሳሰልን ስናጠቃልለው ድራዝ የቁርአንን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከቋንቋዊ ተዓምራዊነት ይልቅ እርሱን ያለፈ ሌላ አዲስ መንገድ እንደሚያሻ አምነው ገልፀው ጀመሩት፡፡ በዚህ የመንገድ በር ማሊክ በአስተማማኝ እርምጃዎች ገባ፡፡ ዛሬ ድረስ እነዚህን የብርሃን ፈለጎች መከተል ለኛ ግድ ሆነ ነው፡፡

---

226 ያለፈው ምንጭ 17

## ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት ውስጥ ዶክተር ሙሐመድ ዐብደላህ ድራዝን፣ በዘመናዊው የኢስላማዊ አስተሳሰብ ውስጥ በተለይ በወሰጢያና ተጅዲድ ዘርፍ የሰነዘሯቸውን የላቁ እሳቤዎች በትኩረትና ስፋት ለማስተዋወቅ ሞክረናል፡፡

የድራዝን የሕይወት ታሪክ፣ የስብዕናቸውን ልምላሜዎች፣ የእሳቤ ዳናቸውንና የአፃፃፍ ዘውጋቸውን አቅርበናል፡፡ ለዚህ ከ20ኛው ክፍለዘመን ከነበሩ ክስተቶች አንዱ የዕውቀትም ይሁን ተግባር ውርስ የሚቋትላቸው ከቁርአን አል-ከሪም እንደሆነም ገልጸናል፡፡

በየትኛውም የኢስላም ዘመን የሰላ አዕምሮ እንጂ ቦይ ሊያበጅላቸው ያልቻሉ አምስት ጣምራዎች ማለትም አዕምሮና አንቀጻዊነት፣ ኃይማኖትና ሳይንስ፣ ምርጫና ግዳጅ ሱና እና ቢድዓ እንዲሁም ሰላምና ጦርነትን በተመለከተ የተጓዙባቸውን የሚዛናዊ እሳቤ አበርክቶዎች ዳሰሰናል፡፡ ድራዝ ከነዚህ ጣምራዎች ጋር በጥልቀትና ስፋት፣ በዕውቀት ዝግጅትና በሚዛናዊ ዕይታ እንዴት በተለየ ሁኔታ እንደተናኗሩ አብራርተናል፡፡

ቀጥለን የድራዝን የተሐድሶ እሳቤ ማዕዘናት ገለፅን፡፡ ለሁለት አዳዲስ የቁርአን ሳይንስ ጥናቶች የዕይታ መሰረቶችንም እንዳኖሩ አብራራን፡፡ሁለቱ የጥናት ዘርፎች «ዒልመል አኽላቅ አል-ቁርአን» እና «ዒልመ መስደሩል ቁርአን» ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ዘርፍ ለብቻቸው የመሰረቱት ሲሆን፤ ሁለተኛውን ዘርፍ ግን መሰረቱን በማኖር ላይ የእውቀት ጉዞ ባልደረባቸው፣ የኢስላማዊው ስልጣኔ ፈላስፋ ማሊክ ቢን ነቢ አግዟቸዋል፡፡ ይህ ጥናት በድራዝ ውስጥ ያሉ የወሰጢያና ተሐድሶ ጎልቶ መታያዎችን የገለፀ፣ ቀለማቸው የሰነዳቸውን ድርሳናት አንባቢ ለማንበብ ይነሳ ዘንድ እንመኛለን፡፡

ስለ ድራዝ ከራሳቸው ብዕር የተሻለ፣ መንፈስና ህሊናቸውን በመጽሐፍቶቻቸው ውስጥ ሲያቋርጥ ተጓዥ ገላጭ የለም፡፡ አላህ ጥበብንና የንግግር ምጥቀትን በርግጥ ሰጥቷቸዋል፡፡

ምስጋና መልካም ነገራት በፀጋዎቹ ለሚሞሉት አላህ የተገባ ነው፡፡



ደክተር ሙሐመድ ሙኽታር አሽ-ሺንቂጢ ሞሪታኒያዊ ፀሃፊ፣ ኳታር በሐመድ ቢን ኸሊፋ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በኢስላማዊ ጥናት የትምህርት ክፍል ውስጥ የእምነቶች ታሪክ ፕሮፌሰርና አስተማሪ ሲሆኑ፤ ከዚህ በፊት በየመን ዩኒቨርሲቲ የተፍሲርና ነሕው መምህር ነበሩ።

የጥናቶቻቸውና የትኩረታቸው አቅጣጫ ብዙው የኢስላም ፖለቲካዊ ፊቅህ፣ የእምነቶች ንፅፅር፣ የማንነት ጉዳዮች እና የዐረብ-ምዕራቡ ግንኙነት ላይ ነው።

ከብዙ የሞሪታኒያውያን ዓሊሞች ጋር ተቀምጠው ፊቅህ፣ ኡሱልና ነሕውን ተምረዋል። የብቃት ምስክር ወረቀቶችን (ኢጃዛ) አግኝተዋል። ከኢብኑ ዓባስ ኢስላማዊ ማዕከል በፊቅህና ኡሱል ዲግሪያቸውን፣ ከአንዋክሾጥ ዩኒቨርሲቲ በዐረብኛ፣ ፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ የትርጉም ስራ ዲግሪን ያገኙ ሲሆን የመን ውስጥ በኢማን ዩኒቨርሲቲ የተፍሲርና ነሕው መምህር ሆነው አገልግለዋል።

ወደ አሜሪካ በመጓዝ ከደቡብ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ በጄነራል ማኔጅመንት ማስተርስ ዲግሪ፣ ከቴክሳስ ቴክ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በእምነቶች ታሪክና ጥናት ማስተርስ ዲግሪና ፒኤች ዲግሪያቸውን ጨርሰዋል።

በዐረብኛና እግሊዝኛ ብዙ መፅሐፍትንና ጥናቶችን አዘጋጅተዋል። ለሕትመትም በቅተው በተለያዩ የዓለም አገራት ቋንቋዎች ተተርጉመውላቸዋል። አል-ጀዚራ ኔት ላይ በቋሚነት በልዩ ትንታኔ የታቀቱ ፅሁፎችን ይፅፋሉ።





አሳታሚ
الوسطية للنشر والتوزيع
Al-Wasatiyyah Publishing